www.abyssinialaw.com

# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

ለቅድመ ስራ ስልጠና ሰልጣኞች የተዘጋጀ
የስልጠና ሞጁል

# የንግድ ሕግና ህገ-መንግስት

በፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ

www.abyssinialaw.com

# ማውጫ

**መግቢያ**

1. የንግድ ህግና ህገ-መንግስት ....6
   የንግድ ስራ ከህገ-መንግስቱና ሌሎች አዋጆች ኣንፃር ....6
   ከፍ/ብሄር ህጉ አንፃር ....8
2. የንግድ መደብር ....9
   ስለ ንግድ መደብር በጠቅላላ ....9
   የንግድ መደብር የሚቋቋምባቸው መብቶች ....10
   ደንበኛ ገብያተኛ ....10
   ተገቢ ያልሆነ ውድድር ....11
   የአእምሮ ንብረትና ህገመንግስቱ....14
   የፈጠራ ስራ ....15
   ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ....24
   የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ....26
   የንግድ ምልክት....33
   በንግድ መደብር ላይ የሚደረግ የዋስትና መያዣ ....40
   **የመወያያ ነጥቦች....44**
3. የንግድ ማህበራት....45
   ስለ ንግድ ማህበራት በጠቅላላ ....45
   የሽርካ ማህበር 48
   የሽርካ ማህበር ኣጠቃላይ ገፅታ ....48
   የኣባላት መብቶችና ግዴታዎች ....51
   የማህበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት ....52
   እሽሙር ማህበር....53
   ኣክስዬንና ሃላፊነቱ የተ.የግ.ማህበር ....55
   የኣክስዬን ማህበር ምስረታ ....56
   አጠቃላይ ይዘት ....57
   የኣክስዬን ማህበር ጥቅምና ጉዳት ....57
   የማህበራቱ መፍረስ....58
   ሒሳብ ማጣራት ....63
   **የመወያያ ነጥቦች....66**
4. የኢንሹራንስ ውል ህግ ....67
   ስለኢንሹራንስ ውል በጠቅላላ ....67

የኢንሹራንስ ውል አመሰራረት ...................................................................68
የኢንሹራንስ መሰረታዊ መርሆች...............................................................72
የጉዳት ካሳ መሰረተ ሓሳብ.....................................................................72
የኢንሹራንስ ውል ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ...............................................74
መዳረግ 77
መዋጮ 78
ቀራቢ ምክንያት ..................................................................................79
አርቦን ..............................................................................................83
መሸሸግና የሐሰት መግለጫ .....................................................................89
አደጋ ከኢንሹራንስ አንፃር .....................................................................91
ስለአደጋ በጠቅላላ.................................................................................91
መግለጫ የመስጠትና የማስታወቅ ግዴታ.......................................................93
**የመወያያ ነጥቦች...............................................................96**
5. የማጓጓዥ ውል ህግ............................................................................98
ስለማጓጓዣ ውል በጠቅላላ.......................................................................98
የየብስ ማጓጓዣ 99
የአጓዡ ካሳ የመክፈል ሃላፊነት...............................................................102
የሚከፈለው የጉዳት ካሳ .......................................................................103
የኣየር ማጓጓዣ 104
የአጓዥ ሃላፊነት .................................................................................105
የኣጓዥ የተወሰነ ሃላፊነት......................................................................107
የባህር ማጓጓዣ 109
ስለባህር ማጓጓዣ በጠቅላላ .....................................................................109
ቢል ኦፍ ሌዲንግ...................................................................................110
የአጓዥ ሃላፊነት ..................................................................................113
5.4.4 የሃላፊነት ወሰን.........................................................................115
5.4.5 ስለ ይርጋ ..............................................................................116
**የመወያያ ነጥቦች..............................................................118**
6. የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነዶች ህግ ..............................................................119
ስለሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በጠቅላላ ......................................................119
ሰነድን በቅን ልቦና መያዝ.......................................................................121
የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶ ዋናገፅታዎች........................................................122
የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች መቃወምያዎች ...................................................125
የመተላለፍያ መንገዶች..........................................................................131

የንግድ ወረቀቶች.....133
የሃዋላ ወረቀት .....133
የተስፋ ሰነድ .....136
ቼክ .....137
የመንገድ ቼክ .....143
6.6.5 በሰነዶች መካከል ያለልዩነትናተመሳሳይነት.....144
**የመወያያ ነጥቦች.....145**
7. የመክሰር ህግ.....146
የመክሰር ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ.....146
የመክሰር ህጉ ተፈፃሚነት.....150
የሽርካ ማህበር መክሰ .....151


## የአክስዮን ማህበር መክሰር153


**የመወያያ ነጥቦች.....157**
ማጠቃለያ.....158
ማገናዘብያዎች.....159

# መግቢያ

የሰው ልጅ ትርፍ ወደ ማምረት ከተሸጋገረበት ጥንታዊ ስልጣኔ ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን ከግዜ ወደ ጊዜ እድገት እያሳየ የመጣው ንግድ ዓለምችን አሁን ያላትን ገፅታ እንድትይዝ ካደረጉት አበይት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ይህንን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በአንድ አከባቢ በሚኖሩ ህዝብች መካከል ከሚደረግ የዕቃ በዕቃ ልውውጥ አንስቶ የሰው ልጆች ባህር ኣቋርጠውና ረጅም ተጉዞው ከጫፍ እስከ ጫፍ የዘለቀ የንግድና ቴክኖሎጂ ምጥቀት አሁን ያለው ትውልድ የተሻለ ሂወት እንዲኖረውና የዓለም ማህበረ ሰብ በአንድ መንደር የመኖር ያክል እንዲቀራረብ ኣድርጎታል፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንታዊቷ ግብፅ፣ ግሪክ፣ ፐርሺያ፣ ህንድና ቻይና የንግድ ልውውጥ ታደርግ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስነብባሉ፡፡ ከዚህ ጥንታዊ የንግድ ግንኙነቷ አንፃር ሲታይ እምብዛም በተፈለገው ደረጃ አድጓል ለማለት የማያስደፍረው የኢትዮጵያ ንግድ በመጠኑም ቢሆን ግን ለዓለማችን ከተበረከተው የእድገት ትሩፋት ተካፋይ ለመሆን ግን ችሏል ፡፡ ለዚህም ነው ከ1923 የብድርና ባንክ አሰራር ህግ በ1933 የንግድ ማህበራት አዋጅና የመክሰር ህግ አዋጅ ከወጣበት ጊዜና ኋላም በ1952 ዓ.ም የንግድ ህጉ ከታወጀ በኃላ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ከዓለም ጋር ለመነገድ በርካታ ጥረቶችን ስታደርግ የምትስተዋለው፡፡ ይህ የዓመታት ጥረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ የንግዱ ዘርፍ በነፃ ገበያ መርህ እንዲሄድ በመደረጉ መንግስት የነደፈው ግብርና መር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችሉና የንግድ ግንኙነቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

የዚህ በንግድ ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ርእሰ ዙርያ የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል ዓላማም ሰልጣኞች በከፍተኛ ትምህርት ቆይታቸው ያገኙትን እውቀት፣ ክህሎች እና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በማስፋትና በማነፅ ይህን በመሳርያነት ተጠቅመው የሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን በማጠናከሩ ሂደት ተገቢውን ፍትህ ለተልጋዩ ህ/ሰብ በመስጠት በመላ አገሪቱ መልካም አስተዳደርን በማሰፈን ጠንካራ የፍትህ ስርዓት እንዲገነቡ ለማስቻል ነው፡፡

የሞጁሉ አዘገጃጀትና ይዘት በተመለከተ በተዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንግድ ህገና ህገ-መንግስት፣ የንግድ መደብር (መድብል)፣ የንግድ ማህበራት፣ የኢንሹራንስ ህግ፣ የማጓጓዥ ውል ፣ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ስለመክሰር በሚሉ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ሆኖ በነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ከህግ ኣተረጓጎምና አተገባበር ጋር ተያይዘው ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዬችን በተለይ ደግሞ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት በኃላ በወጡ የተለያዩ ኣዋጅ

ዙርያ ሰፋ ያለ ማብራርያ በሚሰጥ መልኩና በእያንዳንዱ ርእሰ መጨረሻ የመወያያ ነጥቦች በማንሳት ለውይይት መነሻ ሊሆን በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡

ስለዚህ ሰልጣኞች ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት መውጣት በኃላ የህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ፖሊሲንና ስትራተጅን መሰረት በማድረግ የወጡ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ኣዋጆች በሚገባ ተረድተው ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ አገሪቱ እየተከተለችው ያለውን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት መሰረት በማድረግ ለፈጣን፣ ዘላቂና ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበት የልማት ስትራተጂ ስኬታማነት እንዲያገለግል በሚያስችል መልኩ እንዲተገበር በማድረግ ሙያዊና ዜግነታዊ ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ የዚህ ሞጁል ዋና መልእክትም በእውቀት፣ ክህሎትና ዲሞክራሲ አስተሳሰብ የታነፀ የፍትህ አካላት ባለሙያ በመሆን የተገልጋዩን ህብረተሰብ የፍትህ ጥም በማርካት ህዝባዊ አመኔታን ለማግኘት አበክረን ልንሰራ ይገባል የሚል ነው፡፡

**መልካም ንባብ!!**

# 1. የንግድ ህግና ህገ -መንግስቱ

## *1.1 የንግድ ስራ ከህገ-መንግስቱና ሌሎች አዋጆች አንፃር፣*

ንግድ በዓለማችን ካሉ ቀደምት ግንኙነቶች አንዱና ዋናው የእድገት መሳርያ ነው፡፡ በንግድ ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ላይ አንዳንድ ሃሳቦችን አንስቶ በማየቱ ሂደት ለአጠቃላይ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ንግድ ምንድን ነው? ከሚለው ብንጀምር ንግድ ማለት " A regularly carried out and organized production exchange of goods and services under taken with the objective of earning profit and acquiring wealth through the satisfaction of human needs." የሚል ፍች የሚሰጠው ነው፡፡ የንግድ ስራ ሸቀጦችና አገልግሎቶች ለዋጋ ሲባል መሸጥ ማስተላለፍና መለወጥ፣ ሁሌ የሚከናወን የግብይት ሂደት ያለው፣ ለትርፍ ሲባል የሚከናወን የመሆንና እርግጠኛነት የሌለው የመክሰርና የትርፋማነት ውጤት ሊያስከትል የሚችል ባህሪ ያለው መሆኑ ከመገለጫዎቹ ባህሪያት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የንግዱን ክፍል ኢኮኖሚ በሁለት ማለትም የኢንዱስትሪና የሸቀጥ አገልግሎቶች ክፍለ ኢኮኖሚ በሚል ክፍሎ ማየት የሚቻል ቢሆንም ሁሉም ዘርፎች ለአንድ አገር ኢኮኖሚ እድገት ያላቸው አስተዋፅኦ እጅግ የላቀ ነው፡፡ የሸቀጦችና አገልግሎቶች ዘርፉን (commerce) ወስደን የተመለከትን እንደሆነ በዚህ ዙርያ ያሉ ክፍለ ኢኮኖሚዎች እንደ ባንክ፣ መጓጓዣ፣ ኢንሹራንስ፣ የማሸግ ስራና የማስታወቅያ ስራዎች ናቸው፡፡ የአገራችንን ንግድ ህግና ህገ-መንግስት ስናይ የሰው ልጆች የዕለተ ተዕለት ኑሮን ለማሻሻልና ብሎም ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ለመራመድ የሚያስችል የኢኮኖሚ ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ግንኙነቶች በተፈለገው መንገድ ለማስኬድ የግድ በህግ መገዛትን ስለሚጠይቅ በአገራችንም በ1952 ዓ.ም የንግድ ህግ ወጥቶ እንሆ ለግማሽ ምእተ ዓመት ገደማ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 43(1) ላይ "የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡" በማለት የደነገገውን መሰረት በማድረግ ለአገሪቱ የልማት እድገት ይበጃሉ ያላቸውን በርካታ ህጎች በማውጣት የንግድና የኢንቨስትመንት ስራው ከማንኛውም ግዜ በበለጠ አጠናክሮ እየሰራበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ህግ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ከመውጣቱ በፊትና ዓለም አሁን ወደ ደረሰችበት ዘመነ ግሎባላይዘሽን ከመድረሷ በፊት የወጣ በመሆኑ የራሱ የሆኑ እጥረቶች ሊኖሩት እንደሚችሉ ለመገመት ባይከብድም ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አኳያ ሲታይ መንግስት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 51 (2)፣ 51 (9)፣ 55 (ሐ) እና 77 (6) ፣ 91 (3) እና 89( 1)

www.abyssinialaw.com

የተደነገጉ መንግስታዊና ሃገራዊ ግዴታዎቹን ለመወጣት በንግዱ ዘርፍ በን/ህ/ቁ 86-114 የህግ ሽፋን አግኝቶ ለዓመታት እየተሰራበት ከቆየው ህግ በተጨማሪ ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ኣዋጆች እንደ አዋጅ ቁጥር 67/89 በማውጣትና በየጊዜው በኣዋጅ ቁጥር 171/91፣ 328/95፣ 87/95፣ 95/96 እና 376/96 በማሻሻል ይህን በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ እንደ ደንብ ቁጥር 13/89 እና ሌሎች በማውጣት የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራና አገሪቱ ከዚህ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን በማድረግ ላይ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአገራችን ያለውን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የሚመራበትን የውድድር ስርዓት ቀደም ሲል በን/ህ/ቁ 30-134 ባሉ ድንጋጌዎች የህግ ሽፋን ተሰጥቶት የነበረው ያልተገባ ውድድር (Unfair competition) ዘርዘር ባለና ከህገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ኣገራዊና አህጉራዊ የእድገት ደረጃን ባገናዘበ መልኩ ዓላማው ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትና ማህበራዊ ደህንነት ለማስፈን እና በነጋዴዎች መካከል የሚደረጉትን ፀረ-ውድድር የሆኑ ተግባራት በመቆጣጠር ለውድድር ኣመቺነት ያለው ስርዓት መገንባት መሰረት በማድረግ ኣዋጅ ቁጥር 329/95 በማውጣት የግብይት ስርዓቱ በህግ እንዲገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

እንዲሁም በን/ህ/ቁ 127(መ)፣ 148፣ 149 የተወሰነ ሽፋን ተሰጥቷቸው የነበሩትን የፈጠራና የቅጅ ግዙፍነት የሌላቸው የንግድ መደብር መብቶች አሁን አገራችን ከደረሰችበት የእድገት ደረጃና እነዚህ መብቶች ለዜጎች ካላቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆን በመነሳት ኣዋጅ ቁጥር 123/87 የፈጠራ፣ አስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግን በማስፈር ለመብቱ ሰፊ የህግ ሽፋን በመስጠት ዜጎች ከዘርፉ ተጠቃሚ በማድረግ ላይና የቅጅ መብትን ደግሞ በቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ኣዋጅ ቁጥር 410/97 በማውጣት ንግድ ህጉና በፍታብሄር ህጉ ከ1647 — 1674 ቁጥር ተሰጥቷቸው ከነበረው ሽፋን በእጅጉ የተሻለና ሰፊ የመብት ጥበቃ በሚሰጥ መልኩ አዲስ ህግ ወጥቶ እንዲሰራበትና ከን/ህ/ቁ 140-141 የተወሰነ ሽፋን ተሰጥቶት የነበረውን የንግድ ምልክት  በአዋጅ ቁጥር 501/98 ሰፊ የህግ ሽፋን እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ የንግድ ህጉ በቁጥር 179 ያለውን የንግድ መደብር በዋስትና መያዝና መመዝገባ ጉዳይ አሁን ካለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፈጣንነት ጋር ተጣጥሞ እንዲሄድ ባንኮች በዋስትና የሰጡትን ገንዘብ ቶሎ ሰብስበው ለሌላው ማበደር እንዲችሉ የምዝገባ ስርዓቱ በአዲስ ህግ እንዲገዛ ኣስፈላጊ በመሆኑ ኣዋጅ ቁጥር 98/90 ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የመክሰር ህግን መሰረት ባደረገ መልኩ በንግድ ህጉ 5ኛ መፅሐፍ ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ የባንኮችን ጉዳይ የሚመለከት አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 25/92 እንዲወጣ በማድረግ በርካታ ስራዎችን በመስራተ ላየ ይገኛል፤፤ ለአንድ አገር የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት የደም ስር የሆነው የማጓጓዣ ዘርፍም ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ በርካታ ሕጎች እንደ ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 468/97 የኢትዮያ የኣቬሽን ሴኩሪቲ ኣዋጅ ቁጥር 432/97፣ በበረራ ደህንነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የወጣ ኣዋጅ

ቁጥር 31/88 በማውጣት በህገ-መንግስቱ በግልፅ የሰፈሩትን የልማት፣ የሰላምና የዲሞክራሲ ፖሊሲና ስትራተጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

## 1.2 ከፍ/ብሄር ህግ አንፃር፤

ህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 41(1) "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በአገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደርያው የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው፡፡" በማለት የዜጎችን መብት በግልፅ የሚደነግግ በመሆኑና አንቀፅ 41(2) የህንን በሚያጠናክር መልኩ "ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደርያውን፣ ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው" በማለት የሚደነግግ በመሆኑ አንድ ኢትዮጵያዊ/ት በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በመሰማራት ነግደው የመኖር መብት ህገ-መንስታዊ መብታቸው መሆኑን በግልፅ ያስረዳል፡፡

ይህ ህገ-መንግስታዊ መብት ከፍ/ብሄር ህጋችን አንፃር ሲታይም ፍ/ህ/ቁ 16 የመስራት ነፃነትን መሰረት በማድረግ በፍ/ህ/ቁ 16(1) ላይ "ማንም ሰው ሁሉ የሞያ፣ ስራውን ወይም የእረፍት ግዜዎቹን በሚመለከተው ረገድ መልካም ነው ብሎ በገዛ ኣሳቡ የመረጠውን ስራ ለማካሄድ ነፃነት ኣለው፡፡" ሲል በፍ/ብ/ህ/ቁ 16)2) ላይ ደግሞ "ይህንን ነፃነቱን ሊቀንሱበት የሚችሉት ምክንያቶች የሌለውን ሰው መብት፣ መልካም ባህልና ህጎችን የማክበር ግዴታዎች ብቻ ናቸው" በማለት ስለሚደነግግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና ፍ/ብሄር ህግ መካከል አንድነት ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን በንግድ የመተዳደር ህገ መንግስታዊ መብት ከፍታብሄር ህጉ አንፃር ሲታይ በሁለት መንገዶች ማለትም በፈቃደኛነትና(voluntary restrain) በግድ (compulsory restrain) መብቱ ሊገደብ የሚችልበት ሁኔታ አለ ፤፤ በፈቃደኝነት መብትን ለመገደብ የሚቻለው ልክ በፍ/ብ/ቁ 16(3) ላይ እንደተደነገገው "ማንኛውም ሰው ሁሉ ይህን የመስራት ነፃነቱን በመቀነስ አንድ የተወሰነ ስራ ብቻ ለማካሄድ ወይም አንድ ስራ ላለመስራት የገባው የውል ግዴታ ሁሉ ተገቢ ጥቅም መኖሩን ካላረጋገጠ በስተቀር ሊፀናበት ኣይችልም" የሚለውን መሰረት በማድረግ ነው ፤፤ይሄውም አንድ ሰው በህገ-መንግስቱ የተረጋገጠለትን በንግድ የመተዳደር መብቱን በፈቃዱ ሊተው የሚቻለው በን/ህ/ቁ 158 መሰረት የንግድ መደብር በሚሸጥበት ጊዜ ከሸጠበት ቀን አንስቶ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ተመሳሳይ የስራ ዓይነትና በተሸጠው የንግድ ቤት አከባቢ ለገዢው ጉዳት የሚያደርስ የውድድር ስራ መስራትን ስለሚከለክልና ይህን ከተላለፈ በን/ህ/ቁ 131 ተጠያቂ ሲለሚሆን በመብቱ ለመገልገል በን/ህ/ቁ 22 ያለውን ግዴታ ማክበር ስለሚጠበቅበት በህገ-መንግስቱ የተጠበቀለት መብቱን በራሱ ፈቃድ (voluntary restrain) በስምምነት እንዲተዉ የሚገደዱበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ማንኛውም ሰው በፈለገው የንግድ መስክ ተሰማርቶ ንግድን ለማካሄድ እንደሚችል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 41(1) (2) በግልፅ ቢደነግግም በህገ-መንግስቱም ሆነ በሌሎች ህጎች እንደሚታየው እነዚህ መብቶች ያለገደብ የተሰጡ ኣይደሉም፡፡ ለህዝብ ጥቅም ሲባል አንዳንድ መብቶች ሊገደቡ እንደሚችሉ ሁሉ በፈለጉት መስክ በንግድ የመተዳደር መብትም አስገዳጅ ገደቦች (compulsory restraints) ያሉበት ለመሆኑ ከ/ን/ህ/ቁ 11-26 ባሉ ድንጋጌዎች

ገደቦች ተበጅተውለታል፡፡ ለምሳሌ አንድ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም 18 ዓመት ያልሞላው ሰው ፍ/ብ/ህ/ቁ 288 በሚደነግገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር የንግድ ስራን ማካሄድ አይችልም፡፡ ስለዚህ በንግድ የመተዳደር መብት ህገ-መንግስታዊ መብት ነው ቢባልም ያለ ህጋዊ ገደብ የተሰጠ መብት ላለመሆኑ ን/ህ/ቁ 27ን ከፍ/ብ/ህ/ቁ 652 እና 461(ሐ) ጋር በማዛመድ ካየነው ይህ መብት ከህገ- የመነጨ ገደቦች ያሉበት ለመሆኑ መገንዘብ እንችላለን፡፡

የንግድ ህግ፣ የፍታብሄር ህግና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ያላቸውን ግንኙነት እስካሁን ባየነው መልኩ የሚገለፅ ሆኖ የንግድ ህጉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ ከወጣው የከተማና የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ አንፃር ሲታይ ያለው ገፅታስ ምን ይመስላል? ብለን የተመለከትን እንደሆነ እንደሚታወቀው አገራችን የምትከተለው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው የሰው ጉልበትና ጥሬ ሃበት የሚተዳደረው በሽቀጦች ወይም በአገለግሎት ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በከተሞች አከባቢ በሚከናወን የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋሞችና ለካፒታል ቆጣቢ መካከለኛና ታላላቅ ተቋሞች ትኩረት በሚሰጥ የከተማ ልማት ስትራተጅም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን ያለው የንግድ ህግ ሲመረመር አገራችን እየተከተለችው ያለውን ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የተቀረፀና ይህን ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት የማረጋገጥ ጉዞ በሚያግዝ መልኩ የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ በማጎልበት ሂደት ለሚከሰቱ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ አለመግባባቶች ለመፍታት በእጅጉ የሚቸገርና በርካታ ህጎች በተሟላ መልኩ ይዟል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ንግድ ህግ ሲነሳ ቀደም ሲል በኮድ መልክ የወጣውን የ1952 ዓ.ም የንግድ ህግን ብቻ ሳይሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትን መሰረት በማድረግ ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በርካታ ሕጎችንም ጭምር ስለሆነ እነዚህን በሚገባ ተገንዝበን በስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ አገራችን ለተያያዘችው ፈጣንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጡ ሂደት ውጤታማነት እንዲያገላግሉ አበክረን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

## 2. <u>የንግድ መደብር (መድብል)</u>

### 2.1. ስለንግድ መደብር በጠቅላላ

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ "የንግድ መደብር (Business) ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም ከተለመደው አባባል ወጣ ባለ መልኩ ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 124 "የንግድ መደበር (መድብል) የሚባለው አንድ ግዙፍነት የሌለው በን/ህ/ቁ 5 ለተጠቀሱት የንግድ ስራዎች ዓይነት ለሆነው ላንድ ስራ ማካሄጃ የተዘጋጁ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ሁሉ ናቸው፡፡" በማለት ትርጉም መስጠቱ የትርጉሙ ግዙፍነት የሌለው አባባል እንደመልካም ስም፣ የቅጅ መብት፣ የፓተንት መብትን የሚያመላክት ሲሆን ግዙፍነት ያላቸው የሚለው አባባል ደግሞ እንደ ወንበርና ጠረጴዛ የመሳሰሉትን ተንቀሳቃሽ ግዙፍነት ያላቸውን የሚያካትት ነው፡፡ የአማርኛው ቅጅ የንግድ መደብር ሲል እንደ ሱቅ፣ ንግድ የሚካሄድበትን ስፍራና መጋዘንን ያመለክታል፡፡ ከዚህ

ኣባባል ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች ቋሚ የመነገጃ ስፍራ እንደ ሱቅና መጋዘን የሌላቸው ሰዎች የንግድ መደብር (Business) የላቸውም ሊባሉ ይችላሉን? የሚል እና ህጉ የሚንቀሳቀሱ ሲል ግዙፍነት የሌላቸውን ንብረቶች ነው ወይስ ግዙፍነት ያላቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችንም ያጠቃልላል? የሚሉ ናቸው፡፡ በነዚህ ጥያቄዎች ዙርያ የአዘጋጁ አስተያየት የንግድ መደበር (Business) ነው ወይም አይደለም ብሎ ለማለት ጉዳዩ መታየት ያለብት በንብረቶቹ ስብሰብነት ሳይሆን የተሰበሰቡት ለንግድ ስራ ነው ወይስ ኣይደለም ከሚል መነሻ መሆን ይኖርበታል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ግዙፍነት ያለው ይሁን የሌለው የሚንቀሳቀስ ንብረት በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን የንግድ ስራዎች ለማከናወን እስከ ተገለገልንበት ድረስ የንግድ መደብር (Business) ተብሎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

## 2.2. የንግድ መደብር የሚቋቋመባቸው ነገሮች (Elements of Business)

ቀደም ሲል እንዳየነው የንግድ መደብር ግዙፍነት ያለው ወይም ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሊሆን ይችላል፡፡ ግዙፍነት ከሌላቸው መብቶች ጥቂቶቹን ወስደን የተመለከትን እንደሆነ የንግድ መደብር የሚባለው እንደ ደንበኛ የሆኑ ገብያተኞች (good will)፣ የንግድ ስም(trade name)፣ የሚነገድበት የተለየ የንግድ የማስታወቅያ ሰሌዳ፣ የንግድ ስራ የሚከናወንባቸው ቤቶች የማከራየት መብት፣ የቅጅ መብት፣ ፓተንትና የንግድ ምልክት መብትና ሌሎች መብቶችን ያካተተ ሊሆን ይችላል፡፡

### 2.2.1. ደንበኛ ገብያተኛ (Good will)

የደንበኛ ገብያተኛ (good will) ትርጉም ፡-

Lord Eldon የተባሉ ተመራማሪ "The good will …is nothing more than the probability that the old customer will resort to old place. በማለት የተረጎሙት ሲሆን

Lord Machanghten

> *Good will the very sap and life of the business, with out which the business would, yield little or no profit. It is the whole advantage what ever if may be of reputation and connection of firm. This may have been built up by years of honest work or gained by lavish expenditure of money.*

በማለት ተርጉመውታል፡፡ ከነዚህ ትርጓሜዎች መገንዘብ የሚቻለው የአንድ ንግድ መደብር ደንበኛ ገብያተኛ (good will) ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሆኖ በን/ህ/ቁ 130 እንደተገለፀው ደንበኛ ገብያተኛ ለማግኘት በነጋዴውና በሶምስተኛ ወገን መካከል በተፈጠረ መልካም ግኑኝነት የሚመሰረት ነው፡፡ ለዚህም አንድ ፀሃፊ "good 'will is the result of good' operation of the business organization and is extent depends up on good operation, good handling of customers, quality production, trust and confidence of third parties on the given business organization or trader." በማለት ገልፀውታል፡፡

ስለዚህ ደንበኛ ገብያተኛ (good will) እንደሁሉም የሚንቀሳቀሱ ግዙፍነት የሌላቸው መብቶች የህግ ጥበቃ የተሰጠው በመሆኑ መብቱ በሚጣስበት ጊዜ በዚህ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ወገን በፍ/ብሄር ከውል ውጭ በሆነ ሃላፊነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 2057፣ 2059 በወንጀል ደግሞ በወንጀል ህግ ቁጥር 719 በመክሰስ መብትን ማስከበር የሚያስችል የህግ ጥበቃ የተሰጠው መብት ነው፡፡

## 2.2.2. ተገቢ ያልሆነ ውድድር (Unfair competition)

- የንግድ አሰራር ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንፃር ስንመለከተው አዋጅ ቁጥር 329/95 አገራችን ከምትከተለው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራተጂ ጋር በተጣጠመ መልኩና የህገ-መንግስቱን አንቀፅ 89(2) "መንግስት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል እድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት" የሚለውን መሰረት በማድረግ የወጣ ሲሆን ለዚህም በአዋጁ መግብያ ላይ የተጠቀሱትን
    - የንግዱ ስራ አገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሰረት ተገቢውን አሰራር ተከትሎ መካሄድ ስላለበት፤
    - ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትንና ማህበራዊ ደህንነትን ለማስፈን እና በነጋዴው መካከል የሚደረጉትን ፀረ-ውድድር የሆነ ተግባራት በመቆጣጠር ለውድድር አመቺነት ያለው ስርዓት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤
    - መሰረታዊ የሆነ የአንዳንድ የንግድ ዕቃዎች አገልግሎቶች ላይ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ዋጋውን መቆጣጠርና ስርጭቱንም ስርዓት በማስያዝ ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሰራር ለመዘርጋት አልሞ የወጣ አዋጅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

የዚህ አዋጅ ይዘት የነጋዴውን ማህበረሰብ ጥቅምንና የሌላውን የሸማች ማህበረሰብ ጥቅሞች አጣጥሞና ስርዓት ባለው መንገድ ጤናማ የኢኮኖሚ ውድድር በአገሪቱ እንዲሰፍን ሁኔታዎችን በማመቻቸት አገራችን እየተከተለችው ላለው የሰላም የልማትና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የንግዱ ዘርፍ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በማስቻል ህዝብ በየደረጃው የልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ፖሊሲና ስትራተጂን መሰረት በማድረግ እንዲወጣ የተደረገ ህግ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

ተገቢ ያልሆነ ውድድር በንግድ ህጉ ከቁጥር 130-134 ባሉ ድንጋጌዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 2057 ሽፋን ተሰጥቶት የቆዳ ቢሆንም አሁን አገራችን እየተከተለችው ካለው ገበያ ተኮር የልማት ስትራተጂ ጋር የሚጣጣምና የነፃ ገበያ መርህን መሰረት ያደረገ የገበያ ውድድርን የሚመራ የንግድ አሰራር አዋጅ ቁጥር 329/95 ከወጣ ወዲህ ተገቢ ያልሆነ ውድድር በዋናነት መገዛት ያለበት በዚህ አዋጅ ነው፡፡

ወደ አዋጁ ዝርዝር ይዘት ከመግባታችን በፊት ተገቢ ያልሆነ ውድድር ማለት ምን ማለት እንደሆነና ድርጊቱ የሚገለፅባቸውን መንገዶች ስንመለከት አንድ Haines የተባለ ፀሃፊ

> *Unfair competition is use or simulation by one person of names, symbols or devices of a business rival in such a manner as is calculated to deceive and cause the public to trade with the first, when they intend to and would otherwise have traded with the second.*

በማለት የተረጐመው ሲሆን የተገቢ ያልሆነ ውድድር መገለጫዎች ደግሞ፡-

- ሐሰተኛና አሳሳች ወሬዎችን ከዋጋ፣ ምርት፣ ባህሪና የተመረተበት ቦታና አመራረት ማሰራጨት፡፡
- የማስተዋወቅ ስራን ተጠቅሞ የሸቀጦች የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨት፡፡
- የተጭበረበረ የንግድ ምልክት፣ የንግድ ስም፣ የምርት መግለጫ (Product labeling) እና ማሸግያዎችን(packing) መጠቀም፡፡
- የተሳሳተ (የተጭበረበረ) ደረሰኝ ማቅረብ፣ ሚስጢር መበተን ለምሳሌ እንደ ሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ አመራረት፣ የንግድ መረጃ ማቅረብ ያሉ መግለጫዎች ያሉት ነው፡፡

በንግድ ህጉ ያሉ ድንጋጌዎች በግልፅ በአዋጅ ቁጥር 329/95 የተሻሩ ባለመሆናቸው በስራ ላይ ልናውላቸው የምንችል መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአዋጁ ዓላማ በአንቀፅ 3 ላይ ለነፃ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችን ተገቢ ያልሆነ የንግድ ስራዎች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና በማስወገድ ተገቢ የንግድ ውድድር እንዲሰፍን ለማድረግ እና በንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትና ስርጭት ላይ ገደብ የሚፈጥሩ ድርጅቶችን በመከላለልና በማስወገድ የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ጥቅም ማስጠበቅ በመሆኑ በርካታ ከአደረጃጀትና አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚችሉ ድንጋጌዎች ያሉት ቢሆንም አንዳንድ የአዋጁን አንቀፆች ስንዳሰስ የአዋጁ አንቀፅ 6(1) በድብቅ መስማማትን ስለማያካትት የራሱ የሆነ ውሱንነት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፤፤ ለዚህም የአዋጁ አንቀፅ 6(2) በተወሰነ ደረጃ

- ዋጋን በጋራ የመወሰን ስምምነት፣
- የገበያ ዋጋን ለመወሰን በሽርክና ለመጫረት የሚደረግ ስምምነት፣
- ገበያን ወይም ደንበኞችን መመደብ የመከፋፈል ስምምነት፣
- የምርትና ሽያጭ ኮታ ምደባ ስምምነት፣
- ላለመሸጥ፣ አገልግሎት ላለመስጠትና ላለመደራደር በህብረት አቋም መያዝን እንደ ህገ-ወጥ ድርጊት ስለሚወሰድ ድብቅ አሰራርን በተሰነ ደረጃ ያካተተ ቢሆንም ይህ አድራጎት በድብቅ ሲደረግ ነው ወይስ በግልፅ በአደባባይ እንደዚህ ብሎ መቅረብን ነው እንደ ህገ-ወጥ ድርጊት የሚወሰደው? ለሚለው ህጉ እምብዛም ግልፅ መልስ የሚሰጥ አይደለም፡፡

ገበያን በበላይነት አለአግባብ ስለመጠቀም የሚደነግገው አንቀፅ 11 ገበያ በበላይነት ኣለአግባብ መጠቀም ምን ማለት እንደሆነ በትርጉም ክፍሉ ባለመተርጎሙ በአፈፃፀም ላይ ችግር የሚፈጥርና ለትርጉም የተጋለጠ መሆኑ እንደተጠበቀ የአዋጁ አንቀፅ 11(2) (ሀ) እና 11(2) (ቀ) ግራ የሚጋቡ የሚችሉ ናቸው፤፤ አንቀፅ 11(2) (ሀ)

"በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተገቢ ያልሆነና እጅግ የናረ ወይም የወረደ የመሸጫ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ መጠበቅ ወይም አቅርቦትን መገደብ ወይም ሌላውን ከንግድ ስራ ለማገድና ላለማስገባት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ስራ መስራት" ሲል አንቀፅ 11(2) (ቀ) ደግሞ 'ተገቢ ውድድር እንዳይኖር ለማድረግየማምረቻ ወጪን በማይሸፍን ዋጋ መሸጥ፤፤" ይላል፡፡

የነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት ገበያን በበላይነት አለአግባብ ስለመጠቀም (abuse of dominance) ሳይሆን የሚናገሩት አንዱ ሌላውን ስለመዋጥ (Predatory pricing) የሚናገሩ በመሆናቸው ግልፅነት ይጎድላቸዋል፡፡

ሌላው የአዋጁ ይዘት ችግር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው ያላግባብ ከመወዳደር ውጭ ስለሆነ ሁኔታ የሚደነግገው ነው፡፡

አንቀፅ 10(2) (ሽ)

> በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱትን ዕቃዎች ለማጥፋት ወይም ለመጉዳት ወይም በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ያለውን ማንኛውንም የንግድ ክፍል ለመገደብ ወይም በምኖፓል ለመያዝ በማሰብ የነዚህ ዓይነት እቃዎች በተሰሩበት ኣገር ዋና ገበያዎች ከሚሸጡበት የገበያ ዋጋ ወይም የጅምላ ዋጋ ባነሰ ዋጋ ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት፡፡

የሚለው የህጉ ሃይለ ቃልና ይዘት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስለመወዳደር (Unfair competition) ዙርያ የሚያጠነጥን ሳይሆን ምርትን ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ስለማስገባት (damping) ላይ በመሆኑ ለአፈፃፀም የሚያስቸግር ይዘት ያለው ድንጋጌ ነው፡፡

የአዋጁ አንቀፅ 20 እና 21 ስለዕቃዎች ዋጋ ማመላከትና ስለ የንግድ ዕቃዎች መግለጫ (Labels of goods) የሚደነግጉ በመሆናቸው ይዘታቸው ያላግባብ ከመወዳደር ጋር የሚሄድ ብቻ ኣይደለም፡፡ የአዋጁ ይዘት ሁለት ገፅታዎች እንዲኖሩትና ከውድድር ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ከውድድር ጋር ተያያዝነት የሌላቸው (non-competition issues) ለመለየት በሚያስቸግር መልኩ የተቀረፀ በመሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ ክርክር ሲነሳ መንስኤውንና የክርክሩን ይዘት ለይቶ በማውጣት ህጉ 'commercial competition issue' ላይ ብቻ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ከነዚህ እጥረቶቸ በመለስ ሌላው እንደ ጥንቻሬ የሚታየው ግን በአዋጁ የተደነገጉትን ህጎች መጣስ ሁለት ዓይነት እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ መሆኑ ነው፤፤

1. አስተዳደራዊ እርምጃ በአንቀፅ 25 መሰረት

- ኣቤቱታ የቀረበበትን ድርጊት እንዲታገድ፣ እንዲስተካከል ወይም ጨርሶ እንዲቋረጥ ማድረግ፡-
- የንግድ ፍቃዱን ማገድ ወይም ጨርሶ መሰረዝ
- የተጎጂውን የመወዳደር አቅም በነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ተገቢ እርምጃ መውሰድ
- የዋጋ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ዕቃዎች በሆኑ ጊዜ ዕቃዎቹ እንዲያዙና እንዲሸጡ በማድረግ ከሽያጭ በተገኘው ገቢ ላይ ለሽያጩ ሂደት የወጣውን ወጪ ተቀናሽ ሆኖ ቀሪው ለባለቤቱ እንዲመለስለት ማድረግ ሲሆኑ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ባለቤቱ ወለድ ወይም ሌሎች ክፍያዎችን መጠየቅ የማይችልበት አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ይቻላል፡፡

2. በአዋጁ አንቀፅ 27 በተደነገገው መሰረት የቅጣት ኣወሳሰን ስርዓትን ተከትሎ በአንቀፅ 26 መሰረት የቅጣት ውሳኔ መስጠት ሲሆን በዚህም መሰረት የሚሰጠው ቅጣት
   - በአማራጭ የአጥፊውን ጠቅላላ ንብረት ዋጋ እስከ አስር በመቶ ወይም የአጥፊውን ዓመታዊ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ እስከ አስራ አምስት በመቶ ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጫ፣
   - በተከለከለው ማንኛውም ተግባር ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የማንኛውም ግለሰብ ተባባሪነት መኖር ከተረጋገጠ ጥፋት ባደረገው ሰው ላይ ከብር 5,000.00 (አምስት ሺ) እስከ 50,000.00 (ሃምሳ ሺ) ብር ሊደርስ በሚችል የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ ያልተገባ ውድድር ግለሰብንም ሆነ የአገር ኢኮኖሚ ልማት ፀር በመሆኑ ይህንን ህግ በስራ ላይ በምናውልበት ጊዜ የግለሰብ ኪስ በማደለብ የአገሪቱን ልማት ከሚገድል ስግብግ ነጋዴ ህዝቡንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሚታደግና ልማታዊ ባለሃብቱን በሚያጠናክር መንገድ መሆን እንዳለበት ልንገነዘብ ይገባል፡፡

## 2.2. 3 የአእምሮ ንብረትና ህገ መንግስቱ

የአእምሮ ንብረት ከድሮ ጀምሮ ሮማውያን የግለሰብ መብት (personal right) እና ግዙፍ መብት (real right) በሚል ከሚመድቧቸው የንብረት መብቶች በተጨማሪ ለየት ያለ መብት ሲሆን ስያሜውን በተመለከተ የተለያዩ ፀሐፍት የተለያየ አጠራር ሲጠቀሙ ይስተዋላል:: ለዚህም አንዳንዶቹ ግዙፍነት የሌለው መብት (incorporeal right) ሌሎቹ ደግሞ የአእምሮ ንብረት (intellectual property) በማለት ይጠሩታል:: ይህ አጠራር ምንነቱን የሚቀይር ባለመሆኑ በይዘቱ አንድ ነው :: የአእምሮ ንብረት መብት ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሲሆን አገሮች ይህን የንብረት መብት ከሚከተሉት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲ በመነሳት በህገ-መንግስታቸውና ከዚያ በታች ባሉ ህጎቻቸው ጥበቃ በመሰጠት በልማት መሳርያነት ሲገለገሉበት የሚገኝ የንብረት መብት ነው፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ለአእምሮ ንብረት

የተሰጠው የህግ ማእቀፍ ስንመለከት በአንቀፅ 51(19) ላይ "የፈጠራና የድርሰት መብቶችን ይፈቅዳል፣ ይጠብቃል" ሲል መንግስት ለአእምሮ ንብረት መብት መከበር የሚኖረውን ሃላፊነት መሰረት በማድረግ ሲደነግግ በአንቀፅ77(5) ላይ ደግሞ "የፈጠራና የኪነጥበብ መብቶችን ያስጠብቃል" በማለት ይደነግግል፡፡ ከነዚህ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በአገራችን ኪነ ጥበብ፣ ድርሰትና የቴክኖሎጂ እድገት ከፍ እንዲል በማድረግ ዜጐች በአገሪቱ ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥና እድገት ላይ ያላቸውን ሚና ከወትሮው በተሻለ መንገድ እንዲጫወቱ በማስቻል በሰፊው የልማት ተሳታፊና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ የማድረግ ዓላማ ያለው መሆኑ ነው፡፡

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የህገ-መንግስት ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የአእምሮ ንብረት መብት በፈጠራ (patent) እና በኪነ-ጥበብ ስራ ወይም ድርሰት (copy right) ብቻ የታጠረ የንብረት መብት ነውን? የሚል ሲሆን የአእምሮ ንብረት መብት ከፈጠራ መብት (patent) እና የድርሰትና ወይም የኪነ ጥበብ ንብረት መብት(copy right) በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ንድፍ (Industrial design)፣ የንግድ ምልክትና (Trade marks)፣ የእፅዋት አዳቃዮች መብት(plant breeders right) እና ሌሎች በርካታ መብቶችን የሚያካትት በመሆኑ የህገ-መንግስቱ ህጋዊ ሽፋን ጠበብ ያለ ነው ብሎ መረዳት የሚቻል ቢሆንም የነዚህ መብቶች ጥበቃ ከህገ-መንግስቱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች በመነጩ ሌሎች ህጐች የህግ ሽፋንና የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብቶች ጥበቃ የተደረገላቸው በመሆኑ የዜጐች መብቶች ለአደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ በአገሪቱ የፍትህ ስርዓት የለም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ መንግስትም በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 89(1) መሰረት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሃገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበት መንገድ የመቀየስ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ይህን ህገ-መንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ አዋጆችን አውጥቶ ከማንኛውም ግዜ በበለጠ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚሰጥ አሰራርና አደረጃጀት ዘርግቶ ለዘላቂ ልማት ስትራተጂ ስኬትና በዚ መስክ ሊገኝ የሚችለውን እድገት ለማስመዝገብ ከፍተኛ ስራ በመስራት ላይ ነው፡፡ ይህ መብት በተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት በተሰጣቸው የንግድ መደብሮች ሊያዝ የሚችል መብት ስለመሆኑ በንግድ ህጉና ሌሎች አዋጆች ተደንግጎ የምናገኘው ነው፤፤ በመሆኑም የአእምሮ ንብረት መብት መረጋገጥና አለመረጋገጥ በአንድ አገር ማህበረ-ኢኮኖሚና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያለው ፋይዳን መሰረት በማድረግ የህግ ሽፋን የሚሰጠው የንብረት መብት እንደመሆኑ መጠን በፍትህ አካላት ዘንድም በየጊዜው የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች በአግባቡ ለማስተናገድ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 13(1) የተጣለባቸውን ህገ-መንግስቱን የማክበር እና የማስከበር ግዴታቸውን ሊወጡ የሚያስችል ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 2.2.4 የፈጠራ ስራ (patent)

ቀደም ሲል በን/ህ/ቁ 127(መ) የህግ ሽፋን ተሰጥቶት የነበራው የፈጠራ ስራ አሁን ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በወጣው አዋጅም እውቅና የተሰጠው ነው፤፤ የአእምሮ ንብረት ጥበቃ ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራ ለማስቻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 123/1987 በአንቀፅ 2(5) ላይ "ፓተንት ማለት የፈጣ ስራን ለማስጠበቅ የሚሰጥ መብት ሲሆን የፈጠራ ስራውን ከአንድ ምርት ወይም የምርት ሂደት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡" በማለት ሲተረጉመው በአንቀፅ 2(3) ላይ ደግሞ " ፈጠራ ማለት በቴክኖሎጂ መስክ ለአንድ የተወሰነ ችግር ተግባራዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የፈጠራ ሰራተኛ ሃሳብ ነው " በማለት የፈጠራን ምንነት ይገልፃል፡፡

እውቁ Wikipedia, the free encyclopedia በድረ ገፁ ላይ የፈጠራ ስራን (patent) እምብዛም በአዋጁ ከተሰጠው ትርጉም ባልተለየ መልኩ እንዲህ ሲል ተረጉሞታል፡፡

> *The term patent usually refers to a right granted to any one who invents or discovers process, machine, article of manufacture, or composition of matters, or any new and useful improvement there of.*

ከነዚህ የተቀራረቡ ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው የፈጠራ መብት (patent right) የሚመነጨው አንድ ሰው በአእምሮው ከሚፈጥረው አዲስና ጠቃሚ ምርት ወይም ግኝትና አዲስ ባይሆንም በሌላ ሰው ፈጠራ ተሰርቶ በስራ ላይ የቆየን ነገር በማሻሻል የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችለው ተጨማሪ የፈጠራ ስራ በማከልና በማሻሻል እንደሆነ ነው፡፡ የአዋጁ ተፈፃሚነት ለንግድ መደብርም እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 2(7) " ሰው' ማለት የተፈጥሮ ሰውወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው" ከሚለው መረዳት ስለሚቻል የፈጠራ ስራ እንደ አንድ የንግድ መደብር ግዙፍነት የሌለው መብት በዚህ ፅሁፍ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፤፤ በመርህ ደረጃ የፈጠራ መብት አዲስ በመፍጠር ወይም ያለውን በማሻሻል ሊገኝ የሚችል የአእምሮ ንብረት መብት እንደሆነ መገንዘብ ቢቻልም የአገራችንን ህግ በምናይበት ጊዜ ግን የዚህ ዓይነት መብት የሚሰጠው በአዋጁ አንቀፅ 40(1) መሰረት ለአገልግሎት ሞዴል (ለአነስተኛ የፈጠራ ስራ) ካልሆነ በስተቀር በፓተንት መብትነት አንድን ቀደም ሲል የነበረን የፈጠራ ስራ አሻሽሎ በመስራት የአእምሮ ንብረት መብት ማግኘት እንደሚቻል የሚደነግግ አይደለም፡፡ የዚህ ዓይነት ልዩነት በብዙ አገሮች ህግም ያለ ነው:: ለምሳሌ በአሜሪካ የፓተንት ህግ አንድን ሰው ፈጠራ አሻሽሎ መስራት እንደ መብት ጥሰት ተወስዶ የፍ/ብሄር ተጠያቂነትን የሚስከትል ሲሆን በአውስትራልያ ህግ ተጨማሪ የፈጠራ ስራ መስራት ማለትም አሻሽሎ ማውጣት የተፈቀደ ነው::

በአገራችን የፈጠራ ስራን ለማስጠበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 123/87 አላማዎችን ስንመለከት የፈጠራ ስራ አእምራዊ ንብረት መብት የአንድን ሰው በፈጠራው ስራ መገልገልን (Use or practice) መብት የሚጐናፀፍ በመሆኑ በዋና አላማነት ይዞት የሚነሳው ሌሎችን ያለ ባለመብቱ ፈቃድ እንዳይገለገሉበት መከልከል (excluding others) ነው:: ከዚህ በተጨማሪ

1. ለአገር ውስጥ ፈጣሪዎች (local inventors) ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የአገሪቱን የቴክኖሎጂ እድገት በማፋጠን የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲንና ስትራተጂን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ስራን የመስራት ዓላማ ያለው ነው ፡፡
2. ከአገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች በተጨማሪ ከውጪው ዓለም የቴክሎጂ ሽግግር እንዲኖር የሚያስችል ምቹ ሁኔታን በመፍጠር አገሪቱ ከዚህ ተጠቃሚ እንድትሆን በማድረግ ዘርፉ ለሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ስኬት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት የማስቻል አላማን በመያዝ የወጣ ህግ ለመሆኑ ከአዋጁ መግብያና ከዝርዝር ህጐቹ መረዳት እንችላለን፡፡ በመሆኑም የአገር ውስጥ ፈጠራን በዋና የልማት መሳርያነት በመጠቀም ከውጪው ዓለም መውሰድ ያለብንን ልምድ መበውሰድ ጠንካራ፣ ዘላቂና ተወዳዳሪ ኢኮኖሚን መገንባት መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ እድገት ማረጋገዋን እንደግብ የያዘ ነው፡፡ የፓተንት መብት መጠበቅ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን ስናይ አገሮች የፓተንት መብት እንዲጠበቅ የሚያደርጉባቸው ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን ወሰደን ያየን እንደሆነ:-
   - ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ከዚህ ተጠቃሚ ለመሆን፤
   - መብቱ በመጠበቁ ሰዎች ፈጠራቸውን እንዲያወጡና ህዝቡ ከዚህ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል፤
   - ተመራማሪዎች ወደ ውድድር እንዲገቡና ኩባንያዎች ከዚህ የፈጠራ ስራ ውድድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻልና በቀላል ዋጋ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ፤
   - ኩባንያዎች የፈጠራ ስራውን ገዝተው ማምረት ሲጀምሩ በሌላ የሚፈበረክ ከሆነ አደጋ ላይ ሊጥላቸውና ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ ሊከታቸው ስለሚችል የፓተንት ህግ ከሌለ ደፍረው የፈጠራ ስራን ሊገዙ ስለማይችሉ የህጉ መኖር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: ስለዚህ በአንድ አገር የፈጠራ ህግ ሲወጣ የራሱ አላማዎችና ምክንያቶች ያሉት እንደመሆኑ መጠን በኛ አገርም ከፍ ብለው የተገለፁት አላማዎች ያሉት ነው::

## 2.2.4.1 ጥበቃ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው የፈጠራ ስራዎች

የፈጠራ ስራ መብት (patent right) የሚሰጠው እንዴት ላለ ፈጠራ ነው? የሚለውን ስንመለከት ይህ መብት ለሁሉም እንደማይሰጥ አዋጁ በአንቀፅ 3 ላይ በዝርዝርና ለይቶ የሚያሳይ መልኩ የደነገገውን ወስደን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ አንድ የፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ እንዲያገኝ ከተፈለገ ቀጥሎ ያሉትን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል::

1. *አዲስነት (Novelty) - አንድ የፈጠራ ስራ አዲስ ነው የሚባለው በቀደምት ጥበብ ያልተሸፈነ ሲሆን ነው፡፡ ቀደምት ጥበብ ማለት የፈጠራ ስራውን በተመለከተ ማመልከቻ ከገባበት ወይም እንደአግባቡ ከቀዳሚው ቀን በፊት በየትኛውም የአለም ክፍል በተጨባጭ በሚታይ ህትመት ወይም በቃል ወይም ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ የተገለፀ ነገርን ያጠቃልላል (አንቀፅ 3(2))*
2. *ፈጠራዊ ብቃት (Inventive Step) - አንድ የፈጠራ ስራ ፈጠራዊ ብቃት አለው የሚባለው ከሚመለከታቸው ጋር አግባብነት ካለው ቀደምት ጥበብ አንፃር ሲታይ በመስኩ ተራ እውቀት ላለው ሰው ግልፅ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡ (አንቀፅ 3(4))*
3. *ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት(Industrial Applicability) - አንድ የፈጠራ ስራ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት አለው የሚባለው በዕደ ጥበብ፣ በግብርና፣ በማህበራዊ አገልግሎቶችና ሌላ ማናቸውም መስክ ሊሰራ ወይም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው (አንቀፅ 3(5))*

በመሆኑም አንድ የፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ አግኝቶ ፈጣሪ ነኝ የሚለው ሰውም በመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ስራው እነዚህን ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ህጋዊ መስፈርቶች (legal requirements) ማሟላት የግድ ይላል፡፡

የፈጠራ ስራ ጥበቃ የማይደርግላቸው ስራዎች በአዋጁ አንቀፅ 4 ላይ ተዘርዝረው ያሉት ሲሆኑ እነሱም፤

- የህዝቡን ሰላም ወይም ስነ-ምግባር የሚፃረሩ ፈጠራዎች፤
- የእፅዋት ወይም የእንስሳት ዓይነቶች ወይም የእፅዋት ወይም የእንስሳት ውጤቶችን ለማስገኘት በስነ-ህይወት ዘርፍ የሚከናወኑ ስራዎች፤
- ጨዋታዎችን ለማካሄድ ወይም የንግድና የኢንዱስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተዘጋጁ ስልቶች፣ ደንቦች፣ ዜዴዎች እንዲሁም የኮምፒዩተር ፕሮግራም፤
- ግኝቶች፣ ሳይንሳዊ ቲዎሪዎች (theories) እና የቅመራ ዘዴዎች፤ (mathematical methods)
- ሰውን ወይም እንስሳትን በቀዶ ጥገና ወይም በቴራፒ ህክምና ዘዴዎች ለማከም እንዲሁም የሰዎችን ወይም እንስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎች የፈጠራ መብት ጥበቃ የማይሰጣቸው ክንዋኔዎች ተደርገው ነው የሚወሰዱት፡፡ ይህ ማለት ግን የሰዎችን ወይም የእስሳትን በሽታ ለመመርመር የሚረዱ ዘዴዎችን በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያገለግሉ ውጤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ (አንቀፅ 4(2) ስለዚህ ህጉ ለፈጠራ ስራ የህግ ጥበቃ ለመስጠትም ላለመስጠትም በመለክያነት የሚገለገለው የፈጠራ ስራው የህዝብን

ጥቅም ያስጠብቃል ወይስ አያስጠብቅም? በግል የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት ሊያዝ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን መስፈርቶች የሚጠቀም ነው::

### 2.2.4.2 የፈጠራ ስራ መብትና ይዘት

የፓተንቱ ይዘት ባለቤቱ በፈጠራው ላይ ያለውን ብቸኛ መብት የሚያረጋግጥና ሌሎች በደንብ ቁጥር 12/89 አንቀፅ 14 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ መሆን አለበት፡፡ (የአዋጁ አንቀፅ 15) አንድን የፈጠራ ስራ የስራ የፓተንት ባለ መብት የተሰጠውን ፈጠራ ለመፈብረክ ወይም በሱ ለመገልገል ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ለመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡ ሶስተኛ ወገኖችን የባለ ፓተንቱ ፈቃድ ሳያገኙ ፓተንት በተሰጠው ፈጠራ ለመፈብረክ አይችሉም፡፡ ሶስተኛ ወገኖች ተጠያቂ ሊሆኑ የማይችሉት የፓተንት መብት (patent right) ለፈጣሪው የተሰጠው ከሆነ ብቻ ነው፡፡ (አንቀፅ 22(1) እና 23) ይህ ሰው ያለእርሱ ፈቃድ ፓተንቱን የሚፃረር ወይም መብቱን ሊነካ የሚችል ድርጊትን በሚፈፅም ማናቸውም ሰው ላይ በፍ/ቤት ክስ የመመስረት መብት አለው:: መብቱ ያልተረጋገጠለት ሰው የኔ ፈጠራ ስራ ነው በሚል ብቻ ግን በሶስተኛ ወገኖች ላይ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ የፈጠራው ባለቤት የፓተንት መብት የማግኘትና በሶስተኛ ወገኖች ሊመጣ ከሚችል መጣስ ህጋዊ ጥበቃ እንደሚደረግለት ሁሉ ግዴታም ያለበት ነው:: ይሄውም ባለፓተንቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጠራውን ስራ ላይ የማዋል ወይም በርሱ ፈቃድ ሌሎች ሰዎች ፈጠራውን ስራ ላይ እንዲያውሉ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ (አንቀፅ 27)

የፓተንት መብት የሚሰጠው እንዴት ነው? የሚለውን አንስተን ስናይ በመርህ ድረጃ መብቱ የሚሰጠው ለፈጠራ ሰራተኛው ሲሆን የፈጠራ ስራው በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በጋራ ሆነው አንድን የፈጠራ ስራ ካከናወኑ የጋራ የፓተንት መብት ይኖራቸዋል፡፡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ተመሳሳይ የፈጠራ ስራ ስርቻለሁ በማለት በሚቀርቡበት ጊዜ የፈጠራው ባለቤት የሚሆነው አስቀድሞ ማመልከቻ ያስገባው ነው:: (አንቀፅ 11(1) ) ይሄውም ህጉ (first to file rule and right of priority) በመርህ ደረጃ የሚከተል ነው:: ፓተንት የሚሰጠውም በአዋጁ አንቀፅ 14 መሰረት ኮሚሽኑ ፓተንት ስለመስጠቱ በኦፊሴል ጋዜጣ በማሳወቅ ፤ የፓተንቱን ሰርትፍኬትና የፓተንቱን ቅጂ ለአመልካቹ በመስጠት፤ በመመዝገብና ክፍያ ለሚያስፈፅም አካል የፓተንቱን ቅጂ በመስጠት ነው:: የፓተንቱ ይዘትም ባለፓተንቱ በፈጠራው ላይ ያለውን ብቸኛ መብት የሚያረጋግጥና በደንቡ መሰረት ሌሎች ነገሮችን ያካተተ ይሆናል::(አንቀፅ 15 ) በኢትዮጵያ የፓተንት መብት የሚሰጠው ለተፈጥሮና የህግ ሰው ሲሆን በአሜሪካ አገር የዚህ ዓይነት መብት የሚሰጠው ለተፈጥሮ ሰው ብቻ ነው:: በኛ አገር የፈቃድ አሰጣጥ ስነ-ስርዓቱ ምን ይመስላል? የሚለውን ስንመለከት ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር አንድ ሰው ተቀጥሮ በሚሰራበት ግዜ ለሚገኘው የፈጠራ ስራ የፓተንት መብቱ የሚሰጠው ለቀጣሪው ነው:: የቅጥሩ ሁኔታ ከፈጠራ ስራው ግንኙነት የሌላው ወይም ከቅጥር ወይም የአገልግሎት ውል ጋር ግንኙነት በሌለው መንገድና የቀጣሪው ወይም የአሰሪውን

ሃብት፣ መረጃ፣ ማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ ማተሪያል ወይም መሳርያ ሳይጠቀም የፈጠራ ስራውን ያከናወነው ከሆነ ግን የፓተንት መብቱ የሚሰጠው ለፈጣሪው ወይም ለተቀጣሪው ወይም ለአገልግሎት ሰጪው ነው፡፡ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው የቀጣሪውን መሳርያ በመጠቀምና የተቀጣሪው የግል አስተዋፅኦ ታክሎበት ለሚገኝ የፈጠራ ስራ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለው በስተቀር እኩል ድርሻን መሰረት በማድረግ የሁለቱ ማለትም የቀጣሪውና የተቀጣሪው የጋራ ንብረት ይሆንና የፓተንት መብቱ በጋራ ይሰጣል፡፡ (አንቀፅ 7) ስለዚህ የፈጠራ ስራ ባለቤትነት ይዘቱ የፈጠራውን ብቸኛ ባለመብትነት የሚያረጋግጥ ሰነድ ሲሆን የዚህም ውጤት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው በማድረግ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት ጥበቃ እንዲያገኝ ማስቻል ነው፡፡ የፈጠራ ስራ ባለቤትነት መብት (patent right) የሚሰጠው አንድም ለፈጣሪው ለራሱ ወይም ይህን ስራ እንዲያከናውን የተቀጠረ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በሆነበት ግዜ ደግሞ ፓተንቱ የሚሰጠው ለቀጣሪው መሆኑንና ተቃራኒ ስምምነት ከሌለና ለፈጠራ ስራው የሁለቱም አስተዋፅኦ ካለበት ደግሞ ፓተንቱ የሚሰጠው ለሁለቱም በጋራ ባለቤትነት እንዲያገግል በሚያስችል መንገድ ይሆናል፡፡

### 2.2.4.3 የባለፓተንት መብት ገደቦች

የፓተንት መብት የአእምሮ ንብረት መብት እንደመሆኑ መጠን የፈጠራ ስራው ባለቤት በዚህ መብቱ ብቸኛ ባለቤት በመሆን ሶስተኛ ወገኖች ያለሱ ፈቃድ በዚህ የፈጠራ ስራ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የመከልከል ውጤት ያለው መብት (negative right) ነው:: ሆኖም ግን ይህ መብት በህግ ገደብ (limitation) የማይደረግበት የንብረት መብት (monopoly right) ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ በመሆኑም በአዋጁ አንቀፅ 25 ላይ የተወሰኑ ገደቦች ተጥሎበታል:: እነዚህም፡-

ሀ. ንግድ ነክ ባልሆኑ ተግባሮች ያለፈጣሪው ፈቃድ ቢገለገሉበት በህግ አያስጠይቅም፡፡

ለ. ፓተንት የተሰጠበት ፈጠራ ለሳይንሳዊ ምርምርና ሙከራዎች ዓላማ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ማድረግ የተፈቀደ ነው ፡፡

ሐ. በባለፓተንቱ ወይም በሱ ፈቃድ ኢትዮጵያ ውስጥ በገበያ ላይ ከዋሉ ፓተንት የተሰጣቸው ሸቀጦች ጋር በተያያዘ መልክ የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው::

እንዲሁም በአንቀፅ 25(2) ላይ

> *የህዝብን ጥቅም በተለይም የብሄራዊ ደህንነት፣ የምግብና የጤና ወይም የሌሎች ብሄራዊ የኢኮኖሚ ዋና ዘርፎች የልማት ፍላጐት ለመጠቀም ኮሚሽኑ ያለባለፓተንቱ ፈቃድ የመንግስት ድርጅት ወይም ኮሚሽኑ የሚሰይመው ሶስተኛ ወገን ለባለፓተንቱ ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ፈጠራውን እንዲጠቀም ሊወሰን ይችላል፡፡ የካሳ ክፍያውን በሚመለከት ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ወደ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልበት ይችላል::*

ሲል ይደነግጋል፡፡ የነዚህ ድንጋጌዎች አላማ በህገ-መንግስቱ እውቅና የተሰጠውን የፈጠራ ጥበቃ በመርህ ደረጃ የባለቤትነት መብቱ የፈጣሪው ሰው የራሱ ወይም ከአንድ በላይ በሚሆኑበት ግዜ የጋራ እንደሆነ በመቀበል ለህዝብ ጥቅምና አገር ደህንነት ሲባል ግን በዚህ የአእምሮ ንብረት መብት ላይ ገደብ (Limitation) ሊጣልበት እንደሚችልና ይህም በሚሆንበት ግዜ ባለፓተንቱ ካሳ የማግኘት መብት እንዳለው ማረጋገጥ ነው፡፡

## 2.2.4.4 የፓተንት መቋረጥ፣ መተውና መሰረዝ

የፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ ጥበቃ ለማግኘት የቀረበው ማመልከቻ ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለአስራ አምስት ዓመታት ቢሆንም በተለያየ ምክንያት የመብቱ መቋረጥ፣ መተው፣ መሰረዝ ሊከሰት ይችላል፡፡ የፓተንት መብት ሊቋረጥ የሚችለው ባለመብቱ ፓተንቱን የተወ መሆኑን ለኮሚሽኑ በፅሑፍ ሲያሳውቅና የመብት ማቆያ ክፍያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ውስጥ ያልተፈፀመ ሲሆን ነው፡፡ይሄውም የመብቱ መቋረጥ ሊከሰት የሚችለው በፍላጐትና ግዴታን በአግባቡ ባለመፈፀም ምክንያት እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ የፓተንት መብት መተው ሊከሰት የሚችለው ደግሞ በፍላጐት ላይ ተመስርቶ የሚመጣ ሲሆን የክንውኑ ስነ-ስርዓትም ባለፓተንቱ መብቱን መተውን ለኮሚሽኑ ሲያሳውቅና ኮሚሽኑ ይህን የመተው ሁኔታ በመመዝገብ አትሞ ሲያወጣው ነው፡፡ ባለፓተንቱ መብቱን ትቻለሁ ያለበት ጊዜ መብቱ ለሌላ ሶስተኛ ወገን በውል ከተሰጠ በኃላ ከሆነ የሚኖረው ስነ-ስርዓት የመተው ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው ሌላው ተዋዋይ ወገን ስምምነቱን ሲሰጥ ብቻ ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት መብቱ በውል የተላለፈለት ሰው ጥቅም (third party interest) ለመጠበቅ እንደሆነ መገመት ቢቻልም ይሁንታ በማይሰጥበት ጊዜ ስለሚኖረው ስነ-ስርዓት ህጉ በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ ከአጠቃላይ የድንጋጌው ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ግን ይህ መብት ፀንቶ ለሚቆይበት ግዜ በውል የፓተንት መብት የተላለፈለት ሰው በፓተንቱ እየተገለገለበት ሊቆይ እንደሚችል ነው፡፡ የፓተንት መብትን መሰረዝ የሚመለከትም ቀጥለው የምናያቸው መስፈርቶች በሙሉ ወይም በከፊል ከተሟሉ ፍ/ቤት ፓተንቱን ሊሰርዘው ይችላል፡፡ (አንቀፅ 34፣35 እና 36) ይሄውም

ሀ. ፓተንት የተጠየቀበት ነገር በአዋጁ ቁጥር 123/89 አንቀፅ 3 እና 4 መሰረት ፓተንት ሊሰጥበት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፡፡

ለ. ፈጣሪው በሚበቃ መጠን ግልፅና ሙሉ በሆነ መልክ ባለመገለፁ በመስኩ ለሰለጠነ ሰው በተግባር ለመተርጐም የማያስችል ሲሆን ነው ፡፡

ፓተንቱ ሲሰረዝ የዚህ የፓተንት መብት መሰረዝ ህጋዊ ውጤትም ወደ ኃላ ተመልሶ በሚሰራ ውጤት (retroactive effect) ይኖረዋል፡፡ ለዚህም ነው አንቀፅ 37(2) "በከፊል ወይም በሙሉ

የተሰረዘ ፓተንት ዋጋ ቢስ ሆኖ የሚቆጠረው ፓተንቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይሆናል" ሲል የሚደነግገው፡፡

ስለዚህ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ የፓተንት መብት ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ፈጠራ ስራ ባለቤቶች የሚሰጥ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት ሆኖ ህገ-መንግስታዊና ከዚያ በታች ባሉ አዋጆችና ደንቦች ጥበቃ የተደረገለትና ወደ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችል ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ነው፡፡ የፓተንት መብት ጥበቃ የሚያገኘው ለ15 ዓመት ሆኖ የዚህ መብት ዋናው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም ሶስተኛ ወገኖች ያለባለፓተንቱ ፈቃድ እንዳይገለገልበት መከልከል ነው፡፡ ፓተንት ግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ቢሆንም በአንድ ወቅት ተፈጥሮ ለ15 ዓመት ህጋዊ ውጤት ኖሮት ማንነቱን ሊያጣ ወይም ቀሪ ሊሆን የሚችል ወይም በመሃል እክል ገጥሞት ሊሰረዝ ወይም ሊቋረጥ ወይም በነፃ ፈቃድ ሊተው የሚችል የአእምሮ ንብረት መብትም ነው፡፡

### 2.2.4.5 የአስጋቢ ፓተንት (patent of introduction)

የአስገቢ ፓተንት የሚሰጠው ለማን ነው? የአስገቢ ፓተንት የሚሰጠው በውጭ አገር የፓተንት ፈቃድ ለተሰጠውና የጥብቃ ጊዜው ላላለፈበት እንዲሁም በኢትዮጵያ ፓተንት ላልተሰጠው የፈጠራ ስራ መግለጫ ለሰጠና ሙሉ ሓላፊነት ለሚወስድ ማንኛውም የአስገቢ ፓተንት ሊሰጠው ይችላል:: (አንቀፅ 18) የአስገቢ ፓተንት መመዘኛዎችም ለፈጠራ ፓተንት ከሚጠይቁት መመዘኛዎች ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የአስገቢ ፓተንት መሰረቱ የውጭ ፓተንት እንደመሆኑ መጠን የአስገቢ ፓተንት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚያመለክት ሰው የውጭውን ፓተንት ቁጥር፣ ቀንና ምንጭ ወይም ዝርዝር መረጃውን የማያውቅ ከሆነ የሚገኝበትን ምንጭ መጠቆም ይኖርበታል፡፡ (አንቀፅ 19(1) (2)

የአዋጁ አንቀፅ 11(2) የእንካ ለእንካ መርህ (principle of reprocity) እንደተጠበቀ ሆኖ የአስገቢ ፓተንት አመልካች በአንቀፅ 11(2) የተጠቀሰው አንድ ዓመት ግዜ ከማለቁ በፊት የውጭው ፓተንት ባለቤት ማመልከቻ ካላቀረበ ወይም የአስገቢ ፓተንት ባለቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 21 ማለትም የአስገቢው ፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ መሰረት ፈጠራው ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ካልቻለ ወይም ዓመታዊውን ክፍያ መፈፀም ካልቻለ የአስገቢ ፓተንቱ ዋጋ ቢስ ወይም ህጋዊ ውጤት የሌለው እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ (አንቀፅ 20(1)) ይሄም በሚመለከተው አካል ጠያቂነት የአስገቢ ፓተንት መብቱ በአዋጁ አንቀፅ 36 መሰረት በፍ/ቤት የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

የአስገቢ ፓተንት መብት ፀንቶ የሚቆየው የአስገቢ ፓተንት ከተሰጠ ከሶስት ዓመት በኃላ በየዓመቱ በስራ ላይ የዋለ መሆኑ የማረጋገጥ ግዴታና ዓመታዊ ክፍያ የመክፈል ግዴታው እንደተጠበቀ ሆኖ የአስገቢ ፓተንቱ ፀንቶ የሚቆየው እስከ አስር ዓመት ሊደርስ ይችላል፡፡ (አንቀፅ 21) የዚህ ዓይነት የፓተንት መብት መፍቀድ አላማው የውጭ ፓተንት የተሰጠን ፈጠራ ስራ በኢትዮጵያ እንዲገባ በመፍቀድ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖርና ከዚህ ዘርፍ

ልናገኝ የምንችለውን ጥቅም አሟጦ በመጠቀም ለልማት በማዋል በዘርፉ የአሰራር፣ አደረጃጀትና የሰው ሃይል ብቃት እንዲጨምር ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ወሳኙ የአገር ውስጥ እድገት ቢሆንም ለውጭውም ቢሆን ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አሁን ዓለማችን ከደረሰችበት የግሎባላይዘሽን እድገት አኳያ ሲታይ በእጅጉ አስፈላጊና ተገቢም ነው ፡፡

## 2.2.4.6 የአገልግሎት ሞዴል (Utility model)

በአዋጅ ቁጥር 123/87 እና ደንብ ቁጥር 12/89 ለአነስተኛ የፈጠራ ሰዎች የሚሰጣቸው ጥበቃ የአገልግሎት ሞዴል ሰርትፍኬት እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 38 እና ከደንቡ አንቀፅ 39 መረዳት የሚቻል ሲሆን እንደ ፓተንት መብት ሁሉ የአገልግሎት ሞዴል በህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው የፈጠራ ስራዎችን ያካተተ ነው፡፡

በአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ የሚደረግላቸው የአዲስነትና የኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አነስተኛ ፈጠራዎች በአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት ጥበቃ ይደረግላቸዋል መመዘኛዎቹም፡፡

*አዲስነት - አንድ አነስተኛ የፈጠራ ስራ አዲስ ነው የሚባለው ማመልከቻው በተመዘገበበትቀን ኢትዮጵያ ውስጥ በታተሙ ፅሑፎች ላይ ቀደም ሲል ያልተገለፀ ወይም ለህዝብ ያልቀረበ ወይም በይፋ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፈጠራ ስራው ማመልከቻ ከመመዝገቡ ከ6 ወራት በፊት መገለፁና ጥቅም ላይ መዋሉ አዲስነቱ ኢያስቀረውም (አንቀፅ 39(1) (2))*

*ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት - አንድ የፈጠራ ስራ ኢንዱስትሪያዊ ተግባራዊነት አለው የሚባለው በዕደ ጥበብ፣ በግብርናና በማህበራዊ አገልግሎቶችና ሌላ በማናቸውም መስክ ሊሰራ ወይም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ነው፡፡ (አንቀፀ 3(5))*

የአገልግሎት መዴል ጥበቃ የሚሰጠው ለ5 ዓመት ሲሆን አነስተኛ የፈጠራ ስራው በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ የዋለ ከሆነ ለተጨማሪ 5 ዓመት ይታደሳል፡፡ (አንቀፅ 44(1)) አነስተኛ የፈጠራ ስራን መብት የሚያስጠብቀው የአገልግሎት ሞዴል ከፓተንት ጋር ሲነፃር ቀላል፣ ውድ ያልሆነና ፈጣን የፈጠራ ስራ ማስጠበቅያ መንገድ በመሆኑ ብዙዎች ሊገለገሉበት የሚችል የፈጠራ ስራ ማስጠበቀያ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአገልግሎት ሞዴል ጥበቃ የሚደረግላቸው የአነስተኛ የፈጠራ ስራዎች የመኖራቸው ያህል ጥበቃ የማይደረግላቸውም አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- *ፓተንት የተሰጠበት ወይም የህዝብ ንብረት የሆነን ነገር የቀድሞ ይዘት፣ ጠባይ ወይም ተግባር ቀይሮ በአጠቃቀሙ ወይም በታለመለት ተግባር መሻሻልን* የሚያስከትል ካልሆነ በቀር በቅርፅ፣ በመጠን ወይም በማተሪያል መልክ የሚደረግ ለውጥ የአገልግሎት ሞዴል ጥበቃ አይደረግለትም፡፡ (አንቀፅ 40(1))

- የታወቁ ንጥረ ነገሮችን ጥንቅር ተመሳሳይ ተግባር ባላቸው ሌሎች የታወቁ ንጥረ ነገሮች የመተካትና ይህም በሚገኘው ጥቅም ወይም አሰራር ላይ ምንም ዓይነት መሻሻል የማያስገኝ ሲሆን፡፡ (አንቀፅ 40(2))
- ለህዝብ ሰላምና ስነ-ምግባር ተፃራሪ የሆኑ አነስተኛ ፈጠራዎች ከሆኑ የአነስተኛ የፈጠራ ስራ መብት ማስጠበቅያ የሆነው የአገልግሎት ሞዴል ሰርተፍኬት አይስጥም፤ የሚደረግላቸው ጥበቃም አይኖርም፡፡ (አንቀፅ 40(3))

ስለዚህ የአገልግሎት ሞዴል ሰርተፊኬት ለአነስተኛ የፈጠራ ስራዎች መብት ማስጠበቅያ ተብሎ የሚሰጥ የፈጠራ መብት ሲሆን ጥበቃ የሚሰጣቸውና የማይሰጣቸው የአነስተኛ ፈጠራ ስራዎች በህግ ተለይተዋል:: ይህ መብት ፀንቶ የሚቆየው ለአምስት ዓመት ሲሆን የፈጠራ ስራው በአገር ውስጥ በስራ ላይ የዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሊታደስ ይችላል:: የጥሰት መፍትሔን (remedies) በሚመለከት በአሜሪካን አገር የፍ/ብሄር ተጠያቂነትን ብቻ የሚያስከትል ሲሆን በፈረሳይና አውስትራሊያ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው:: በኛ አገር ህግም የፍታብሄር ተጠያቂነት ከውል ውጭ ባለ ሃላፊነት በአንቀፅ 2027 ff በወንጀል ደግሞ በወ/ህ/ቁ 721 የሚያስጠይቅ ነው::

## 2.2.5 ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ (Industrial Designs)

የኢንዱስትሪ ንድፍ ማለት ምን ማለት ነው? የኢንዱስትሪ ንድፍ ማለት የመስመሮች ወይም የቀለሞች ቅንጅት ወይም ከመስመሮችና ከቀለሞች ጋር የተያያዘ ወይም ያልተያያዘ ባለሶስት ገፅታ ቅርፅ ሲሆን ቅንጅቱ ወይም ቅርፁ ለኢንዱስትሪ ወይም ለዕደ ጥበብ ውጤቶች ልዩ መልክ የሚሰጥና በኢንዱስትሪ ወይም ዕደ-ጥበብ ለሚመረት ምርት እንደ ንድፍ የሚያገለግል ነው፡፡ ሲል በአንቀፅ 2(2) ላይ ሲተረጉመው እውቁ Wikipedia free encyclopedia በህጋችን ከተሰጠው ትርጉም እምብዛም ባልተለየ መልኩ:-

> *Industrial design rights are Intellectual property rights that protect the visual design of objects that are not purely utilitarian. An Industrial design consists of creation of shapes, configurations or composition of patterns or color or combination of patterns and color in three-dimensional form containing aesthetic value.*

የሚል ትርጉም ሰጥቶታል::

### 2.2.5.1 ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው ንድፎች

በኢንዱስትሪ ንድፍ የንብረት ባለቤትነት መብት እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች የህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውና የማይደረግላቸው የኢንዱስትሪ ንድፎች ያሉት ሲሆን ጥበቃ የሚደረግላቸውን የተመለከተን እንደሆነ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ያሟሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል::

*የኢንዱስትሪ አዲስነት - አንድ የኢንዱስትሪ ንድፍ አዲስ ነው የሚባለው የንድፉ ዋና ዋና ባህርያት በኢትዮጵያ ወይም በውጪ ከታወቁ ተመሳሳይ ንድፎች የተለየና ከምዝገባ ቀን ወይም እንደ አግባቡ ከቀዳሚው ቀን በፊት ባለው አንድ ዓመት ግዜ ውስጥ ያልተገለፁ ሲሆን ነው፡፡ በንድፎቹ መካከል ያሉ የተለዩ ገፅታዎች ልዩነት በጥቃቅን ዝርዝሮች ከሆነ ተመሳሳይ ናቸው ተብለው ይወሰዳሉ፡፡ (አንቀፅ 46(2) (ሀ))*

*ተግባራዊ ተፈፃሚነት - አንድ የኢንዱስትሪ ንድፍ ተግባራዊ ተፈፃሚነት አለው የሚባለው ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ምርቶችን በተደጋጋሚ ለማውጣት በሞዴልነት ለማገልገል የሚችል ሲሆን ነው፡፡ (አንቀፅ 46(2) (ለ))*

የኢንዱስትሪ ንድፍ ህጋዊ ጥበቃ የማይደረግላቸው ንድፎችን ስንመለከት ደግሞ

- እውቅና ስለማይኖረው ጥበቃ ሊደረግለት አይችልም፡፡ (አንቀፅ 46(3))
- ቴክኒካዊ ውጤቶችን ለማግኘት ብቻ ለሚውሉ ማናቸውም ነገሮች በዚህ አዋጅ ለኢንዱስትሪያዊ ንድፎች የሚሰጠው ጥበቃ አይሰጣቸውም፡፡ (አንቀፅ 46(4))

ለህዝብ ሰላም ወይም ስነ-ምግባር ተፃራሪ የሆነ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ከሆነ አይመዘገብም፡፡ ካልተመዘገበ ደግሞ ህጋዊ ሰተርፍኬት ባለቤት በንድፉ ለመሰራት ወይም ለመልገል ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኃን ለመጠቀም ብቸኛ መብት እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡ (አንቀፅ 49) ይህን መብት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የኢንዱስትሪ ንድፉን ያቀፈ ምርት ናሙና ወይም የንድፉን ስእላዊ አምሳያና ንድፉ ሊያገለግል የታቀደውን የምርት ዓይነት መያዝ ይኖርበታል:: ከማመልከቻው ጋር የተመደበውን ክፍያ ይከፍላል:: ከዚህ በኋላ የቀረበው ንድፍ ተመርምሮ ተቀባይነት ካገኘ የኢዱስትሪ ንድፍ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ይሄውም የኢንዱስትሪ ንድፍ መብት እንዴት ይረጋገጣል? የኢንዱስትሪ ንድፍ መብት የሚረጋገጠው በምዝገባ ሲሆን የምዝገባው ይዘትም

- የንድፍ ስራው የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መሆኑን
- የኢንዱስትሪ ንድፉን ቀዳሚነት
- የኢንዱስትሪያዊ ንድፉን ሰራተኛ ማንነትና ባለቤቱ በኢንዱስትሪዊ ንድፉ ያለውን ብቸኛ መብት ይይዛል::

በመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ምዝገባ ወሳኝ ነው:: ኮሚሽኑ የቀረበለት ማመልከቻን በማስመልከት በሚሰጠው ውሳኔ አመልካቹ ካልተስማማው የውሳኔው ቅጂ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ60 ቀን ውስጥ ይግባኙን ወደ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል:: ስለዚህ በአገራች ሆነ በሌሎች አገሮች የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግ ለፈጠራ ስራ ጥበቃ የሚሰጥ ቢሆንም ለሁሉም የኢንዱስትሪ ንድፎች ሁሉ ልዩነት በሌለው መንገድ (indiscriminately) ጥበቃ የሚሰጥ ህግ ግን አይደለም::

### 2.2.5.2 መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

የኢንዱስትሪ ንድፍ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት እንደሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ፀንቶ የሚቆይበት ግዜ ያለው ነው:: አገሮች እንደየ ፍትሕ ስርዓታቸው የተለያየ መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ አላቸው:: ለምሳሌ በካናዳ 10 ዓመት፣ በጃፓን 15 ዓመት፣ በአሜሪካ 14 ዓመት በእንግሊዝ የተመዘገበና ያልተመዘገበ የሚል አሰራር ስለሚከተሉ የተመዘገበ ከሆነ 25 ዓመት ያልተመዘገበ ከሆነ ደግሞ ለ15 ዓመት ፀንቶ ይቆያል:: በኢትዮጵያም የምዝገባ ማመልከቻው ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ለ5 ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን ይህ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ እየዋለ መሆኑ ሲረጋገጥ ደግሞ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ መብት ለተጨማሪ ሁለት አምስት ዓመታት ሊራዘም ይችላል፡፡ (አንቀፅ 50(1)) ይህም የይራዘምልኝ ማመልከቻ የማብቅያ ግዜው ከመድረሱ በፊት ዘጠና ቀን አስቀድሞ በማመልከት ሊከናወን ይገባል ካልሆነ አይታደስም ፡፡ (አንቀፅ 50(2))

ስለዚህ የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የባለቤት መብት የሚሰጠው ለንድፍ ፈጣሪ ሲሆን ጥበቃ የሚሰጣቸው ንድፎች ለአገር ልማት ከሚያበረክቱት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንፃር እየታዩ ሲሆን በይዘታቸውና አላማቸው የህዝቡን ሁለንተናዊ እድገት ወደ ኃላ የሚጐትቱ የኢንዱስትሪ ንድፎች የማይመዘገቡና ከሶስተኛ ወገኖች ጥሰት ለመከላከል ማንኛውም ዓይነት የህግ ጥበቃ የማይደረግላቸው መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 123/1987 ድንጋጌዎችና ደንብ ቁጥር 12/89 አንቀፅ 40 እና ቀጥለው ያሉ ድንጋጌዎች ልንረዳው የምንችል እውነታ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ ንድፍ ህግ እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች ስርዓት ባለው መንገድ እየተመራ ለአገር ልማት እንዲውል የማድረግ ህዝባዊ አላማን መሰረት ያደረገ ነው ፡፡

### 2.2.6 የቅጅና ተዛማጅ መብቶች (Copy Right and Neighboring Rights)

የቅጅና ተዛማጅ መብቶችን በማስመልከት የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/96 በአንቀፅ 2(8) ላይ "የቅጅ መብት ማለት ከአንድ ስራ የሚመነጭ የኢኮኖሚ መብት ሲሆን አግባብነት ባለው ጊዜ የሞራል መብቶችን ይጨምራል" በማለት ሲተረጉመው ተዛማጅ መብት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ደግሞ በአንቀፅ 2(14) ላይ " ተዛማጅ መብት ማለት ከዋኝ፣ የድምፅ ሪከርዲንግ ፕሮዲሰር፣ የብሮድካስቲንግ ድርጅት በስራው ላይ ያለው መብት ነው" በማለት ተርጉሞታል፡፡ እውቁ Wikipedia free encyclopedia በበኩሉ

> *Generally it is "the right to copy", but also gives the copy right holder the right to be credited for the work, to determine who may adapt the work to other forms, who may perform the work, who may financially benefit from it, and others.*

በማለት የቅጂ መብት ለአእምሮ ንብረት ባለቤት የሚያስገኘውን መብት ሰፋ ባለመልኩ ተርጉሞት እናገኛለን፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ነገር የቅጂ መብት ሽፋን የሚሰጠው

ሃሳብን (ideas) እና መረጃን (information) ሳይሆን የህግ ጥበቃ የሚሰጠው የቅጂውን መብት መሰረት በማድረግ ስለሆነ ጥበቃው ለሃሳቡና ለመረጃው ሳይሆን ለአፃፃፍ ቅርፅ (forms) ወይም አገባብ (manner) መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የቅጅ መብት ተኩረት የሚያደርገውና ሽፋን የሚሰጠው ለሀሳቡ አገላለፅ አንጂ ሀሳቡ አንዳይጣስ ማድረግ አይደለም:: *Copy right usually protects the expression of an idea not the idea itself. Thus, copy right does not prohibit a reader from freely using and describing that concept to others, it is only the particular expression of that process as originally described that is covered by copy right.*

የቅጅና ተዛማጅ መብቶች አዋጅ አላማ በአገራችን ያለውን የስነ-ፅሁፍ፣ የኪነ ጥበብ እና ሌሎች ተመሳሳይ የፈጠራ ስራዎች የህግ ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግ የአገራችንን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኒኖሎጂያዊ እድገት በማፋጠን አገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል ነው፡፡ ይህን አብይ አላማ መሰረት በማድረግ አዋጁ ከአሁን ቀደም በፍታብሄር ህጉ ከቁጥር 1647- 1674 ባሉ ህጎች ለቅጅ መብት ተሰጥቶ የነበረን የጥበቃ ሽፋን በማስፋት አዳዲስ መሰረተ ሃሳቦችና መብቶች እንዲካተት ያደረገ ነው:: የማስተላለፍያ መንገዶቹ (transferability) እንዲሰፋ በማድረግ ተገቢ የሆነ ጥበቃ እንዲያገኙና ዋስትና አግኝተው ባለሙያዎቹ በልበ ሙሉነት እንዲሰሩ የማስቻል አላማን በመያዝ የወጣና በስራ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ከማንኛውም ግዜ በላይ በአደረጃጀትና አሰራር ተጠናክሮ በመሄድ ላይ ያለ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ ያገኘ የኢኮኖሚም ዘርፍ ነው፡፡ በቅጂ መብት ሽፋን የሚሰጣቸውን የአእምሮ ንብረቶች በማስመልከት Wikipedia ላይ ያየን እንደሆነ ፤

> *copy right may apply to a wide range of creative, intellectual, or artistic forms or "works" . . . can include, poems, theses, plays, other literacy works, moves, dances, musical composition, audio recordings, drawings, sculptures, photographs, software, radio and television broadcasts, and industrial designs, graphic designs.*

በማለት የቅጅ መብት ጥበቃ የሚያገኙ ስራዎችን በመዘርዘር ሲያሰፍር በአገራችን የወጣው አዋጅ ቁጥር 410/96 ከዚህ ጋር በተቀራረበ መልኩ ጥበቃ ስለሚደረግላቸው የቅጅ መብት ማስገኛ ስራዎች በአንቀፅ 4(1) (ሀ) (ለ) ላይ የሚከሉት ፈጠራ ስራ ጥበቃ ይደረግላቸዋል በሚል ስር፤

- ትርጉም፣ የማመሳሰል ስራ፣ ቅንብርና ሌላ የስራውን ዓይነት የሚቀይር ወይም የሚያሻሽል ስራ ወይም

- በይዘት፣ በቅንብር፣ ወይም በአመራረጥ የተነሳ ኦርጅናል የሆነና በሚነበብ መሳርያ ወይም በሌላ መልክ ያለ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የቅኔ ስብስብ ወይም ዳታቤዝን የመሳሰለ የስብስብ ስራ፡፡

በማለት የሽፋን አድማሱን ሲገልፅ የህግ ጥበቃ ለማግኘት ስለሚኖረው መስፈርት በማስመልከት ደግሞ በአንቀፅ 6(1) ላይ ማንኛውም የስራ አመንጪ የስራው አላማና ጥራት ከግምት ስውጥ ሳይገባ የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት መብት ሊያገኝ የሚችለው ስራው ወጥ ወይም ኦርጅናል ከሆነ፣ ከተቀረፀ ወይም ግዙፍነት ካገኘ ስራውን በማውጣት ምክንያት ብቻ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ እንደሚያገኝ ሲደነግግ ስራው የፎቶ ግራፍ ስራ በሚሆንበት ግዜ ደግሞ ከፍ ብለው ከተገለፁት መስፈርቶ በተጨማሪ ስራው የአንድ ስብስብ አካል ሲሆን ወይም በመፅሓፍ መልክ ሲታተሙ ወይም የስራ አመንጪውን ወይም ወኪሉን ስምና አድራሻ ሲይዙ እንደሆነ በአንቀፅ 6(2) (ሀ) (ለ) ላይ በግልፅ ሰፍሯል፡፡ ስለሆነም በአገራችን የአንድን ስራ ቅጂ መብት ለማግኘት የተጠቀመበት የአፃፃፍ ወይም የፎቶ አነሳስ ወይም የዘገባ ስርጭት ቅርፅ (form) ወይም አግባብ (manner) ኦርጅናል መሆንንና ስራዎቹ የፎቶና የብሮድካስቲን በሚሆኑበት ግዜ ደግሞ ኦጅናል ከመሆን በተጨማሪ በህጉ አንቀፅ 6(2) እና (3) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሟሟላት እንዳላባቸው ህጉ ያስገድዳል፡፡

### 2.2.6.1 የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች መብቶች

የቅጅ መብት ባለቤት ብቸኛ መብቶች (exclusive rights)

- ቅጂዎችን ማባዛት ወይም እንደገና ማባዛትና መሸጥ፤
- ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ከአገር ማውጣት፤
- የመጀመርያውን ስራ የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፤
- ስራውን ለህዝብ ማቅረብ፤
- መብቱን ለሌሎች የማስተላለፍ፤
- ስራውን በሬድዮና ቴሌቪዝን ማስተላለፍ ናቸው::

የቅጅና ተዛማጅ ስራ መብት የኢኮኖሚና የሞራል መብቶች በሚል ለሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን በአንቀፅ 19 ላይ ያለው ስለ ቅጂ ማሰራጨት መብትና በአንቀፅ 9 ላይ በግል አገልግሎት ስራ ስለማባዛት ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የቅጂ ስራ የአእምሮ ንብረት ባለቤት የሚኖሩት የኢኮኖሚ መብቶችን በማስመልከት ህጉ በአንቀፅ 7 ላይ ማንኛውም የስራ አመንጪ ወይም የአንድ ስራ ባለቤት የሚከተሉትን ለመፈፀም ወይም ሌላ ሰው እንዲፈፅማቸው ለመፍቀድ ብቸኛ መብት ይኖረዋል በማለት ስራን የማባዛት፣ የመተርጐም፣ የማመሳሰል፣ የማቀናበር፣ ወይም ወደ ሌላ ዓይነት የመቀየር፣ በሽያጭ ወይም በኪራይ ኦርጅናል ስራን ወይም ቅጅውን የማከፋፈል፣ ኦጂናል ወይም ቅጂውን ከውጭ አገር የማስገባት፣ ኦርጅናል ወይም ቅጅውን ለህዝብ የማሳየት፣ ስራን በይፋ የማከናወን፣ ስራን ብሮድካስት የማድረግ ወይም በሌላ መንገድ የማሰራጨት መብቶች ይኖሩታል፡፡ ይህ

እንደተጠበቀ ሆኖ ህጉ ለዚህ አጠቃላይ የቅጂ የኢኮኖሚ መብት ጥበቃ ሲሰጥ ለሁሉም ክንዋኔዎች እንዳልሆነ በአንቀፅ 7(2) ላይ የሚደነግግ ሲሆን በ7(3) ላይ ደግሞ ዋናው አመንጪ ወይም ወራሾች ስለሚኖራቸው ኢኮኖሚያዊ መብት በደንብ እንደሚወሰን ደንግጓል፡፡ አንድ የቅጂ ወይም ተዛማጅ ስራ ባለቤት የሚኖሩት የኢኮኖሚ መብቶች ከፍ ብለው የተዘረዘሩት ሲሆኑ ባለቤቱ በነዚህ መብቶች ሊሰራባቸው የሚችለው ወይም መብቱ ፀንቶ የሚቆየው እስከመቼ ነው? የሚለውን ጥያቄ አንስተን ስናይ የተለያዩ አገሮች የተለያየ የጊዜ ሰሌዳን ይጠቀማሉ ለምሳሌ በአሜሪካ መብቱ ፀንቶ የሚቆየው ከ50-70 ዓመት ሲሆን በየ 28 ዓመቱ መታደስን ይጠይቃል:: ከዚያ በኋላ የህዝብ ንብረት (public domain) ይሆናል :: በጣልያን ከሞተ በኋላ ለ6 ዓመት፤በፈረንሳይ ለ14 ዓመትና በስፔን ለ80 ዓመት መብቱ ፀንቶ የሚቆይበት ህግ አላቸው:: ወደኛ አገር ህግ ስንመጣ አዋጁ በአንቀፅ 20 ላይ:-

20(1) *" ኢኮኖሚ መብቶች የስራ አመንጪው በሂወት በቆየበት ዘመንና ከሞተ በኃላ ለወራሾቹ እስከ ሃምሳ ዓመት ፀንተው ይቆያሉ፡፡"*

20(2) *" በጋራ የስራ አምንጪዎች የተሰራ ስራን በሚመለከት ጉዳይ የሃምሳ ዓመቱ ግዜ መቆጠር የሚጀምረው የመጨሻው የስራ አመንጪው ከሞተበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡"*

20(3) *" የስራው አመንጪ ከሞተ በኃላ የታተመ ስራ የሃምሳ ዓመት የጥበቃ ግዜ መቆጠር የሚጀምረው ስራው ከታተመበት ግዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡"*

20(4) *" አንድ ከኦዲዮቪዥዋል ስራ ውጪ የሆነ ስብስብ ስራ አኮኖምያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም መጀመርያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመርያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻ ከሆነ አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመት ይሆናል፡፡"*

20(5) *" ስራው የአመንጪውን ሰም ካልያዘ ወይም በብእር ስም የታተመ ከሆነ የስራው አመንጪ የኢኮኖሚ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም መጀመርያ ለህዝብ ከቀረበበት ወይም መጀመርያ ከታተመበት ጊዜ የመጨረሻው አንዱ ጀምሮ ለ50 ዓመታት ይሆናል፡፡"*

20(6) *" በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (5) ከተመለከተው ግዜ በፊት የስራው አመንጪ ማንነት ከታወቀ ወይም የማያጠራጥር ከሆነ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደሁኔታው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡"*

20(7) *"በፎቶ ግራፍ ስራ ላይ ያሉ የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተው የሚቆዩት ስራው ከተሰራበት ግዜ ጀምሮ ለሃያ አምስት ዓመት ይሆናል፡፡"*

20(7) *"በኦዲዮቪዥዋል ስራ ላይ ያለ ኢኮኖሚያዊ መብት ፀንቶ የሚቆየው ስራው ከተሰራበት ወይም ለህዝብ ከተሰራጨበት ግዜ የመጨረሻ ከሆነው አንዱ ጀምሮ ለሃምሳ ዓመታት ይሆናል፡፡"*

ከዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው የኢኮኖሚ መብቶች ግዜው መቁጠር የሚጀምረው ሞትን ወይም የመጨረሻ ህትመትን ወይም ከሞት በኃላ ለሚወጣ ህትመት ህትመቱ ለመጀመርያ ግዜ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ መሆኑን ነው፡፡

የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች የኢኮኖሚ መብት እንደ ማንኛውም መብት ከባለቤቱ ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችል መብት ነው፡፡ የሚተላለፈውም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በማስተላለፍ ወይም ፈቃድ በመስጠት ሲሆን ውሉ መመስረት ያለበትም በፅሁፍ ነው፡፡ ይሄውም መብት በሚተላለፍበት ግዜ ፈቃድ የሰጠው ወይም የመብቱ ባለቤት የሚጠቀምባቸውን ቁሳዊ ነገሮች አያጠቃልልም፡፡ የመብት ማስተላለፊያው ሰነድ መብቱ የሚተላለፍበትን ጊዜ በግልፅ ካልያዘ የመብቱ ይተላለፍልኝ ጥያቄ መቅረብ የሚችለው በ10 ዓመት ግዜ ውስጥ ነው:: የፈቃድ ይተላለፍልኝ ጥቄያው ደግሞ በ5 ዓመት ግዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በሌላ አነጋገር የተጠቀሰው ግዜ ካለፈ በኃላ የይተላለፍልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ማለት ነው፡፡ (አንቀፅ 23 እና 24) በዚህ መንገድ መብቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይገለገልበት ከቀረና በቅጅና ተዛማጅ መብት ባለቤት መብት ላይ ጉዳት ያደርስ እንደሆነ የስራው አመንጪ የመብቱን መተላለፍ ወይም ፈቃድ መስጠትን ሊሽረው ይችላል፡፡(አንቀፅ 25)

የስራው አመንጪ የኢኮኖሚ መብቶች ባለቤት ቢሆንም ባይሆንም የሞራል መብቶች አሉት፡፡ እነዚህም:-

- ወቅታዊ ሁኔታን በብሮድካስት አማካይነት ለመዘገብ ባጋጣሚ ወይም በድንገት ከተካተተ ስራ ውጪ የስራ አመንጪነቱ እንዲታወቅ የመጠየቅ መብት አለው ፡፡ (አንቀፅ 8(1) (ሀ))
- ሳይታወቅ የመቆየት ወይም የብእር ስም የመጠቀምና ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጉድፍ የስራ መዛባት፣ መቆራረጥ ወይም በሌላ መልክ መቀየርን የመቃወም መብት ይኖረዋል፡፡ (አንቀፅ 8(1) (ለ)(ሐ))
- ስራን የማሳተም ሞራላዊ መብት ይኖረዋል፡፡ አንቀፅ 8(1) (መ))

አንድ የቅጅና ተዛማጅ ስራዎች ባለቤት በአንቀፅ 8 ላይ የተዘረዘሩትን የሞራል መብቶች ለወራሾች ወይም የስጦታ ተቀባዮች ካልሆነ በቀር በሂወት እያለ እነዚህን መብቶች ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገኖች ሊያስተላልፋቸው የሚችል መብቶች አይደሉም፡፡ (አንቀፅ 8(2)) የሞራል መብት የሚወረስ ወይም በስጦታ የሚሰጥ ቢሆንም  የስራው አመንጪ በሂወት ባለበትና መብቱ ፀንቶ ባለበት ግዜም ሆነ ወራሾች ወይም የስጦታ ተቀባዮቹ በመብቱ የተጠቃሚነት መብታቸውን ትተነዋል  ብለው ለማመልከት ይችላሉ፡፡ የሞራል መብቶች ፀንተው የሚቆዩበት የኢኮኖሚ መብቶች ፀንተው ከሚቆዩበት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አንቀፅ 8(3) (4))

አንድን የቅጂ መብት የተሰጠበትን ንብረት ፍትሓዊ በሆነ መንገድ መገልገልን (fair use) በማስመልከት የተለያዩ አገሮች የተለያየ አሰራርን የሚከተሉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የሚሰሩበት መለኪያን ወስደን ስናይ፤-

- የተጠቀመበት አላማና ባህሪው (purpose & characteristic)

- የቅጂ መብቱ ተፈጥሮ (nature)
- ከስራው የቱን ያህል ነው የተወሰደው (what amount or portion of the whole work was taken)
- በቅጂ መብቱ ላይ በገበያ የሚኖረው ዘላቂ ውጤት (the effect of the use upon the potential market for the value of the copyrighted work) የሚሉ ናቸው::

በካናዳ ለግል አገልግሎት አባዝቶ መጠቀም ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደ ሲሆን በአውስትራሊያ አባዝቶ መጠቀም የሚፈቀደው ለምርምር፣ ለጥናት፣ ተችቶ ለመፃፍ ፣ ለዜና ሪፖርትና የህግ ምክር አገልግሎት ለመስጠት ሲሆን ብቻ ነው:: በአሜሪካ ህግ 10 ቀጂ ማባዛት ለንግድ ስራ እንደተባዛ ይቆጠራል ከሚል በቀር ከዚያ በታች ማባዛት የተፈቀደ ስለመሆኑ በግልፅ የሚለው የለም:: የኢትዮጵያ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ህግም በአንቀፅ 9(1) ላይ አንድ ቀጂ (a single copy) ለግል አገልግሎት ሲባል ማባዛት የሚፈቅድ ነው:: ስለዚህ የኢትዮጵያ የቅጂና ተዛማጅ መብቶች ህግ አለም አቀፍ መመዘኛ (International standards) ያሟላና ለስራ አመንጭነት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ህገ-መንግስታዊ እውቅና የተሰጠው መብት ሆኖ እንደ ሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ሊተላለፍ የሚችልና የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለው የኢኮኖሚና የሞራል መብት የሚያስገኝ ንብረት ነው፡፡

## 2.2.6.2 የመብት ጥሰት መፍትሔዎች (Remedies)

የቅጅና ተዛማች መብቶች ለማስጠበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር 401/96 ሶስት ዓይነት መፍትሔዎችን የሚሰጥ ሲሆን እነሱም የፍ/ብሔር መፍትሔ፣ የደንበር ላይ እርምጃና የወንጀል ቅጣት ናቸው፡፡

### የፍ/ብሄር መፍትሔ

የፍታብሔር መፍትሔን በተመለከተ ስልጣኑ የተሰጠው ለመደበኛ ፍ/ቤት ሰለሆን ፍ/ቤት የመብት ጥሰት ያለመሆኑን ከማረጋገጡ በፊትና ካረጋገጠ በኃላ ሊወስድ ከሚችለው እርምጃ ዓንፃር በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: ይሄውም ከመረጋገጡ በፊት ሊወሰድ የሚችለው በጊዜያዊነት የእግድ ትእዛዝ (interim injunction) መስጠት ሲሆን የመብት ጥስት መኖሩ ከተረጋገጠ ግን

- ባለመብቱ ያወጣውን ወጭና ለደረሰበት ጉዳት ቁሳዊና ሞራላዊ ካሳ እንዲከፈለው ይወሰናል::
- ያለ ባለመብቱ ፈቃድ እንዳይባዛ ወይም ከአገር ውጭ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የተባለን ነገር ያስገባ ወይም ያሰራጨ ካለ እንዲወረስ ያዛል ::
- ከቅጅ መብት ጋር የተያያዙ የሂሳብ መግለጫዎች ሰነዶች፣ የንግድ ስራ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወረቀቶችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና እሽጉች እንዲያዙ ትእዛዝ ይሰጣል::

- አመልካች ከካሳው በተጨማሪ ያለአግባብ በልፅጓል ሲል የከሰሰ እንደሆነ ፈቃድ ቢሰጠው ሊከፍል ይችል የነበረውን ያህል እንዲከፍለው ይወስናል ::
- ባለቤቱ ከተጠርጣሪው የተገኘውን ትርፍ ብቻ እንዲከፈለው በጠየቀ ጊዜ እንዲከፍለው መወሰን፡፡ ተከሳሹ የተጠየቀው ትርፍ በሌላ ገበያ የተገኘ ሂሳብ ነው የሚል ከሆነ የማስረዳት ሸክም በተከሳሹ ላይ ይወድቃል፡፡
- ይሄውም ለባለመብቱ የሚከፈለው ካሳ ለደረሰበት ጉዳትና በመጣሱ ሌላው ወገን ያገኘውን ትርፍ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡
- የቅጅ መብት በመጣሱ ምክንያት የሚከፈል ሞራል ካሳ ከ 100.000 ብር ያላነሳ ሆኖ የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡
- ሆኖም ግን መብት የጣሰው ሰው ድርጊቱን የፈጸመው ባለማወቅ ወይም ሊያውቅ የሚችልበት በቂ ምክንያት የሌለው ከሆነ ፍ/ቤቱ ያገኘውን ትርፍ ብቻ እንዲመልስ ሊወሰን ይችላል፡፡
- ቅጅዎችን ወይንም ጥቅሎቹን በቅጅ ባለመብቱ ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከንግድ እንቅስቃሴ ውጭ እንዲሆኑ ወይም እንዲወገዱ ወይም በሌላ ተገቢ አኳኋን እንዲጣሉ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ይህ ቅጅዎችን በቅን ልቦና በያዘ 3ኛ ወገን ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ (አንቀፅ34)

## የደንበር ላይ እርምጃ

- በቅጅ ባለመብቱ በሚቀርብለት ማመልከቻ የጉምርክ ባለስልጣን ቅጅዎችን በቁጥጥር ስር ያደርጋል::
- ይህን እርምጃ መውሰዱ ለአመልካቹ ወይም የዕቃው ባለቤት ወድያውኑ ያሳውቃል::
- አመልካቹ በ10 ቀናት ውስጥ ህጋዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልቻለ እቃውን ለመያዝ የተወሰደው እርምጃ ይነሳል ::
- አመልካች ያቀረበው ማመልከቻ ህጋዊ መሰረት የሌለው ሲሆን በመያዙ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል::
- በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሰረት የጉምሩክ ባለስልጣን መብት የጣሰን ዕቃ መውረስ ይችላል፡፡ (አንቀፅ35)

## የወንጀል ሃላፊነት

- የወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ሆን ብሎ የቅጅ መብትን የጣሰ ሰው ከ 5 ዓመት ባላነሰ እና ከ10 ዓመት ባልበለጠ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- የወንጀል ህጉ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በከፍተኛ ቸልተኝነት በዚህ አዋጅ ጥበቃ የተደረገላቸው የቅጅ መብቶችን የጣሰ ከሆነ ከ 1ዓመት በማያንስና ከ 5 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሰራት ይቀጣል፡፡

- አግባብነት ባለው ግዜ ወንጀሉን ለመፈጸም ያገለገሉ ዕቃዎችን መሳሪያዎችን መብት የጣሱ ዕቃዎችን መያዝ፣ መውረስና ማውደምን ይጨምራል፡፡ (አንቀጽ36)

ስለዚህ የኢትዮጵያ የቅጅና ተዛማጅ መብቶች ህግ አለም አቀፍ መመዘኛ (International standards) ያሟላና ለስራ አመንጭነት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ህገ-መንግስታዊ እውቅና የተሰጠው መብት ሆኖ እንደ ሌሎቹ የአእምሮ ንብረት መብቶች ሊተላለፍ የሚችልና የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለውና የኢኮኖሚና የሞራል መብት የሚያስገኝ ስራ ነው፡፡ የመብቱ ተጠቃሚዎች የፍታብሄር መፍትሄ የሚያገኝ መሆናቸው በተጨማሪ የመብቱ ጥሰት የወንጀል ተግባርን ያካተተ ከሆነ በወንጀል ተጠያቂ የማስደረግን መብት የሚያጎናፅፍ ነው፡፡

## 2.2.7 የንግድ ምልክት (Trade Mark)

የንግድ ምልክት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 በአንቀፅ 2(12) ላይ፡-

> *የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱ ቃላቶችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን ወይም የዕቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርፅ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡ በማለት ሲተረጉመው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ* Wikipedia the free encyclopedia
>
> *Trade mark is a distinctive sign or indicator of some kind which is used by an individual, business organization or other legal entity to identify uniquely the source of its products and/or services to consumers, and to distinguish its products or services from those of other entities.*

ሲል የንግድ ምልክት ምንነትን ይገልፃል፡፡ ስለሆነም የንግድ ምልክት ማለት የአንድን ምርት ወይ አገልግሎት ወይም ምንጭ (origin) በማስመዝገብ እንደ ብቸኛ መለያ (exclusive sign) ተወስዶ ሰዎች አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላው ምርትና አገልግሎት ለመለየት የሚያገለግል ምልክት ሆኖ ማሳከር (confusion) የማስወገድ አላማ ያለው ነው፡፡

የንግድ ምልክት ህጋዊነት የሚመሰረተው ወይም ጥበቃ የሚያገኘው በምዝገባ እንደሆነ ከአዋጁ አንቀፅ 4፣ 5፣ 15 እና 16 መረዳት የሚቻል ሲሆን Wikipedia ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ የንግድ ምልክቶች የሚባሉ እንዴት ያሉ ምልክቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ልክ በአንቀፅ 2(12) እንደተዘረዘረው፡-

‘‘A trade mark is a type of intellectual property, and typically comprises a name, word, phrase, logo, symbol, image or combination of these elements.’’

በማለት የንግድ ምልክቶች ምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉ መዘርዘሩ ህጋችን የቱን ያህል አለማቀፋዊ መመዘኛዎችን (international standards) ያሟላ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ የንግድ ምልክት አላማም ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች መልካም ስም እና ዝና ለማስጠበቅና በተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል መሳከር (confusion) በማስወገድ የንግድ ስራ የነፃ ገበያ ስርዓትን መርህ ተከትሎ እንዲሄድና የሸማቾችን ምርጫ ማስጠበቅም ነው:: ብሄራዊ ጥቅም በተለይም የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂን እውን የማድረግ አላማም ያለው ነው፡፡ በመሆኑም ጤናማ፣ ነፃ ውድድርና በእውቀት ላይ የተመሰረተ የግብይት ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ህጉ በሚያዘውና ግልፅ በሆነ የንግድ ምልክት ላይ ተመስርቶ ማምረትና አገልግሎት መስጠት ለአንድ ህብረተሰብ እድገት ቁልፍ መሳርያ ነው፡፡ በመሆኑም በነፃ ገበያ መርህ መሰረት ጤናማ የምርትና አገልግሎት ውድድር በማካሄድ ህብረሰተቡ ሰፊ አማራጭ አግኝቶ ለከፈለው ዋጋ የሚመጥን እቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ የአዋጅ ቁጥር 329/95 የንግድ አሰራር መርህን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 2.2.7.1 የንግድ ምልክት ምዝገባ

ለምዝገባ ብቁ መሆን የሚቻለው፤-

- የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በግልፅ ለመለየት የሚያስችል መሆን ለመመዝገብና ህጋዊ ጥበቃ ለማግኘት አንዱ መስፈርት ነው፡፡ (አንቀፅ 5(1) )
- አንድ የንግድ ምልክት በጥቁርና ነጭ ወይም በከለር ቀለም ሊመዘገብ ይችላል:: በጥቁርና ነጭ ቀለም የተመዘገበ የንግድ ምልክት በማናቸውም የቀለሞች ቅንጅት ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን የንግድ ምልክቱ የተመዘገበው በከለር ቀለም ከሆነ ጥበቃ የሚደረግለት በተመዘገበው የከለር ቀለም ቅንጅት ብቻ ይሆናል፡፡ (አንቀፅ 5(2) )
- አንድ ሊመዘገብ የሚችል የንግድ ምልክት የምልክቱ ልዩ ባህሪ የሚቀንስ ወይም የሌላ ሰውን መብት የሚጥስ እስካልሆነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግላቸው የማይችሉ ክፍሎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ (አንቀፅ 5(3) )

ለምዝገባ ብቁ ስለማይሆኑ የንግድ ምልክቶች በማስመልከት አዋጁ በአንቀፅ 6 ላይ የዘረዘራቸውን ስንመለከት ደግሞ:-

- በአንቀፅ 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ ሲሆን ምልክቱ በንግድ ምልክትነት አይመዘግብም፣
- ድምፅ ወይም ሽታን የያዘ የንግድ ምልክት አይመዘገብም፣
- ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግልቶች ለመለየት የማያስችል ከሆነ የንግድ ምልክቱ አይመዘገብም፣
- የህዝቡን ሰላምና ስነ-ምግባር የሚፃረር ሲሆን እንደዚሁ አይመዘገብም ፣

- የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዓይነቶች፣ ጥራት፣ ብዛት፣ ጠቀሜታ፣ ዋጋ ወይም የመነጨበትን ቦታ፣ የተመረተበት ወይም የሚቀርብበትን ግዜ ወይም ባህሪ ብቻ የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣
- የንግድ ምልክቱ የሚመለከታቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሚመለከት ወይም በኢኮኖሚያዊ ወይም የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተለመዱና በጋራ መግባብያ ቋንቋነት የሚያገለግሉ ምልክቶች ወይም መለያዎች ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡
- ከዕቃው ተፈጥራዊ ሁኔታ የመነጨ ወይም የአንድን ዕቃ ቴክኒካዊ ውጤት ለማግኘት አስፈላጊ የሆነን ወይም ዕቃው ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚጨምርን ቅርፅ ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት::
- የዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ የመነጩበት ቦታ ወይም ዓይነትና ባህሪ በተለመከተ ህዝቡን ወይም የንግዱን ማህበረሰብ ሊያሳሳት የሚችል የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡
- ከአሁን ቀደም በተዘጋጀ ኦፊሴላዊ ምልክት የተመዘገበ የማንኛውም ሀገር መንግሰት፣ በይነ-መንግስታዊ ድርጅት ወይም በአለም አቀፍ ስምምነት የተቋቋመ ድርጅት፣ ወታደራዊ ምልክት፣ ሰንደቅ አላማ፣ ሌላ አርማ፣ ስም፣ ምህፃረ ቃል፣ የስም አህፅሮት መሰረት ያደረገ የንግድ ምልክት ሲሆን፡፡
- የአመልካቹ የቤተዘመድ ስብ ብቻ የያዘ የንግድ ምልክት
- ያለ ግለሰቡ ፈቃድ የአንድን በህይወት ያለ ግለሰብ ሙሉ ስም የያዘ የንግድ ምልክት ሲሆን በህግ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ አመልካች እንዲመዘገብለት የሚያቀርበው ምልክት የሶስተኛ ወገን መብት የሚነካ በሚሆንበት ግዜ አይመዘገብም:: ከዚህ አኳያ ህጉ የሶስተኛ ወገኖችን መብት በመጠበቅ የንግድ ምልክት እንዳይደረግ የሚከለክልባቸው ሁኔታዎች በአንቀፅ 7 ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን እነሱም፤
- ቀደም ሲል ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሲሆንና ማሳከርን (confusion) የሚፈጥር ሲሆን፤
- የንግድ ምልክቱ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆነ የሌላ ሰው እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ፤
- በባለቤቱ በፅሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግለትን የሌላ ሰው የስነ-ፅሁፍ ወይም ኪነ-ጥበባዊ መብት ወይም የሌላ ሰውን የፎቶግራፍ ወይም የዲዛይን መብት የያዘ ነው ተብሎ ሲታመን የንግድ ምልክቱ አይመዘግብም፡፡ ያለመመዝገብ ህጋዊ ውጤት እንደሚታወቀው የህግ ጥበቃ አለማግኘትና ከህግ ጋር በሚፃረርበት ግዜ ደግሞ ለፍ/ብሄርና ወንጀል ተጠያቂነት የሚዳርግ ነው፡፡

### 2.2.7.2 ምዝገባ የሚያስገኘው መብት

- ባስመዘገበው የንግድ ምልክት የመጠቀም ወይም ሌላ ሰው እንዲጠቀበት የመፍቀድ መብትን ያስገኛል፡፡
- ሌሎች ወገኖች የንግድ ምልክቱን በሚያሳስት መንገድ እንዳይጠቀሙና ህዝቡን እንዳያሳስቱ የማድረግ መብትን ያጐናፅፋል፡፡
- ሌሎች ሰዎች የባለቤቱን ጥቅምን በሚጐዳ አኳኃን እንዳይገለገሉበት የማድረግ መብት ይሰጣል፡፡
- ሌሎች መሰል ድርጅቶች ተመሳሳይ ምልክት ተጠቅመው ማሳከር በመፍጠር መብቱ እንዳይጐዱ ለማገድ የሚያስችል መብት ያስገኝለታል::
- የንግድ ምልክት ማሳከር (confusion) ተፈጥሯል ባለበት ግዜ ክስ የመመስረት መብት ይኖረዋል፡፡ (አንቀፅ 26)

የአንድ የንግድ ምልክት መመዝገብ ከፍ ብለን ያየናቸውን መብቶች የሚያስገኝ ቢሆንም መብቶቹ ያለገደብ የተሰጡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም አንቀፅ 27 በምዝገባ የተገኙ መብት ገደብን በማስመልከት የንግድ ምልክቱን በመያዝ በእቃዎቹ ምንጭ ዓይነት ለውጥ ሳይደረግባቸው በማንኛውም አገር በመሸጥ ላይ ባሉ ሶስተኛ ወገኖች ላይ የንግድ ምልክቱ ባለቤት የመከልከል መብት አይኖረውም፡፡ እንዲሁም ሶስተኛ ወገኖች በቅን ልቦና ዕቃቸውን ወይም አገልግሎታቸውን ምንጭ በማያሳስት መንገድ ለማስተዋወቅ ወይም ለመረጃ አላማ እንዳይገለገሉበት የንግድ ምልክት ባለቤቱ መከልከል አይችልም፡፡ ይህ ማለት ግን ሶስተኛ ወገኖች በነዚህ ገደቦች ሽፋን በባለመብቱ ላይ ጉዳት እዲያደርሱ ህጉ ፈቅዷል ማለት አይደለም፡፡

የንግድ ምልክት በምዝገባ መብቶችን ሲያስገኝ ገደቦች ያሉበት እንደመሆኑ ሁሉ የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ፈራሽ የሚሆንባቸው ሁኔታዎችና የምዝገባው ፈራሽነት ውጤት ምን እንደሆነም በህጉ ሽፋን ተሰጥቶታል፡፡ ምዝገባው ፈራሽ የሚሆነው በአዋጁ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሳያሟሉ የቀሩ እንደሆነ ምዝገባው ፈራሽ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ምዝገባው በከፊል ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ ከሆነ ባልተመዘገቡት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ የንግድ ምልክቱ በከፊል ፈራሽ ይሆናል፡፡ (አንቀፅ 36) የምዝገባው ፈራሽነት ውጤትም ውሳኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው የንግድ ምልክቱ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ይህም ማለት የምዝገባው ፈራሽነት ወደ ኃላ ተመልሶ ውጤት (retroactive effect) ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ የሶስተኛ ወገኖች መብትን ለመጠበቅ የንግድ ምልክቱ ፈራሽ ስለመሆኑ በአእምሮ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ አገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በማውጣት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ በዚህ መንገድ ፈራሽ የሆነ የንግድ ምልክት ባለቤት በፈቃድ ውል ምልክቱን የሰጠው አካል ይህን የንግድ ምልክት እንዲከፍል ያደረገው ገንዘብ ቢኖርም ይመለስልኝ ብሎ መጠየቅ ግን አይችልም፡፡ ስለዚህ የንግድ ምልክት ፈራሽ መሆን ሁለት ውጤቶች ያሉት ሲሆን እነሱም ወደ ኃላ ተመልሶ የመስራትና ለምዝገባው ሲባል የተከፈለ ገንዘብ ካለም

የማይመለስ መሆኑ ናቸው፡፡ (አንቀፅ 37) ከፍ ብለን የተመለከትናቸው የምዝገባ ውጤቶች ወይም መብቶች፣ ገደቦቻቸው፤ ፈራሽነትና ውጤቱን ሲሆን የንግድ ምልክት ምዝገባ ሊታደስ፣ ሊተውና በጥቅም ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ስለሚሰረዝበትና በዚህ መብት የመጠቀም በሙሉ ወይም በከፊል መብት በመስጠት ወይም ፈቃድ በመስጠት ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ስርዓትም በህጉ (በአንቀፅ 20፣ 25፣ 34፣ 35፣ 28) ላይ በዝርዝር ተደንግገው የምናገኛቸው ናቸው፡፡ የንግድ ምልክት እንደሌሎች የአእምሮ ንብረቶች የራሱ የሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ያለው ሲሆን አንቀፅ 24 ይህን በማስመልከት "በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ 35 እስከ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ምልክት ምዝገባ ፀንቶ የሚቆየው የምዝገባው መመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለሰባት ዓመታት ይሆናል " ሲል የሚደነግግ ሲሆን አንቀፅ 35 ጥቅም ላይ ያልዋሉ የንግድ ምክቶች ስለሚሰረዙበት ሁኔታ የሚደነግግ ህግ እንደመሆኑ መጠን አንድ የተመዘገበ የንግድ ምልክት በስራ ላይ ባልዋለበት ግዜ የግድ ፀንቶ የሚቆይበት 7 ዓመት መጠበቅ ሳያስፈልግ ሊሰረዝ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በአንቀፅ 36 እንደዚሁ አንድ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ፈራሽ ስለሚሆንበት ሁኔታ የሚደነግግ በመሆኑ በዚህም ሁኔታ ፀንቶ የሚቆይበትን 7 ዓመት መጠበቅ አስፈላጊ ያለመሆኑን ይገልፃል፡፡ አንቀፅ 37 ስለፈራሽነት ውጤት የሚደነግግ በመሆኑ የንግድ ምልክቱ ፀንቶ ባይቀጥልም በመፍረሱ ምክንያት የሚኖረው ውጤት ወደ ኃላ ተመልሶ እንዳልተመዘገበ እንደሚቆጠርና በምዝገባው ምክንያት የተከፈለው ገንዘብ የማይመለስ ስለመሆኑ የሚደነግግ በመሆኑ የአንቀፅ 24 ሐሳብ ፀንቶ የሚቆየው ለሰባት ዓመታት ቢሆንም በመሃል ግን የንግድ ምልክቱ ምዝገባ ሊሰረዝ፣ ፈራሽ ሊሆንና የፈራሽነት ውጤት ሊኖው እንደሚችል የሚደነግግ ነው፡፡

የንግድ ምልክት ምዝገባን በማስመልከት መዝጋቢው ፅ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በይግባይ ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት መሄድ ይችላል:: ስለዚህ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት በሶስተኛ ወገኖች ለሚደርስ ጥሰት የፍታብሄር መፍትሄ (civil remedies) እና የወንጀል ቅጣት (criminal sanctions) በማስከተል የፍታብሄርና የወንጀል ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ ህግ ከፍተኛ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚያደርግለት መብት ነው፡፡(አንቀፅ 17፣ 40 እና 41)

እስከ አሁን ያየናቸውን አጠር ባለ መንገድ ለማስቀመጥ የንግድ ምልክት እንደሁሉም የአእምሮ ንብረቶች ከምዝገባ በኃላ የሚገኝ የግዙፍነት የሌለው የንብረት መብት ሆኖ በሂደት ሊሰረዝ፣ ፈራሽ ሊሆን፣ ሊተውና ሊታደስ የሚችል መብትና ግዴታ ያለበት በመጨረሻም ከ7 ዓመት በኃላ ካልታደሰ መብቱ ቀሪ የሚሆንና ህግ የፍታብሄርና የወንጀል ጥሰት እንዳይገጥመው በፍትህ ስርዓቱ ከፍተኛ የሆነ ጥበቃ ተሰጥቶት የአገር ኢኮኖሚ ጤናማ በሆነ የግብይት ስርዓት ላይ እንዲመሰረትና የሸማቶችን መብት ከማሳከር (confusion) ነፃ በሆነ መንገድ በነፃ ፍላጐት ላይ የተመሰረተ የዕቃ ወይም የአገልግሎት ምርጫ እንዲካሄድ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት ለኢኮኖሚ ልማቱ ስኬት የግብይት ስርዓቱ የነፃ ገበያ መርህን ተከትሎ እንዲሄድ የማድረግ አለማና ግብ ያለው ነው::

### 2.2.7.3 የመብት ጥሰት መፍትሄዎች (Remedies)

የንግድ ምልክትን መሰረት በማድረግ ክርክር በሚነሳበት ጊዜ ፍ/ቤት እና የጉምሩክ ባለስልጣን ጊዜያዊ መፍትሄዎች ሊሰጡ እንደሚችሉና ዘላቂ መፍትሄም በፍ/ቤት ሊሰጥ እንደሚችል ይኸውም የፍ/ብሄር እና የወንጀል መፍትሔ ብሎ ማስተናገድ እንደሚቻል አዋጁ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

### የፍ/ብሄር መፍትሔ

በዚህ አዋጅ መሰረት በጊዜያዊ የፍ/ብሄር መፍትሔነት የሚወሰዱት ጊዜያዊ እርምጃዎች ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ የሚሰጥ ጊዜያዊ እግድ (interim injunction) ሲሆን ይኸውም አዋጁ በአንቀፅ 39(4) (ሀ)ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ155 (1) ከተደነገገው በተሻለና ግልፅ በሆነ መንገድ እግድ ለመስጠት አደጋ ላይ የወደቀው ጥቅም በካሳ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ አደጋው የማይቀር መሆኑ ሲረጋገጥ፣ የክሱን ጥንካሬና ውሳኔ መስጠት በእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በመመርመር እግድን መስጠት እንደሚቻል የሚደነግግ በመሆኑ በፍ/ቤት ስልጣን ላይ ልጓም ያበጀ ነው፡፡

የሁለቱ ተከራከሪዎች አቋም ተመሳሳይ በሚሆንበት ጊዜም ፍ/ቤት ጠለቅ ያለ ምርመራ (deep investigation) ማካሄድ እንዳለበት አዋጁ በአንቀፅ 39 (4) (ሐ) ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ በዚሁ አዋጅ የሚሰጥ እግድ ስለተጠየቀ ብቻ የሚሰጥ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የንግድ ምልክት ክርክር በሚኖርበት ጊዜ ሌላው ሊወሰድ የሚችል መፍትሔ ንብረቱ ዋስትና ተደርጐለት ለ10 ቀናት በጉምሩክ ተይዞ እንዲቆይ ማድረግ ሲሆን ከሳሽ ወይም መብቴ ተጣሰ በማለት አቤቱታውን ለጉምሩክ ባለስልጣን ያመለከተ ሰው በዚያ 10 ቀን ውስጥ ከፍ/ቤት ትዕዛዝ ካላመጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ ሆኖ ንብረቱ ለሌላው ወገን ይመለስለታል:: (አንቀፅ 42(1)) የዚህ ህግ ፋይዳም ባለመብቱ የእፎይታ ጊዜ(breathing time) አግኝቶ ጉዳዮን ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብና መመዘኛዎቹን አሟልቶ ከተገኘ ከፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ በማውጣት በመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ጊዜ መስጠት ነው፡፡ ሌላው በአዋጁ ያለ ጊዜያዊ መፍትሔ ፍ/ቤት ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ ምክንያት አንደኛው ወገን መብቴ ተጥሷል በማለት ያመለከተ እንደሆነ በአንቀፅ 39(1) (ለ) እና 39(5) መሰረት ለክርክር መነሻ የሆነው ንብረት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 161(1) (ሀ) እና በወ/ሰ/ሰ/ህ/ቁ32 መሰረት እንዲበረብርና እንዲያዝ እንዲሁም እንዲታሰር ወይም እንዲታቀብ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ለፍ/ቤቱ ስልጣን የሚሰጥ በመሆኑ አንድ የንግድ ምልክት ባለቤት መብቱ እንዲሁ እንዳይጣስ የህግ ከለላ የሚሰጠውና በዘላቂነትም በፍ/ቤት ውሳኔ መብቱን እንዲያስከብር የሚያስችል ነው፡፡ እስካሁን ያየናቸው አንድ የንግድ ምልክት ባለቤት መብቴ ተጥሷል ባለበት ጊዜ ስለሚያቀርበው ክስና ጊዜያዊ መፍትሔ:: ቀጥለን ስለሚኖሩት ዘላቂ መፍትሔዎች (Final Remedies) እናያለን፡፡

አንዱ መፍትሔ በፍ/ ቤት ከሶ ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡ ሌላው የንግድ ምልክት ባለቤቱን መብት መጣሱ ከታወቀ በዚያ ጊዜ ውስጥ ያገኘውን ትርፍ(

Account of Profit) እንዲመለስ ማድረግ ሲሆን የዚህ ዓይነቱ መፍትሔ በአፈፃፀም ላይ አንድ ህገ ወጥ ስራን የሚሰራ ሰው የንግድ ሒሳብ ደብተር ይይዛል ተብሎ ስለማይገመት ስሌቱ ለማወቅ አስቸጋሪ የሆነ የመፍትሔ አገባብ ነው፡፡ ገንዘባዊ ጥቅም ካላቸው መፍትሔ በተጨማሪ ፍ/ቤት የእንዲታወቅ ፍርድ (declaratory judgment) በመስጠት የንግድ ምልክት መብት በሶስተኛ ወገኖች እንዳይጣስ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አዋጁ በፍ/ብሄር መፍትሔነት ያስቀመጣቸው እግድ (injunction) እና ካሳ (compensation) ሲሆኑ በአንቀፅ 40(2) ያለው የካሳ አከፋፈል ስርዓት በፍ/ብ/ህ/ቁ 2091 ከተደነገገው ጉዳት ካሳ = የጉዳት መጠን ከሚለው መርህ ማፈንገጥ (deviation) የሚስተዋልበት ነው፡፡ ይኸውም የንግድ ምልክት መጣስን ተከትሎ የሚመጣ የካሳ አከፋፈል ስርዓት መሰረቱ ጉዳት (damage) መሆኑ ቀርቶ መብት ጥሷል የተባለው ሰው መጣሱ ከተረጋገጠ በዚያ ንግድ ምልክት ጥሶ በመነገድ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ በሙሉ እንዲከፍል በማድረግ ወይም ፈቃድ ተሰጥቶት ቢነግድ ይከፈል ከነበረው ኪራይ(royalty) የሚበልጥ እንዲከፍል በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ስሌቱ "Compensation equals to damage" መሆኑ ቀርቶ የዚህ አዋጅ መርህ ለየት ባለ መንገድ ስለቱ "Compensation equal to net Profit or royalty +" ነው፡፡ በመሆኑም የንግድ ምልክት አዋጅ ቁጥር 501/98 የሚከተለው የካሳ አከፋፈል ክልሰ ሓሳብ (theory) ያለአግባብ መበልፀግን the theory of unlawful enrichment ክልስ ሐሳብ ሲሆን የፍ/ብሄር ህጉ የሚከተለው የጉዳት ካሳ አከፋፈል the theory of damages ክልስ ሓሳብን የተከተለ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ አዋጁ በአንቀፅ 40(1) ላይ ልክ በፍ/ብሄር ህጉ አንቀፅ 2121 ላይ እንደተደነገገው ዘላቂ እግድ (permanent injunction) ሊሰጥ ስለሚችልበት ሁኔታ " ተከሳሹ የመብት መጣስን ድርጊት እንዲያቆም ሊወሰን ይችላል በማለት ስለሚደነግግ ለባለ መብቱ ከፍተኛ የአእምሮ ንብረት መብት ጥበቃ የሚሰጥ ነው፡፡

የፍ/ብሄር መፍትሔን በማስመልከት ስለሚኖሩ ጥሰቶችና መፍትሄዎቻቸው እንደተገለፀው ሆኖ የንግድ ምልክት ባለቤቱን መልካም ስምና ዝናን (reputation of honor) እንዲመለስልት ፍ/ቤት ፍ/ብ/ህ/ቁ 2120 እና ን/ህ/ቁ/134(2) (ሀ) በሚያዙት መሰረት በማስታወቂያ እንዲወጣና ህዝቡ እንዲያውቀው እንዲደረግ ለማዘዝ ስለሚችል የንግድ ምልክቱ ባለቤት በዚህ ራሱን መልሶ ወደ ገበያው በማስገባት ለበለጠ ጥቅም ሊሰራ የሚያስችለውን ሁኔታ እንዲመቻችለት ያደርጋል፡፡

## የወንጀል ሃላፊነት

በመጨረሻም አዋጁ የንግድ ምልክት ጥሰትን መሰረት በማድረግ የፍ/ብሄር መፍትሄዎች እንደሚደነገግ ሁሉ በአንቀፅ 41 ላይ ወንጀልን በማስመልከት የንግድ ምልክት መብት ጥሷልተብሎ የተጠረጠረው ሰው ድርጊቱ መፈፀሙ ሲረጋገጥ በወ/ህ/ቁ 720 መሰረት ሆነ ብሎ የጣሰ ከሆነ ከ5 ዓመት በማያንስና ከ15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው በቸልተኛነት ከሆነም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ

እስራት ይቀጣል፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን ለመፈፀም ያገለገሉ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎችና መብት የተጣሰባቸውን ዕቃዎች መያዝ፣ መውረስና እና ማስወገድን ያጠቃልላል ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የንግድ ምልክት መጣስ የቱን ያህል እንደሚያስቀጣ ብቻ ሳይሆን ህጉ ህዝቡ በህጋዊ የንግድ ምልክት ባልተጠቀሙ ግለሰቦች እንዳይታለልና ያልሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት በመግዛት ሊደርስበት ከሚችል ጉዳት ለመጠበቅ የቱን ያህል ክብደት እንደሰጠ ነው:: ከዚህ ህግ በስተጀርባ ያለው ህዝባዊ ፖሊስ ስግብግብ ነጋዴዎችን ከድርጊታቻው እንዲታቀቡ በማድረግ ህ/ሰቡን የነፃና ፍትሐዊ ግብይት ስርዓት ተጠቃሚ ማድረግም ጭምር ነው:: ስለዚህ የአእመሮ ግዙፍነት የሌላቸው የሚንቀሳቀስ ንብረቶቸ መብት የንግድ መደብር መብቶችም ስለሆኑ በንግድ ህጉ ከተሰጣቸው የህግ ሽፋን በላይ በነዚህ አዋጆች ጥበቃ የተደረገላቸው በመሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ የሚነሱ አለመገባባቶች በንግድ ህጉና ሌሎች አዋጆች መፍትሄ ሊያገኙ ይገባለ፤፤

## 2.3 በንግድ መደበር ላይ የሚደረግ የዋስትና መያዣ

የንግድ ህጉ በንግድ መደብር ያለን መብት በመያዣ ዋስትና ማስያዝ እንደሚቻል በን/ህ/ቁ 179 እና ቀጥሎ ባሉ ድንጋጌዎች የሚፈቅድ መሆኑ ከእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል ፤፤የዚህ ዓይነት መያዣ ምዝገባን በማስመልከት በነጋሪት ጋዜጣ እንደሚወጣ በን/ህ/ቁ 1175 ላይ ተደንግጎ ለዓመታት ህጉ በነጋሪት ሳይወጣ መቆየቱ ካለው እውነታ ለመረዳት የሚቻል ሓቅ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት ከወጣ በኋላ ግን በንግድ ተቋማት ዙርያ የሚታየውን ክፍተት ለሞምላትና ለኦኮኖሚው እንቅስቃሴ አመች ሁኔታ ለመፍጠር የንግድ ተቋሞቻቸውን በባንክ በዋስትና ካስያዙ ባለዕዳዎች ላይ ጥሩ የንግድ አሰራር ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ኣዋጅ ቁጥር 98/90 ወጥቶ በስራ ላይ ከዋለ እንሆ አሰርት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በዚህም መሰረት በኣዋጁ አንቀፅ 2(1) ላይ ለንግድ ተቋሞ ማለት በ1952 ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ የተመለከተው የንግድ መደብር ነው" በማለት ፍችው የሚሰጥ ሲሆን በአንቀፅ 2(5) ላይ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ኣካል ነው ይላል፡፡

አንድን የንግድ ተቋም በመያዣነት ለማስመዝገብ የንግድ ፍቃድ ለመስጠት በህግ ስልጣን ከተሰጠው የንግድ ፍቃድ መኖርን የሚጠይቅ ሲሆን ለመመዝገብ በኣዋጁን ኣንቀፅ 5 እና 6 መስፈርቶችንና መሟላት ያለባቸውን ነገሮች እንዲሟሉ ህጉ ያስገድዳል፡፡ በዋስትና መያዣነት በን/ህ/ቁ 175(1) (ሰ) እና 178(1) (ሠ) መሰረት የተሰጠን ንብረት ገንዘብ ጠያቂው መለያ ምልክት (identification mark) ሊያደርግባቸው ይችላል፡፡ በኣዋጁ አንቀፅ 13 መሰረት ን/ህ/ቁ 189 ቢኖርም የመያዣ ዋስትና መያዣ ያለው ገንዘብ ጠያቂ ባንክ የሚፈልገው ገንዘብ ሳይከፍል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቅያ ለባለ ዕዳው በመስጠት ንብረቱን በሓራጅ

የመሸጥና ንብረቱን ወደ ገዢ የማስተላለፍ ወይም በመጀመርያው የሓራጅ ሽያጭ ገዥ ከጠፋ ንብረቱን በዋስትና በሰጠው መጠን የባለቤቱን መብት በስሙ እንዲዛወር ያደርጋል፡፡ ይህ ኣዋጅ ቀደም ሲል ኢትዮጵያ ስትከተለው ከነበረው የመያዣ ንብረት በፍ/ቤት ኣሽጦ ዕዳን መክፈል (Judicial foreclosure) ወደ ገንዘብ ጠያቂው በዋስትና የያዘውን የንግድ ተቋም በራሱ ኣሽጦ ገንዘቡን ገቢ ወደሚያደርግበት (power of sale foreclosure) እንዲሸጋገር ያደረገ አሰራር ነው፡፡

ይህ ኣዋጅ ወደኋላ ተመልሶ ስለሚኖረው ውጤትም በአንቀፅ 14 ላይ ከኣሁን ቀደም በን/ህ/ቁ 1175(2) መሰረት ተመዝግበው የነበሩትን የንግድ ተቋም መያዣዎች ከ30 ቀን ላላነሰ ጊዜ ማስጠንቀቅያ በመስጠት ልክ በኣዋጁ አንቀፅ 13 ከተገለፀው ባልተለየ መልኩ ለባንክ መብት የሚሰጥ ነው፡፡ ባንክ በዋስትና መያዣ የያዘውን ንበረት በሓራጅ በሚሸጥበት ጊዜ እንደኣግባብነታቸው ፍ/ብ/ሰ/ሰ/ሕ/ቁ 394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ሂደቱን መምራት እንደሚጠበቅበት የኣዋጁ አንቀፅ 16 የሚደነግግ በመሆኑ የባለእዳዎች መብት የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ ግልፅ ነው፤፤ አንድ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ በኢትዮጵያ የንግድ ተቋም በዋስትና መያዣነት የመስጠትና የምዝገባ ስርዓት ውሉ የሚደረገው ከባንክ ጋር በሚሆንበት ጊዜ የኣዋጅ ቁጥር 98/90 ድንጋጌዎችን መከተል የግድ የሚል መሆኑና ውሉ የሚደረገው ከባንክ ውጭ ከሆነ ሰው ጋር በሚሆንበት ግዜ ግን የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ማስተናገድ ስለሚኖርብን የፍትህ ስርዓቱ ሁለት የንግድ ተቋም የዋስትና መያዝን ምዝገባን አሰራር የሚከተል መሆኑ ነው፡፡ በዋስትና የተያዘን ንብረት አሽጦ ለእዳ መክፈያነት ማዋል(foreclosure) ምን ማለት እንደሆነ ስንመለከት፤-

> *Foreclosure is defined as to shut out, to bar, to destroy an equity of redemption, a termination of all rights of the mortgagor or his guarantee in the property covered by the mortgage... the term is also loosely applied to any of the various methods, statutory or otherwise known in different jurisdictions, of enforcing payment of the debt scurried by a mortgage by taking and selling the mortgaged estate. የሚል ትርጉም ያለው ነው፤፤*

የመያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነቶችም ጥብቅ መያዣን ለዕዳ መክፈያ ማዋል(Strict foreclosure) ይህ ዓይነት የመያዣ ዕዳ መክፈያነት ማዋል በፍርድ መያዣ ተቀባዩ በመያዝነት የያዘውን የንብረት ባለቤትነት ወደ እሱ እንዲዛወርለት አመልክቶ ዕዳ ከፋዩ ፍርድ ቤት በሚሰጠው የመፈፀምያ ጊዜ ውስጥ ዕዳው ሳይከፍል ቢቀር መያዣ ተቀባዩ (ገንዘብ ጠያቂው) በመያዣነት ባስያዘው ንብረት ላይ ለመጨረሻ ግዜ የባለቤትነት መብቱ የሚያጣበት የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነት ነው፡፡ ጥብቅ የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ያለው ጠንካራ ጎን አሰራሩ መያዥ ተቀባዩን(ባለሃብቱን) በመያዥነት የያዘውን ንብረት ለዕዳ

መክፈያነት ንብረቱን እንዲወስድ የሚፈቅድ አሰራር ስለሆነ ባለ ሃብቱን ንብረቱን ሲሸጥ የሚያወጣውን ወጪ የሚቀንስ ከመሆኑም ባሻገር በፍርድ ሂደት የሚጠፋውን ረጅም ግዜና ክፍያ እንዲቀንስለት የሚያደርግ አሰራር ስለሆነ ከባለ ሃብቱ ጥቅም አኳያ ስታይ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ አሰራር ካለው ደካማ ጎን አንፃር ሲታይ ደግሞ በመያዣነት የተያዘውን ንብረት የዕዳው መክፈያ ግዜ በማለቁ ብቻ የአንድን ሰው ሃብት ዕዳውን ባለመክፈሉ መያዣ ሰጪውን ካለው ዕዳ በላይ የሚያወጣውን ንብረት እንዲያጣ በአንፃሩ መያዣ ተቀባዩን ማግኘት ከሚገባው ሃብት በላይ እንዲያካብት የሚያደርግ አሰራር በመሆኑ ከባለ ዕዳው መብት በእጅጉ የሚጎዳ አሰራር ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አሰራር በመጥፋት ላይ ያለ የመያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል አሰራር ነው፡፡

በፍርድ ቤት ውሳኔ መያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል (Judicial Foreclosure) የዚህ ዓይነት የመያዥ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ፍርድ ቤት በመያዣ የተያዘውን ንብረት ተሸጦ ለዕዳ መክፈያነት እንዲውል የሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት ንብረቱ ተሸጦ ዋጋው በዕዳ ከሚጠየቀው የገንዘብ መጠን በላይ በሆነ ግዜ ለዕዳ መክፈያነት ከዋለው ገንዘብ ውጭ ያለውን ቀሪ ገንዘብ በባለ ዕዳው እንዲመለስ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚሰጥበት የሚያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል አሰራርን የሚከተል የመያዣ ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዓይነት አሰራር በአገራችን የፍታብሄር ህግ ቁጥር 2851 እና 3060ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 65/89 ከመውጣቱ በፊት ፍ/ብ/ሰ/ሰ/ህ/ቁ.394-449 ባሉ ድንጋጌዎች ሲሰራበት የቆየ የመያዥ ንብረትን ለዕዳ መክፈያነት የማዋል ዓይነት አሰራር ነው፡፡

በፍርድ ቤት ውሳኔ መያዣን ለዕዳ መክፈያነት ማዋል ያለው ጠንካራ ጎን መያዣን ለዕዳ መክፈያነት በሚሸጥበት ግዜ ሂደቱ በፍርድ ቤት ክትትል እና ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ስለሚፈፀም ለእዳ መክፈያነት የተያዘው ንብረት ተሸጦ በዕዳ ከሚጠየቀው ገንዘብ በላይ ባወጣ ግዜ ቀሪው ገንዘብ ለመያዣ ሰጪው(ለባለ ዕዳው) እንዲመለስለት የሚፈቅድ አሰራር ስለሆነ ከባለዕዳው መብት አኳያ ሲታይ ጠቃሚ አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር በፍርድ ቤት የማለፍን ግዴታ ያለበት በመሆኑ በፍርድ ቤት ለማለፍ የሚጠይቀውን የገንዘብ ወጪ ሆነ የግዜ ብክነት ስለሚያስከትል ባለሃብቱ በወቅቱ ከባለ ዕዳ የሚጠይቀውን ሃብት እንዲያገኝ የማያስችል ነው፡፡

መያዣ ተቀባዩ በመያዣነት የያዘውን ንብረት ከፍርድ ቤት ውጭ ሸጦ ለዕዳ መክፈያነት የሚያውልበት አሰራር (Power of sale foreclosure) የሚባለ ሲሆን ይህ ዓይነት የመያዣነት ለዕዳ መክፈያ ማዋል መያዣ ተቀባዩ ለመያዣ ሰጪው (ባለ ዕዳው) ዕዳ የመክፈያው ግዜ ማለፍን እና እንዲከፍለው ማስጠንቀቅያ በመስጠት በማስጠንቀቅያ በተገለፀ ግዜ ውስጥ ዕዳ ከፋዩ ዕዳውን ሳይከፍል ሲቀር በመያዣነት የተያዘውን ንብረት ሸጦ ለዕዳ መክፈያነት የሚያውልበት አሰራርን የተከተለ የመያዣ ንብረት ለዕዳ መክፈያነት የማዋል ዓይነት ነው፡፡

ይህ ዓይነት አሰራር ባንኮች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት እየተተገበረ ያለ አሰራር ነው፡፡

መያዣ ተቀባይ በመያዣነት የያዘውን ንብረት ከፍርድ ቤት ውጭ ሽጦ ለዕዳ መክፍያነት ማዋል ያለው ጠንካራ ጎን በፍርድ ቤት ለማለፍ የሚጠየቀውን ገንዘብና ግዜ የሚቆጥብ በመሆኑ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን ይህ አሰራር ከባለ ዕዳው የንበረት ባለ መብትነት አንፃር ስታይ በህግ በተቋቋመ ሌላ ሶስተኛ ወገን የሚመራና ዕልባት የሚያገኝ ባለመሆኑ በተለይ በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በተለያዩ ምክንያቶች ዕዳው ሳይሸፍን በቀረ ግዜ ባለዕዳውን በከፍተኛ ደረጃ ቀሪው ዕዳ በመያዝነት ካስያዘው ንብረት ውጭ ባለ ሃብቱ እንዳይገባ ለመከልከል ክስን ወደ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሽያጭ ሂደቱ ለማሰናከል እንዲጥር የሚጋብዝ አሰራር ስለሆነ የዚህ ዓይነት ድክመት የሚታይበት አሰራር ነው፡፡ እነዚህ የመያዣን ለዕዳ መክፈያ ማዋል ዓይነቶች ካለባቸው ጠንካራና ደካማ ጎን አንፃር ስታዩ እንደሌላው አሰራር ሁሉ የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን ያላቸው ሲሆኑ ኢትዮጵያ እየተከተለችው ያለ የፎርክሎዠርና አሰራር ከፍርድ ቤት ውጭ በመያዣበት የተያዘውን ንብረት ሽጦ ለዕዳ መክፈያነት የማዋል አሰራር ላለፉት 40 ዓመታት ስትከተለው የቆየችውን ክስን አጣርቶ የባለ ሃብትነትን እና የባለዕዳነትን መብትና ግዴታ በውሳኔ ከመስጠት ባሻገር የአፈፃፀም ስነ-ስርዓት ሰፋ ባለመልኩ በህግ በመያዣነት የተያዥነት የተያዘውን ንብረት ለፍርድ መስፈፀምያ የሚውልበት አሰራር በህግ በማሻሻል ሲሆን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በቀዳሚነት የወጣውን ኣዋጅ ቁጥር 65/89 ሆነ ይህንን ኣዋጅ በመሻር የወጣው ኣዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/97 በመደንገግ ነው፡፡ የዚህን አሰራር አስፈላጊነትና ወቅታዊነት በሚከተለው ሁኔታ በኣዋጅ ቁጥር 97/90 መግብያ ላይ ያለ ሲሆን ይሄውም፡፡ በባንኮች በዋስትና የተያዙ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች እንዲሸጡ በፍርድ ቤት ክስ ኣቅርቦ ለማስወሰንና ውሳኔውንም ለማስፈፀም የሚወስደው ጊዜ በጣም ረጅም በመሆኑ፡- በቁጠባ ሂሳብ መልክ ህዝብ የሰበሰቡትንና ከተለያዩ ምንጮች ያገኙትን ገንዘብ በማበደር የሚገኘው የወለድ ገቢ የሚተዳደሩ ባንኮች ስራ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማሳደሩ፡- ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ኣመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ባንኮች ለተያየዩ የንግድና የልማት እንቅስቃሴ የሚሰጣቸው ብድሮችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመሰብሰብ እንዲችሉና ለወደፊቱ ጥሩ የንግድ አሰራር ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ለባንክ ብድር በመያዣ የተሰጠ የሚያንቀሳቅሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ሽያጭ በሚመለከት በስራ ላይ ያሉትን ሕጎች ማሻሻልና አዲስ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፡፡ በኣዋጅ መግብያ ላይ እንደተገለፀው ባንኮች ይህ ኣዋጅ ከመውጣቱ በፊት የነበረውን የብድር አሰባሰብ አሰራር ተከትለው ይሰሩ ቢባሉ ውጤቱ አገሪቱ እየተከተለችው ያለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚጎዳ በመሆኑ ይህን ሁለት ዓይነተ አሰራር መከተሏ አግባብነት ያለው ነው፤፤ ስለሆነም ኢትዮጵያ በፍ/ቤት የመሸጥንና በባንክ የማሸጥን ስርዓት በመከተል የምዝገባው ስርዓትና መዝገቡን ሁለት እንዲሆን የተደረገ አሰራር የምትከተል መሆኗ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

## የመወያያ ነጥቦች

1.ደንበኛ ገብያተኛ (good will) ምንድን ነው? የደንበኛ ገብያተኛ የገንዘብ ጥቅም (Value) የሚወሰነው ምንድን ነው?

2.አቶ ዘመኩን የተባለ የፒኮክ ጫማ መሸጫ መደበር ከፍቶ ላለፉት 5 ዓመታት ሲነግድ ከቆየበት መደብሩ አጠገብ ወ/ሮ ሂወት ተመሳሳይ የፒኮክ ጫማ መሸጫ መደብር ብትከፍት አቶ ዘመድኩን በተገቢ ያልሆነ ውድድር ክስ ሊመስርትባት ይችላልን? ለምን?

3.የቀበሌ 20 ነዋሪዎች ኣግኣዚ የእቁብ ማህበር ቢመሰርቱና በተመሳሳይ ሁኔታ የቀበሌ 19 ነዋሪዎች ኣግኣዚ የእቁብ ማግበር ቢመሰርቱ የቀበሌ 20 ነዋሪዎች በቀበሌ 19 ነዋሪዎች ላይ ያልተገባ ውድድር ክስ መመስረት ይችላሉን ? ለምን?

4.አቶ በቀለ የተባለ እውቅ የመንደሩ ነጋዴ በመንደሩ ሌላ ኣቶ በቀለ የሚባል ነጋዴ መኖሩን ቢሰማ ባለተገቢ ውድድር ክስ ማቅረብ ይችላልን? ለምን?

5.በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 41(1) (2) እና ን/ህ/ቁ 158 መካከል መጣረስ ኣለን? ይህን የንግድ ህግ ድንጋጌ የህገ-መንግስቱን ይዘት ስለሚፃረር በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 9(1) መሰረት መሻር ያለበት ድንጋጌ ነው ብሎ መከራከር ይቻላልን? ለምን?

6.ከንግድ ምልክት ጀርባ ያሉ ፖሊሲዎች ምንና ምን ናቸው?

7.በአንድ ግዙፍነት ያለው የሚንቀሳቀስ ንብረት የንገድ ምልክት፣ የፓተንትና የቅጅ መብቶች መቀላቀል ሊከሰት ይችላልን? እንዴት?

8.የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚያሰኛቸው መብቶች ምንድን ናቸው?

9. ንግድ ምልክት ጥሰት መፍትሂዎች (Remedies) ምንድን ናቸው?

10.የንግድ ምልክት ጥምች ምንድን ናቸው?

# 3. የንግድ ማህበራት

## 3.1. ስለንግድ ማህበራት በጠቅላላ

የንግድ ማህበራት እድገት ከአገሮች የኢኮኖሚ እድገት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው፡፡ የትሳሰሩ ሰንሰለት የሚጀምረው በግለሰብ ደረጃ ንግድን ከማካሄድ ሲሆን በተደራጀ መልክ እስከ ማስኬድ የሚዘልቅ ነው፡፡ ይህ የተለያየ ደረጃዎችን እያለፈ አሁን ወዳለንበት ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች (Transnational corporations) እንደ ኣሸን የፈሉበት ዘመነ ግለባላይዘሽን የደረሰው የንግድ ማህበራት አደረጃጀት ግዙፍነትና እነዚህን ለማስተዳደር የወጣው ህግ ስንመለከት ወደ አገራችን ለመጀመርያ ግዜ 1884 ዓ.ም የገባውን “Franco - Ethiopian Rail way company” ብንወስድ እስከተጠቀሰው ጊዜ ኢትዮጵያ ኩባንያ የሚባል ሆነ የንግድ ማህበራት ህግ እንዳልነበራት ከታሪክ ፀሃፍት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ኩባንያ በ1905 የተከፈተው አብሲንያ ባንክ ሲሆን ይህም ራሱን ችሎ ሳይሆን የግብፅ ብሄራዊ ባንክ ቅርንጫፍ በመሆኑ የተከፈተ ነበር፡፡ ለመጀመርያ በኢትዮጵያ የተከፈተው ኢትዮጵያ ባንክ (Bank of Ethiopia) በ1931 ዓ.ም ሲሆን ቀጥሎ የኢትዮጵያ እርሻና ንግድ ልማት ኩባንያ በጥቂት የገዢ መደብ መሰራችነት ሊቋቋም ችሏል፡፡ በአገራችን የንግድ ማህበራት ህግ ለመጀመርያ ጊዜ የወጣውም በ1933 ዓ.ም ነበር ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኣገራችን የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ በተለይ ደግሞ በተደራጀ መልኩ በንግድ ማህበር መቋቋም ከጀመረ ቅርብ እንደሆነና ከነበረው ንጉሳዊ ኣገዛዝ በኃላም የደርግ መንግስት ይከተለው በነበረ የእዝ ኢኮኖሚ ምክንያት የነበሩት ኩባንያዎች በመንግስት ተወርሰው በመቆየታቸው ሂደቱን ዘገምታዊ እንዲሆን እንዳደረገው ነው፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ ባለው ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ በመፈጠሩ ተደራጅቶ የንግድ ስራ የመስራት መብት እንደገና ሊያንሰራራ ችሏል፡፡ በተደራጀ መንገድ የንግድ ስራን የማከናወን መብት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስትና ይህን መሰረት በማድረግ ከወጡት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ኣንፃር ስንመለከተውም

የንግድ ማህበር ሰዎች በግላቸው ከመነገድ ይልቅ ለአንድ የኢኮኖሚያዊ ዓላማ በመደራጀት በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት የሚያስችላቸው የገንዘብ አቅምንና የገበያ ማስፋፋትን መሰረት በማድረግ በተሻለ የንግድ ስራ የተሻለ ገቢ ለማግኘት አቅደው የሚመሰርቱት ናቸው፡፡ ይህ የመደራጀት መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 31 ላይ “ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም ኣግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በህገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡” በማለት ስለተደነገገ “ማንኛውም ሰው” የሚለው የህገ-መንግስቱ ሃይለ ቃል የሚያመለክተው የተፈጥሮ ሰውንና በሕግ ሰውነት የተሰጣቸው የንግድ ማህበራት መደራጀትን ሲገልፅ “ለማንኛውም ዓላማ” የሚለው ደግሞ ለንግድ ስራም ጭምር በንግድ ማህበር የመደራጀትን መብት የሚፈቅድ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ በንግድ ማህበራት የመደራጀት መብት በህገ-መንግስቱ 41(2) “ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደርያውን ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው”

www.abyssinialaw.com

ከሚለው ህገ-መንግስታዊ መብት አንፃር ያየነው እንደሆነም ዜጎች አዋጪ ነው ባሉት የንግድ ማህበር መርጠው እንደመተዳደርያ ስራቸው ሊወስዱት የሚያስችል ህገ-መንግስታዊ መብት ያላቸው መሆኑን እንድንረዳ የሚያስችለን ነው፡፡

በአንድ አገር የኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት የንግድ ማህበራት አገራችን እየተከተለችው ላለው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራተጂ ስኬታማነት የሚጫወቱት ሚናም በእጅጉ ከፍተኛ ነው፡፡ ዜጎች በተናጠል ቢሰሩዋቸው የማዋእለ ንዋይ፣ የማስተዳደር ዓቅማቸውን የሚፈታተኑ የንግድ ስራዎች ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማና የወደፊት በዘርፉ ተስማርተው በመስራት የመበልፀግ ራእይ ካላቸው ሰዎች ጋር ተደራጅተው በተለያየ የኢኮኖሚ ዘርፍ በመስራት ራሳቸውን ጠቅመው በአገራዊ ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ማረጋገጥ ሂደት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ የሚያስችል ዘመናዊ አሰራር ስለሆነ በስፋት ልንሰራበት የሚያስችለን የአደረጃጀት ስርዓት ነው፡፡ አገራችን ከእዝ ክፍለ ኢኮኖሚ ተላቃ ወደ ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲና እስትራተጂ ትግበራ ከገባች ወዲህ በንግድ ህጉ ባሉ ድንጋጌዎችና የገበያ ስርዓቱን መሰረት በማድረግ በወጡ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና የባንክና ኢንሹራንስ አሰራሮች ታግዘው እግጅ በርከታ አክስዮን ማህበራትና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት ተመስርተው የአገሪቱን ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማረጋገጥ ሂደት ላይ የመሆናቸው ሚስጢር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራተጂ ለውጥ ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ በንግድ ማህበራት ተደራጅቶ መስራት በህገ-መንግስቱና ከዚያ በታች ባሉ የአገራችን ህጎች ጥበቃ የተሰጠው መብት በመሆኑ እየተከተልን ያለውን ሁሉም ዜጎች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ፈጣንና ዘለቂ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲና ስትራተጂ እውን በማድረጉ ሂደት በመስርያነት ልንጠቀምባቸውና ስርዓት ባለው መልኩ ሊመሩ እንደሚገባ በውል ልንገነዘብ ይገባል፡፡

በአገራችን ያለውን የንግድ ማህበራት አመዳደብ (classification) ሌሎች አገሮች እየተከተሉት ካለ አመዳደብ አንፃር ስናየው አገሮች እስካሁን እየተከተሉት ያለው አሰራር አንድን ማህበር የንግድ ማህበር ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመለየት ሁለት አካሄዶችን የሚከተል ነው፡፡ ይሄውም አንዳንዶቹ በተቋቋሙበት ዓላማ (objective) መሰረት ለንግድ ስራ የተቋቋመ ከሆነ የንግድ ማህበር ነው ብለው ሂደቱ በንግድ ህግ እንዲገዛ ሲደረግ ከዚህ ውጭ የሆነ ስራ ለመስራት የተደራጀ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ለንግድ ስራ ያልተደራጀ ማህበር (non-commercial organization) ብለው በመፈረጅ በሌሎች የአገሪቱ ህጎች እንዲገዛ የሚያደርግ አሰራርን የሚከተሉ ናቸው፡፡ ለዚህ በምሳሌነት ልትጠቀስ የምትችል ቤልጂም ስትሆን ሌሎች አገሮች እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች ደግሞ የንግድ ማህበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ወይም ፎርም መሰረት በማድረግ የሚለዩበት አሰራር እንጂ ለንግድ የተቋቋመ (commercial) ወይም ለንግድ ያልተቋቋመ (non-commercial) የሚል ክፍፍል የማያደርጉ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የኢትዮጵያን የንግድ ማህበራት አመዳደብ እንዴት እንደሚለይ ስንመለከት ህጋችን የንግድ ማህበራትን ለንግድ የተቋቋመ (commercial) እና ለንግድ ያልተቋቋመ (non-commercial)

በሚል ምድብ የሚከፍል አካሄድን የሚከተል ነው፡፡  ይህ የፈረንሳይ የንግድ ማህበራትን ኣመዳደብ የሚከተለው ህጋችን በን/ህ/ቁ 10 ላይ አንድ የንግድ ማህበር ለአንድ የተለያዩ የሚታወቅ የንግድ ስራ የተደራጀ ከሆነ የንግድ ማህበር ተብሎ እንደሚወሰድና የተደራጀው በኣክስዮን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩትን ስራዎች አካሄደ አላካሄደ የንግድ ማህበር ተደርጎ የሚወሰትበትን አሰራር የሚከተል ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ማህበር የንግድ ማህበር ነው ብሎ ለመፈረጅ የተደራጀበት ዓላማ በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን ተግባራት ለማከናወን ከሆነ ከተቋቋመበት ዓላማ (objective) ተነስተን የንግድ ማህበር ነው ስንለው በሌላ በኩል ግን የተቋቋመበት ዓላማ በን/ህ/ቁ 5 ያሉትን የንግድ ተግባራት ለመፈፀም ባይሆንም የተከተለው ፎርም (form) በኣክስዮን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር እስከሆነ ድረስ ማህበሩ የንግድ ማህበር ነው ተብሎ እንደሚወሰድ የሚደነግግ ህግ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበት የሽርካ ማህበር የንግድ ማህበር ለመባል በን/ህ/ቁ 5 ካሉት ዝርዝር ተግባራት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅበት ሲሆን የንግድ ህጉ እንደምንጭ የሚወሰደው የፈረንሳይ ህግ ግን ከዚህ ለየት ባለ መልኩ የተቋቋመበት ዓላማን መሰረት ሳያደርግ ሁሌ ልክ በኛ አገር ን/ህ/ቁ 10(2) ለኣክስዮንና ሃላፊነቱ ለተወሰነ የግል ማህበር የተሰጠው የህግ ሽፋን ለሁለት ዓይነት ሃላፊነት ላለበት ሽርካ ማህበር (General and Limited) የህግ ሽፋን የሚሰጥ ነው፡፡ ከፈረንሳይ ኣካሄድ ለየት ባለ መልኩና ከኢትዮጵያ ን/ህ/ቁ 10(1) ኣካሄድ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚደነግግ የጀርመን ህግ ሲሆን በተለይ ደግሞ ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበትን ማህበር በተመለከተ የአገራችን ንግድ ህግ የጀርመን ህግን አካሄድ የሚከተል ነው፡፡

በአገሮች የንግድ አሰራር እንደዚህ ያለ ኣመዳደብ መከተል የሚያስፈልግበት ምክንያት የንግድ ማህበሩን ከሌላው ማህበር በመለየት የንግድ ሂደቱን ስርዓት ባለው መንገድ ለመምራትና ሂደቱ ኣገሪቱ ለነደፈችው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራተጂ ስኬት በመሳርያነት እንዲያገለግልና የሶስተኛ ወገኖችን መብት በማስጠበቁ ሂደት የራሱ የሆነ የቁጥጥርና ድጋፍ ስርዓት እንዲኖረው ለማስቻል ነው፡፡  ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ኢትዮጲያም ሆነች ፈረንሳይ፣ ጀርመንና ቤልጂም ለሰወስተኛ ወገን የማሳወቅ (publicity) ኣሰራርንና የንግድ ምዝገባ (Commercial registry) ኣሰራርን ተከትሎ እንዲሄድ የሚያደርግ ኣሰራር በመከተል ስርዓት ባለው መንገድ እንዲመራ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ አንድ ሰው በንግድ መዝገብ ከተመዘገበ ነጋዴ ነው ተብሎ የመገመት መብት ያለው መሆኑን ን/ህ/ቁ 117(1) ሲደነግግ ይህን ሳያደርግ የንግድ ስራ ሲያከናውን ቢገኝ ግን ን/ህ/ቁ 115 የወንጀልና የፍ/ብሄር ሃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚደነግግ ህግን ተከትሎ በወንጀል ሃላፊነት ወ/ህ/ቁ 434 እና ኣዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 46 ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፡፡ የፍ/ብሄር ሃላፊነትን  በሚመለከትም ን/ህ/ቁ 118(1) መሰረት በማድረግ በንግድ መዝገብ ሳይመዘገብ የንግድ ስራ ሲያከናውን የተገኘ ሰው

ለስራው ስራ እንደ ነጋዴ ተወስዶ ሃላፊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በሌላ አነጋገር በሶስተኛ ወገን ላይ ያደረሰው ጉዳት ካለ ከውል ውጭ በሆነ ሃላፊነት ተጠያቂ በማድረግ ለደረሰው ጉዳት መክፈል ያለበትን ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ነጋዴ በመሆኑ ለመንግስት መክፈል ያለበትን ግብር ላለመክፈል ሳይመዘገብና ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ እየሰራ ቢገኝ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለበትን ግብር ገቢ እንዲያደርግ ማስገደድ ይቻላል፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊወሰድ የሚችለው አስተዳደራዊ እርምጃ በአዋጅ ቁጥር 67/89 አንቀፅ 21(2) መሰረት ንግዱን እንዲዘጋ ማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ የንግድ ማህበራት አጠቃላይ ገፅታን ስንመለከት የራሳቸው የሆነ ህጋዊ አደረጃጀትና ተልእኮ ያላቸው ሆነው ህጋዊ ሰውነት ለማግኘትና ወደ ገበያው ለመግባት የምዝገባ፣ ፈቃድና ማስታወቅ ስራዎችን የሚጠይቁ ጠንካራ የአገር ኢኮኖሚ በመገንባት ሂደት የተበታተነን መዋእለ ንዋይ አሰባስቦ በተደራጀ መልክ የልማት ስራን ለማከናወን የሚያስችሉ መሳሪያዎች ሲሆኑ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተደራጅቶ የንግድ ስራ የማከናወን መብት በህገ-መንግስቱና ከዚያ በታች ባሉ ህጎች የተረጋገጠ መብት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

## 3.2 ሽርካ ማህበር

### 3.2.1 የሽርካ ማህበር አጠቃላይ ገፅታ

"የሽርካ ማህበር ውል ማለት ሁለት ወይም ብዙ ሰዎች መዋጮ አዋጥተው በአንድነት እና በህብረት የኢኮኖሚ ተግባር ያለው ስራ ለመስራትና ከሚገኘው ትርፎም ሆነ ከሚመጣው ዕዳ ተካፋይ ለመሆን የሚስማሙበት ውል ነው፡፡" በማለት ን/ህ/ቁ 211 ተርጉም የሰጠው ሲሆን በማነፃፀርያነት ያገለግለን ዘንድ አንድ Professor M.C.Kuchhal የተባሉ ህንዳዊ የዘርፉ ተመራማሪ የሰጡትን ትርጉም የወሰድን እንደሆነ "partnership is the relation between persons who have agreed to share the profit of a business carried on by all or any of them acting for all" (P.295) በማለት ተርጉመውታል፡፡ ከነዚህ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጋራ የሆኑ ሓሳቦች (common elements) ያሉዋቸውና የተለያዩበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ነው፡፡

በን/ህ/ቁ 211 መሰረት አንድ የሽርካ ማህበር ለማቋቋም

- ❖ ውል መኖር አለበት፣
- ❖ መዋጮ ማዋጣት፣
- ❖ በአንደነት እና በህብረት የኢኮኖሚ ተግባር መስራት፣
- ❖ ትርፍም ሆነ ዕዳ ለመክፈል መስማማትን የሚጠይቅ ሲሆን ፕሮፌሰር M.C.Kuchhal በሰጡት ትርጉም ደግሞ
    - o There must be a contract,
    - o Between one or more persons,
    - o With the objective of sharing profits,

o The business must be carried on by all or any of them caring for all. የሚሉ ሃሳቦችን ይዟል፡፡ እነዚህን ስናነፃፅር የዘርፉ ተመራማሪ ለሽርካ ማህበር በተሰጡት ትርጉም ላይ ስለመዋጮና ዕዳ በሚኖርበት ጊዜ ስለሚኖረው አከፋፈል የሚለው ነገር የለም፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የታወቀ ነው ከሚል ወይስ በሌላ ምክንያት? ክርክር ሊያስረሳ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ የአዘጋጁ አስተያየት ግን መብትና ግዴታ ተነጣጠለው የማይሄዱ በመሆናቸው መዋጮ ማዋጣትም ሆነ ዕዳ ሲኖር የመክፈል ግዴታ በህንድ ህግም አለ የሚል ነው፤፤

በአገራችን የንግድ ማህበራት ህግ ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ካለው የሽርካ ማህበር በስተቀር በሌሎቹ የሽርካ ማህበራት የተለያዩ የሽርካ ማህበር ኣባላት ያሉ ስለመሆኑ የሚገልፅ ድንጋጌ የለም፡፡ M.C.Kuchhal በፃፉት መፅሐፍ ላይ እንደሚታየው ግን የተለያዩ የሽርካ ማህበር ኣባላት እንዳሉ ሲሆን እነርሱም

1. ተሳታፊ (active or actual) የሽርካ ማህበር ኣባል የዚህ ዓይነት ኣባል በሽርካ ማህበሩ የዕለተ ዕለት እንቅስቃሴ ተካፋይ የሚሆንና ኣባል ስለመሆኑ ለህዝብ በማስታወቅያ የወጣና ከማህበሩ በሚሰናበትበት ጊዜም ከስንብቱ በኃላ ለሚመጣ የሽርካ ማህበሩ ዕዳ ተጠያቂ ላለመሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ከሽርካ ማህበሩ መውጣቱን ለህዝብ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት የሽርካ ማህበር ኣባልነት ነው፡፡
2. ስዉር (Sleeping or dormant partner) የሚባል ገንዘቡን ብቻ ወደ ሽርካ ማህበሩ በማስገባት ከተገኘው ትርፍም ሆነ ኪሳራ ከድርሻው ዝቅ ያለ ገንዘብ እየተከፈለው ግን ደግሞ ኣባልነቱን ለህዝብ ሳያሳውቅ የሽርካ ማህበር ኣባል ሆኖ የሚቀጥል ነው፡፡
3. ዝምተኛ (Silent partners) የዚህ ዓይነት ኣባል ከሽርካ ማህበሩ ኣባላት ጋር በሚያደርገው ስምምነት በሽርካ ማህበሩ ኣስተዳደራዊ ስራ ሳይሳተፍ ግን ደግሞ በዕለተ ዕለት የንግድ ማህበሩ ስራዎች እየተሳተፈ የተገኘ ትርፍና ኪሳራ ከሌሎች አባላት ጋር የሚከፈልና ለሶስተኛ ወገኖች ለሚነሳ የይከፈለኝ ጥያቄ ሃላፊነት የሚወስድ የሽርካ ማህበር አባል ነው፡፡
4. ለትርፍ ብቻ ኣባል የሆነ (partner in profit only) የዚህ ዓይነት ኣባል በሚገኘው ትርፍ የተወሰነውን መጠን ከሌላው የሽርካ ማህበሩ ኣባል ለመውሰድ የተስማማና ሽርካ ማህበሩ ለሚያጋጥመው ኪሳራ ተጠያቂ ያልሆነ ግን ደግሞ በህንድ የንግድ ማህበራት ህግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የሽርካ ማህበር (Limited partnership) ባለመኖሩ ሶስትኛ ወገኖች ለሚያነሱት የመብት ጥያቄ ግን ሃላፊነት የሚወስድ የሽርካ ማህበር ኣባል ነው፡፡
5. ንኡስ የሽርካ ኣባል (sub partner) የሽርካ ማህበሩ ኣባል ከሌላ የውጭ ሰው ጋር ከሚገኘው ትርፍ ላይ ለመከፈል ብቻ የሚስማማበትና በሽርካ ማህበሩ ላይ ምንም ዓይነት መብትም ሆነ ሃላፊነት የሌለው ዓይነት ኣባል ነው፡፡
6. በአባል ሳይሆን ኣባል የመሰለ (partner by estoppels or holding out) የዚህ ዓይነት ሽርካ በማህበሩ የሽርካነት ግንኙነት ሳይኖረው ለሶስተኛ ወገኖች በማህበሩ ሽርክና ኣለኝ ብሎ በመናገሩ፣ በመፃፉ ወይም በድርጊት ከሳየና በሶስተኛ ወገኖች ላይ በማህበሩ

ምክንያት ጉዳት ከደረሰባቸው እንደ ሌሎቹ የሽርካ ማህበሩ አባላት ተጠያቂ የሚሆን ዓይነት አባል ነው፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በኢትዮጵያ ያለው የሽሪኮች ዓይነት በህንድ ካለው የሽርካ ዓይነት ያነሰ ለመሆኑ ግልፅ ቢሆንም እዚህ ላይ ሊያነጋግር የሚችለው ነጥብ ከላይ በተገለፀው መንገድ ሽርኮች በመሆናቸው ሃላፊነት አለባቸው የሚል ክርክር ቢነሳ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳቱን ማስተናገድ ያለባቸው በንግድ ህጉ መሰረት ወይስ በሌላ የፍ/ብሄር ህግ የሚል ሲሆን እዚህ ላይ እንደመፍትሄ ሐሳብ መውሰድ ያለበት በንግድ ህጉ ባልተሸፈኑ ግንኙነቶች መገዛት ያለባቸው እንደሌላው ውል ወይም ከውል ውጭ ሃላፊነት መሆን አለበት የሚል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት ሶስት ዓይነት የሽርካ ማህበራት ያሉ ሲሆን የነዚህን ማህበራት አጠቃላይ ገፅታ አጠር ባለ መልኩ ስንመለከት፤-

1. ተራ የሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 227-270)
   - በጥቂት አባላት የሚመሰረት ሽርካ ማህበር ነው፡፡
   - የንግድ ማህበር ላይሆን ይችላል፡፡
   - በን/ህ/ቁ 5 የተዘረዘሩትን ተግባራት ላያከናውን ይችላል፡፡
   - በስራ ላይ የመዋሉ አጋጣሚ ዝቅተኛ ነው፡፡
   - የአባላቱ ሃላፊነት ያልተወሰነ ነው፡፡
   - የአባላቱ ጥቅም በነፃ አይተላለፍም፡፡
2. ህብረት ሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 280-295)
   - ብዙውን ግዜ በጥቂት አባላት የሚመሰረት ነው
   - የአባላቱ ጥቅም በነፃ አይተላለፍም
   - አባላቱ ያላቸው ሃላፊነት ያልተወሰነ ነው
   - ሽርካ ማህበሩ የሚመራው በአብዛኛዎቹ የተራ ሽርካ ማህበር ህጎች ነው፡፡
3. ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለበት ሽርካ ማህበር (ን/ህ/ቁ 296-303)
   - አንድ ወይም ሁለት የማህበሩ አባላት ሃላፊነታቸው የተሰወነ ከመሆኑ ውጭ ልክ እንደ ህብረት ሽርካ ማህበር ዓይነት ማህበር ነው፡፡
   - የአባላቱ ጥም በነፃ አይተላለፍም

የነዚህ የሽርካ ማህበራት ምንነት በሚከተሉት መመዘኛዎች (criteria's) ሲታይም የሚከተሉትን ጭብጦች ይዞ እናገኘዋለን፡፡

| ተ.ቁ | የንግድ ማህበሩ ዓይነት | ሃላፊነት | የአባላቱ ጥቅም መተላለፍ | የአባላቱ ቁጥር | ህጋዊ ሰውነት | መነሻ ካፒታል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተራ ሽርካ ማህበር | ያልተወሰነ ሃላፊነት ን/ህ/ቁ 255 | በነፃ አይተላለፍም ን/ህ/ቁ 250 | > 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1) | ህጋዊ ሰውነት አለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 210(2) | 15,000 ብር |
| 2 | ህብረት ሽርካ ማህበር | ያልተወሰነ ሃላፊነት ያለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 294 | በነፃ አይተላለፍም ን/ህ/ቁ 282(1) | > 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1) | ህጋዊ ሰውነት አለው ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 286 | 15,000 ብር |
| 3 | ሁለት ዓይነት ሃላፊነት ያለው የሽርካ ማህበር | ያልተወሰነና የተወሰነ ሃላፊነት ያላቸው አባላት ያሉበት ነው፡፡ ን/ህ/ቁ 300-301 | በነፃ አይተላለፍም ን/ህ/ቁ 274(2) | > 2 <6 ን/ህ/ቁ 211(1) | ህጋዊ ሰውነት አለው ን/ህ/ቁ 286/303 | 15,000 ብር |

በሽርካ ማህበር መሰረቱ ውል ነው ሲባል በሽርካ ማህበርና ሌሎች ውሎች መካከል ልዩነት የለም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹን የወሰድን እንደሆን

- የሽርካ ማህበር እንደ ሌሎች ውሎች ባለ እዳ (debtor) እና ባለሃብት (creditor) የሚፈጥር ወይም የአንዱ መብት ሌላው ግዴታ የሚሆንበት አካሄድን መሰረት የሚያደርግ አለመሆኑና ሁሉም የሽርካ ማህበሩ አባላት ተመሳሳይ አቋም (equal footing) ያላቸው መሆኑ ከሌሎች ውሎች የሚለየው ባህሪው ነው፡፡
- ሌሎች ውሎች ተቋምን (institution) የመመስረት ባህሪ የሌላቸው ሲሆን የሽርካ ማህበር ስምምነት ግን ተቋምን ሊፈጥር የሚችል ነው፡፡
- ሌሎች ውሎች ውልን የማፍረስ ውጤት ሲኖራቸው ሽርካ ማህበር ግን ሽርካ ማህበሩን ለመመስረት የተደረሰው ስምምነት ከመፍረሱ በተጨማሪ ማህበሩም እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የሽርካ ማህበራት እንደ ሌሎቹ የንግድ ማህበራት ሰዎች በግል ማከናወን ያልቻሉትን የንግድ እንቅስቃሴ በሽርክና ተደራጅተው እውቀታቸውንና ጥሪታቸውን በማቀናጀት ለራሳቸውና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ በሆነ በኢኮኖሚው ዘርፍ በመስራት በልማት አጋርነት ሊሰማሩባቸው የሚችሉ የስራ መስኮች ናቸው፡፡

## 3.2.2 የሽርካ ማህበር አባላት መብቶችና ግዴታዎች

- ማህበሩን ለነሱ ተስማሚ በሆነ መንገድ የመመስረት
- ንብረቱንና ጥቅሙን እንደፈለጉ በጋራ ስምምነት ማስተዳደር
- በማህበሩ ጉዳይ ላይ ያልተገደበ መብት ያላቸው መሆኑ
- የትርፍ ክፍፍል ስርዓት የመወሰን (ን/ህ/ቁ 252)
- ኪሳራ ሲኖርም ይህንን የመጋራት መብትና ጥቅም ይኖራቸውል፡፡

- ✓ በህብረት ሽርካ ማህበር የሃብት ክፍፍልና የዕዳ መጋራትን በማስመልከት የሚለው የለም (ን/ህ/ቁ 284(7)
- ከሽርካ ማህበሩ ጋር ያለመወዳደር (ን/ህ/ቁ 244፣292)
- የሽርካ ማህበሩን ንብረት ለሽርካ ማህበሩ አገልግሎት እንዲውል የማድረግ (245)
- ባለሃብቶች ከሽርካ ማህበሩ የሚጠይቁትን ዕዳ የመክፈል (ን/ህ/ቁ 255፣280፣294 እና 296)
- የሽርካ ማሕበር አባላት ፈቃድ ሳታገኝ የማህበሩን ጥቅም ወደሌላ ያለማስተላለፍ (ን/ህ/ቁ 282)

## 3. 2 .3 ስለሽርካ ማህበር መፍረስና ሒሳብ ማጣራት

የማህበር መፍረስ ማለት ማህበሩ ህልውናው የሚያጣበት (Organization comes to an end) ሲሆን ይህ መፍረስ በዋናነት ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸውን የንግድ ማህበራት የሚመለከት በመሆኑ ፈረሰ ማለት የንግድ ስራን ከመስራት አቆ ወይም ታመመ እንጂ ሞተ ማለት እንደሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም የንግድ ማህበሩ ከፈረሰ በኃላ ሒሳብ የማጣራት ስራ ይካሄዳል፡፡ ይሄውም ሂሳብ አጣሪዎች (Liquidators) ድርሻ ሲሆን አጣሪዎች ስራቸውን አከናውነው እስኪጨርሱ ድረስ የንግድ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆን እንደተጠበቀ ይቆያል፡፡ ይህን ህልውናውን የሚያጣው አጣሪዎቹ የማጣራቱን ስራ ጨርሰው የተገኘው የንግድ ማህበር ገንዘብ ለባለ እዳዎች የሚከፈለው ተከፍሎ ካለቀና ቀረ ካለም በአባላቱ መካከል ተከፋፍሎና ሂደቱ ካለቀ በኋላ ነው፡፡ የንግድ ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያገኘው በምዝገባና በማሳወቅ እስከሆነ ድረስ ህልውናውም ማጣት ያለበትም በንግድ መዝገብ የነበረን የማህበሩ ስም እንዲሰረዝ በማድረግና ሶስተኛ ወገኖች ህልውናውን ያጣ መሆኑን እንዲያውቁት በማስታወቅያ እንዲገለፅ በማደረግ ነው፡፡

የማህበሩ መሰረዝ ሊከሰት የሚችለው በሶስት ምክንያቶች ሲሆን እነሱም በህግ፣ በስምምነትና በፍርድ ቤት ናቸው፡፡ አንድ የንግድ ማህበር በህግ ሊፈርስ የሚችለው የተቋቋመበትን ዓላማ ያሳካ ወይም ማሳካት የተሳነው እንደሆነ ነው፡፡ ሌላው የንግድ ማህበር በህግ እንዲፈርስ የሚደረግበት ሁኔታ ማህበሩ ሲመሰረት የተወሰነው የግዜ ገደብ በመድረሱ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የማህበሩ አባላት የመፍረሻ ጊዜው ከመድረሱ በፊት በስምምነት ጊዜውን ማራዘምና በንግድ መዝገቡ ማሻሻያ እንዳያደርጉ ይከለከላሉ ማለት አይደለም፡፡ የአንድ ንግድ ማህበር አባላት የመፍረሻ ጊዜው ከመድረሱ በፊት አስቀድመው ማህበሩ እንዲፈርስ ከተስማሙ የስምምነታቸው ቅጂ ለመዝጋቢው አካል በማቅረብና ለሶስተኛ ወገኖች በማሳወቅ የንግድ ማህበሩ እንዲፈርስም ሆነ የማጣራቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኃላ እንዲሰረዝ ለማድረግ ይችላሉ፡፡

አንድ የንግድ ማህበር በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሊወሰንበት የሚችለው የንግድ ማህበሩን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የጤና መታወክ ወይም በአባላቱ መካከል ሊያሰራ የማይችል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት መፈጠሩን ከተረዳ ማህበሩ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይሄውም ለመፍረሱ በቂ ምክንያት (good cause) መኖሩ ሲረጋገጥ የሚፈፀም ነው፡፡ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰዱ የሚችሉትም ለምሳሌ የማህበሩ አባላት በተፈጠረው አለመግባባት ውሳኔ ማሳለፍ የማይችሉ ሲሆን ወይም ማህበሩን በምግባረ ብልሹነት ማስተዳደር ከተጀመረ ለመፍረሱ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል፡፡ ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ሽርካ ማህበር መሰረቱ ውል ሆኖ በውሉ መሰረት መቀጠል ሲሳነው ወይም ዓላማውን አሳክቶ ወይም ቀደም ሲል በተገለፁ በርካታ ምክንያቶች ሊፈርስ ብሎም ሂሳቡ ከተጣራ በኃላ ሊሰረዝ የሚችል የንግድ ማህበር ነው፡፡

### 3.3 የእሽሙር ማህበር

እሽሙር ማህበር በን/ህ/ቁ 271 መሰረት ሰዎች ሌሎች ፎርማሊታዎች እንዲያሟሉ ሳይጠበቅባቸው ለአንድ ዓላማና ግብ በመስማማት ብቻ ሊመስርቱት የሚችል የንግድ ማህበር ሲሆን የሚቋቋመው ለንግድ ወይም ለንግድ ላልሆነ ስራ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌሎች አገሮች የህግ ማእቀፍ ለእሽሙር ማህበር የሚሰጠው ቦታ እንደ ኢትዮጵያ የንግድ ህግ የንግድ ማህበር ነው በሚል ሳይሆን በን/ህ/ቁ 271 ላይ እንደተገለፀው "…. ማህበርተኞቹ እንደፈቃዳቸው የውላቸውን ሁኔታዎች ወስነው ያቋቋሙት ማህበር" ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ ለምሳሌ በጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣልያን እሽሙር ማህበር እንደ ሰዎች ሰብሰብ እንጂ እንደ አንድ የንግድ ማህበር የሚታይበት ሁኔታ በህጋቸው የለም፡፡ እሽሙር ማህበር ከኢትዮጵያ ህግ አኳያ ሲታይ የተለየ ወይም አጠቃላይ ስራ ለመስራት ሊቋቋም የሚችል ሲሆን ከጊዜ አንፃርም ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ ሊቋቋም የሚችል የንግድ ማህበር ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የእሽሙር ማህበር ህግ ጋር የሚመሳሰለው የቤልጅም ህግ ሲሆን በዚች አገር ከ1873 ዓ.ም ጀምሮ እሽሙር ማህበርን እንደ ንግድ ማህበር እውቅና የሚሰጥ ህግ አለ፡፡ የእሽሙር ማህበር ምስረታ በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ ህግ የለም ይህም ማለት ውሉ በፍ/ህ/ቁ 1681 መሰረት በቃል፣ በተለመዱ ምልክቶች ሊመሰረት ይችላል ማለት ነው፡፡ ውሉ በፅሁፍ የማይደረግ በመሆኑ በሰዎቹ መካከል ክደት ቢፈጠር መብትን ለማስጠበቅ ከፍተኛ የማስረዳት ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሌላው ግራ የሚያጋባው ነገር ቢኖር ግን በን/ ህ/ቁ/ 275(4) ላይ "የስራ አስኪያጁ ስልጣን በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ ይወስናል ይህን ስልጣን የሚወስነው ቃል ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች መቃወምያ ሊሆን አይችልም" ሲል የሚደነግግ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ብቻም አይደለም ን/ህ/ቁ 276(2) እንደዚሁ "ስራ አስኪያጅ ያልሆኑ ማህበርተኞች ለማህበሩ ዕዳዎች ተካፋይ የሚሆኑት በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ በተወሰነው መጠን ብቻ ነው" ይላል፡፡ ይህን ከን/ህ/ቁ 214 ጋር በማገናዘብ ስናየው የእሽሙር ማህበር ምስረታ በፅሁፍ የመሆን ጉዳይ የምርጫ ጉዳይ ነው ሊባል

ይችላልን? የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ የሚያረገን ሲሆን ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ምስረታው በማህበር መመስረቻ ፅሁፍ (memorandum of association) ነው ከተባለ ይህ በንግድ መዝገብ ሊመዘገብና ለሶስተኛ ወገኖች የማሳወቅ ግዴታን ሊያስከትል ኣይችልምን? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው፡፡ እንደ አዘጋጁ አስተያየት ከሆነ ዛሬ ስለ እሽሙር ማህበር መመስረቻ ፅሁፍ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች ከኣርቃቂው ቅደም ተከተልና ወጥነት አለመኖር የመነጨ እንጂ የእሽሙር ማህበር ግንኙነት በፅሁፍ እንዲሆን የሚያስገድድ ሁኔታ ስላለ ኣይደለም የሚል ነው፡፡ ለዚህም እንደመነሻ ሊወሰድ የሚችለው ከኢትዩጰያ ንግድ ህግ ተመሳሳይነት ያለው የቤልጅም ህግ ስለእሽሙር ማህበር ምስረታ ፎርም ሆነ ለሶስተኛ ወገኖች ስለማስተዋወቅ የሚለው ነገር ኣለመኖሩ ነው፡፡ ሌላው እሽሙር ማህበር እንደሌሎቹ የንግድ ማህበራት ህጋዊ ሰውነት የሌለውና በማህበር ስም ንብረት ለመያዝም ሆነ ለመክሰስም ለመከሰሰም የማይችል ኣባላቱ በን/ህ/ቁ 273 መሰረት ባወጡት መጠን የግል ንብረታቸው የግል እንደሆነ ተደርጎ የመውሰድ ኣካሄድን የሚከተል ነው፡፡ የእሽሙር ማህበር ህልውና ለሶስተኛ ወገኖች የተጋለጠ ከሆነ ማህበሩ እሽሙር ማህበር መሆኑ ይቀርና በን/ህ/ቁ 272(4) መሰረት እንደ ሽርካ ማህበር ተወስዶ ሶስተኛ ወገኖች መብታቸውን ለማስጠበቅ በማህበሩ ላይ ክስ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡ የእሽሙር ማህበር ኣስተዳዳሪ እንዳልተጋለጠ ወኪል (Undisclosed agent) በስሙ ስለሚሰራ ለማንኛውም የመብት ጥያቄ በግሉ ሃላፊ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበለትን ዕዳ ከከፈለ በኋላ ከማህበርተኞቹ ገንዘቡን እንዲመልሱለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት እሽሙር ማህበር

- አብዛኛው ጊዜ በጥቂት ሰዎች የሚመሰረት
- በአብዛኛው ለተወሰነ ዓላማና ጊዜ የሚመሰረት
- ህጋዊ ሰውነት የሌለው (ን/ህ/ቁ 210(2)፣ 232(2)
- የኣባላቱ ጥቅም በነፃ ሊተላለፍ የማይችል(ን/ህ/ቁ 274(2)
- ማህበሩ ለሶስተኛ ወገኖች በጋህድ የማይታይ
- የኣባላቱ ሃላፊነት የሚወሰነው በመመስረቻ ፅሁፍ መሰረት ሆኖ የተወሰነ ሃላፊነት ያላቸው ናቸው፡፡ (ን/ህ/ቁ 276 (2) )
- የኣባላቱ ብዛት ከሁለት የበለጠ ከስድስት ያነሰ መሆን ያለበት(ን/ህ/ቁ 211(2)
- የመነሻ ካፒታል 15,000 ብር የሆነ የንግድ ማህበር ነው፡፡

በኢትዮጵያ እሽሙር ማህበር ላይ የመክሰር ፍርድ የማይሰጥበት ምክንያት ህጋዊ ሰውነት የሚሰጠው (separate legal personality) ስለሌለው ነው፡፡ በአንድ አንድ እንደ ጀርመንና ኣሜሪካ ባሉ አገሮች ግን የሽርካ ማህበር ህጋዊ ሰውነት የሚይሰጣቸው ባይሆንም በእንደዚህ ያሉ የንግድ ማህበራት ላይ ግን የመክሰር ፍርድ ሲሰጥባቸው ይስተዋላል፡፡ በእንግሊዝ ህግ ደግሞ ሽርካ ማህበር ህጋዊ ሰውነት የማይሰጠው በመሆኑ የመክሰር ፍርድ ኣይሰጥበትም፡፡

በፈረንሳይ ህግ ደግሞ በሽርካ ማህበር ላይ የመክሰር ፍርድ የሚሰጠው የአባላቱን መክሰር ሳይጨምር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ያለው አሰራር አንድ ከእሽሙር ማህበር በስተቀር ያለ የንግድ ማህበር የሚጠበቅበትን ዕዳ መክፈል ካልቻለ በን/ህ/ቁ 1156 መሰረት የመክሰር ውሳኔ የሚሰጠው በን/ህ/ቁ 1158(1) (2) ማስጠንቀቅያ ከተሰጠው በኋላ አባላቱ ዕዳውን ካልከፈሉ አብረው ከንግድ ማህበሩ ጋር የመክሰር ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

## 3.4 አክስዮንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

አክስዮን ማህበር ግለ ሰቦች በግላቸው ሊያቋቁሙትና ተወዳዳሪ ሆነው ለመውጣት የመዋእለ ንዋይ እጥረታቸውን ለማስወገድ እየተጠቀሙበት ያለ ዘመናዊ የንግድ ማህበር ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ንግድ ማህበር የገንዘብ እጥረትን ለመቅረፍ ወይም በተደራጀ መንገድ ወደ ገበያ ለመግባት በማሰብ የሚመሰረት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ገንዘብ ያላቸው ባለፀጎች የአክስዮን ዕጣ በመግዛት ገንዘቡ ትርፍ እንዲያስገኝላቸው የሚጠቀሙበትም ጭምር ነው፡፡

የአክስዮን ማህበርም ሆነ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የራሳቸው በጎ ገፅታዎች ያሏቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ (limited liability) መሆን ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 304 እና 510 (1) ይህ በአንግሎ አሜሪካን ካለው አሰራር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ጠንካራ ጎድናቸው የአክስዮን ማህበሩ አባላት በሙሉ ቢሞቱም ኩባንያው ግን የማይሞት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለትም ሌሎች ተወላጆች አክስዮኑን በመውረስ ሊቀጥሉበት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በሁለተኛ ዓለም ጦርነት ግዜ የኩባንያው ባለአክስዮኖች ለጠቅላላ ስብሰባ እንደተቀመጡ በሃይድሮጅን ቦንብ አልቀዋል ኩባንያው ግን አባላቱ በቦምብ በማለቃቸው ምክንያት ህጋዊ ሰውነቱን አላጣም፡፡ ይህ አክስዮን ማህበር ባህሪ ከሽርካ ማህበር የሚለየውና የጥንካሬው መገለጫ ነው፡፡ ሌላው አክስዮን ማህበር ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ በመሆኑ ግዙፍ ኢንተርፕራይዞች እንዲኖሩና ለዚህም ህዝብ በገቢ ማስገኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲሳተፍ የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡ በመጨረሻም አክስዮን ማህበር የአባላቱን ማንነት ታሳቢ የማያደርግ መሆኑ ናቸው፡፡ አክስዮን ማህበር የራሱ ጠንካራ ያለው እንደመሆኑ መጠን የራሱ ድክመት ያለው ነው ለዚህም ይመስላል Avatar sigh “Corporate entities works like boomerang and hits a man who tries to use it” በማለት የሚገልፁት፡፡ እንደ አክስዮን ማህበር ደካማ ጎድኖች የሚወስዱት ጉዳዮችም፤-

- አክስዮን ማህበር ለመመስረት የሚጠይቀው ስነ-ስርዓት ውስብስብና አስቸጋሪ መሆኑ (Formation formalities and procedure are cumbersome)
- ለምስረታው የተለያዩ ባለሙያዎች እንደ የመመስረቻ ፅሁፉንና ደንቡን የሚያረቅ የህግ ባለሙያ፣ በዓይነት የተደረገውን መዋጮ ለመገመት የሂሳብ ወይም የምህንድስና

ባለሙያን መጠቀም ስለሚጠይቅ ወጪ እንዲጨምር የሚያደርግ መሆኑ (Incorporation requires expenditure)

- የኩባንያው ንብረት እንደ ኩባንያው ንብረት እንጂ እንደ ኣባሉ ንብረት ስለማይታይ በመዋጮ የተዋጣው ንብረትና የዚህ ንብረት አስተዳደር የተነጣጠለ መሆኑ (Separation of fund and management)
- የአክስዮን ማህበር የሚቋቋመው ለኣባለቱ ትርፍ ለማስገኘት ቢሆንም የማህበሩን ዘላቂ ጥቅም፣ ለብሄራዊ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ የማድረግ፤ ለሰራተኞች ህልውና ሃላፊነት የመውሰድ፣ በሚመረተው ምርትና ደንበኞች መካከል ያለውን ጤናማ ግንኙነት የማስጠበቅ ሃላፊነት (Social responsibility) ያለበት መሆኑ በቀላሉ የሚጠቀሙበት እንዳይሆን የሚያደርገው ምሆኑ ናቸው፡፡

### 3.4.1 የአክስዬን ማህበር ምስረታ

1. በማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ በፈረሙ ሰዎች (persons who sign on a memorandum of association)
2. በፕሮስፔክተስ ላይ በሚፈርሙ ሰዎች (Persons who sign on a prospectus)
3. በዓይነት መዋጮ ባደረጉ ሰዎች (Persons making contribution in kind)
4. ልዩ ዕጣ ባላቸው ሰዎች (Persons allocated with special shares of profit)
5. ለአክስዬን ማህበሩ መመስረት መነሻ እቅድ ባዘጋጁ ሰዎች (Persons who initiate plans for the formation of company or making possible the formation) ሊመሰረት ይችላል፤፤ የመስራቾች መብትና ግዴታም፤-

- ➢ ልዩ የአክስዬን ትርፍ
- ➢ የአክስዬን ማህበሩ ኣባል የመሆን
- ➢ በዓይነት መዋጮ የማዋጣት
- ➢ ለማስተዋወቅ የወጣ ወጪ እንዲመለስላቸው ከማህበሩ የመጠየቅ መበት
- ➢ የማህበሩ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የመሾም መብቶች ያሉዋቸው ሲሆን በግዴታነትም
- ለኩባንያው ጥቅም በቅን ልቦና የመስራት
- በማስተዋወቅ ሂደት የተገኘ ጥቅም አለመሸሸግ
- የአክስዮኑን ዋጋ ከፍ አድርጎ የተገኘ ጥቅምን ኣለመሸሸግ ሲሆኑ እነዚህን ጥሰው በሚገኙበት ጊዜ በጋራና በነጣላ ለሶስተኛ ወገኖች ጉዳት ሃላፊ ናቸው፡፡ የወንጀል ሃላፊነትን በተመለከተ እንደየ ሁኔታው በወ/ህ/ቁ 692፣ 695፣ 696 መታየት ያለበት ሲሆን የፍ/ብሄር ሃላፊነት በተመለከተ ፍ/ህ/ቁ 2028 እና ቀጣይ ህጎች የሚታይ ይሆናል፤፤ ክስ የማቅረብያ ይርጋ ግዜው በን/ህ/ቁ 309 (2) መሰረት ክሱ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

የሃላፊነቱ የወሰነ የግል ማህበር በባህሪው የሽርካ ማህበርና አክስዬን ማህበር ቅይጥ ሆኖ እርስ በርስ ትውውቅ ባላቸውና የአባሉ ማንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚመሰረት የንግድ ማህበር ነው፡፡ የማህበሩ እጣዎች ለውጭ ሰው የማይሸጥ ሲሆን ከምስረታ በኋላም የማህበሩ አባላት ፈቃዳቸውን ሳይሰጡ ድርሻውን ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት በአባላቱ መካከል ሊሆን ብቻ ነው፡፡ አክስዬን ማህበርም ሆነ ሃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ከምስረታ በኋላ ማህበሩ ስም ሊኖረው ይገባል፡፡ የሚሰጠው ስያሜ የህዝብ ፖሊሲን መፃረር፣ የሶስተኛ ወገኖች መብትን የሚነካ መሆን የለበትም (ን/ህ/ቁ 133(2) () እና 134) እንዲሁም በንግድ ማህበሩ ስም ፊት "አክስዬን ማህበር (አ/ማ) ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሚል መጨመር አለበት (ን/ህ/ቁ 305 እና 514(2))

## 3.4.2 የአክስዬን ማህበርና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አጠቃላይ ይዘት

1. አክስዬን ማህበር
   - ከሌሎቹ የሽርካ ማህበር የተለየ መሆኑ፡፡
   - የአባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 508)
   - የአባላቱ ቁጥር ብዙ ላይሆን ይችላል ይሄውም ለምስረታው ≥ 5 አባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 307(1)
   - ህጋዊ ሰውነት አለው፡፡ (ን/ህ/ቁ 214(2))
   - የአባልነት መብት በነፃነት ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ይችላል
   - ከፍተኛ መዋእለ ንዋይ በሚጠይቁ የንግድ ስራዎች ለመሰማራት የሚመሰረት ነው፡፡

2. ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
   - ❖ የአክስዬን ማህበርና ሽርካ ማህበር ቅይጥ ነው፡፡
   - ❖ የአባላቱ ሃላፊነት የተወሰነ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 510)
   - ❖ የተወሰነ ቁጥር የሚያዝና የአባላቱ ጥቅም ወደ ሶስተኛ ወገን በነፃነት የማይተላለፍ በመሆኑ የሽርካ ማህበር ባህርያት ያሉት ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 523 (2))
   - ❖ ህጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 214 (2))
   - ❖ የመነሻ ካፒታሉ 15,000 ብር ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 512)

## 3.4.3 ኩባንያዎቹ ጥቅምና ጉዳት -

- ጠንካራ የገንዘብ አቅም (financial strength)
- የተወሰነ ሃላፊነት (limited liability)
- የመስፋፋት እድል (Scope of expansion)
- ውጤታማና ንቁ አስተዳደር (efficient and bold management)
- የተበተነ አደጋ (diffused risk) ጥቅሞች ያሉዋቸው ሲሆን ከጉዳት አንፃርም
- ➢ በቀላሉ የማይመሰረት መሆን (difficulty of formation)

- የንብረቱ ባለቤት ያለመሆን (Lack of owner's personal Interest)
- የውሳኔ መዘግየት (delay indecision making)
- በጥቂቶች እጅ የወደቀና ተንኮል የተላበሰ አስተዳደር (Oligarchic fraudulent management)
- የግብር ክፍያው ከፍተኛ መሆን(high taxation)
- ሚስጢር አለመጠበቅ (Lack of secrecy) ናቸው፡፡

### 3.4.4 የማህበራቱ መፍረስ

#### 1. በህግ መፍረስ (dissolution by law)

እነዚህ ማህበራት በህግ ሊፈርሱ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች የተቋቋሙበትን ዓላማ ማሳካት ሲሳናቸው ወይም መፈፀም ሲያቅታቸው (failure of purpose or impossibility of performance) ፣ ከማህበሩ ካፒታል ሶስት አራተኛው ሲጠፋ (loss of three quarter of the capital) እና የመክሰር ክስ ሲቀርብ (institution of bankruptcy proceedings) ናቸው፡፡ (ን/ህ/ቁ 331(4)፣ 517 (ሐ)) ሌላው አክስዮንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተመሰረተበት ዓላማ አሳክቶ ወይም ሳይሳካ ግዜው ሲደርስ የሚከናወን መፍረስ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 217(ሀ)፣ 495(1)

አንድ አክስዬን ማህበር የተቋቋመበትን ዓላማ በማሳካቱ ምክንያት በህግ በሚፈርስበት ሁኔታ ዙርያ አንድ ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ 58/92 ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ጋር የነበረን የፍ/ቤት ጉዳይ ወስደን ስንመለከት ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ ፈቃዱ የተሰጠው በአዋጅ ቁጥር 84/1986 መሰረት ሆኖ ብሄራዊ ባንክ የንግድ ፈቃዱን የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የተቋቋመ ነው በሚል ምክንያት በመሰረዙ ምክንያት ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት በሆርን ኢንተርናሽናል ከሳሽነት የቀረበ ሲሆን በፍርድ ቤት ትእዛዝ ባንኩ እንዲፈርስ ተደርጓል ፍ/ቤቱ አክስዬን ማህበሩን ለማፍረስ የተጠቀመበት የህግ ድንጋጌ ን/ህ/ቁ 495(1) (ለ) ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ይዘት "ማህበሩ የተቋቋመበት ስራ ሲያልቅ" የሚል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ፍ/ቤቱ ሆርን ኢንተርናሽናል ባንክ እንዲፈርስ ለሰጠው ውሳኔ በምክንያትነት የገለፀው ህግ በአግባቡ እንዳልሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም፤፤ እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ ግን የዚህ ዓይነት ክፍተት ሊመጣ የቻለው በአገራችን የምስረታ (formation) ችግር ያለበት አክስዬንም ሆነ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከተመሰረተ በኋላ በህግ ስለሚፈርስበት ሁኔታ በንግድ ህጉ ያልተሸፈነ በመሆኑ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

#### 1.2 የማህበሩ ዕድሜ ማለቅ (Expiration of the company)

ን/ህ/ቁ 217(3) ማህበሩ በህግ ወይም በስምምነት የሚፈርስበት ምክንያት በሚል ርእሰ ስር ማህበርተኞቹ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተስማሙ በቀር ማህበሩ የተቋቋመበት ዘመን ሲፈፀም ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ አንድ አክስዬን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር ሊፈርስ

ከሚችልባቸው ምክንያቶች አንዱ በመመስረቻ ፅሁፍ ላይ ለተወሰነ ግዜ የተቋቋመ ማህበር ከሆነ የጊዜው መድረስ በራሱ በህግ ያገኘውን ህጋዊ ሰውነቱን እንደሚያጣ የሚገልፅ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አባላቱ ማህበሩ ዘመኑ ሊያልቅ ሲቃረብ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ (extra-ordinary meeting) በመጥራት የማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ (memorandum of association) በ2/3 ድምፅ እንዲሻሻል ከወሰኑ በማሻሻል ሊቀጥሉ እንደሚችሉ በህግ የተፈቀደ መሆኑ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 217(3)፣ 495(1) (ሀ)፣ 425(1)፣ 423 እና የማህበሩ ዓይነት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚሆንበት ጊዜ በን/ህ/ቁ 536(2) መሰረት መሻሻልን የሚጠይቅ ነው፤፤

**1.3 የማህበሩ ካፒታል ሶስት አራተኛ መጉደል** (loss of three quarter of the capital)

ለማህበሩ በህግ መፍረስ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ማህበር ስራውን ለማከናወን የግድ ገንዘብ ያስፈልገዋል ይህ ገንዘብ በሶስት ዓይነት መንገድ የሚገለፅ የማህበሩ ካፒታል ሊሆን ይችላል ይሄውም፡-

- በማህበሩ መመስረቻ መሰረት ዕጣ (አክስዬን) እንዲወጣ በመደረግ የሚገኝ የማህበሩ ካፒታል (nominal capital or authorized capital) የሚባለው ዓይነት ካፒታል፣
- ሌላው በማህበሩ የወጡ አክስዬኖች ዋጋ (issued or subscribed capital) የሚባለው ሲሆን፣
- ሶስተኛው ለአክስዬኖች የተከፈለው ገንዘብ መጠን (paid up capital) ወይም አክስዬኑ ያልተከፈለ ዋጋ (un paid capital) የሚባል ሲሆን በዋናነት አንድ አክስዬን ማህበር ስራዎቹን በሚያካናውንበት ጊዜ ሶስተኛ ወገኖች ዋስትና ተሰምቷቸው ያለ ስጋት ከኩባንያው ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸው የማህበሩ ካፒታል ስለሆነ አክስዬን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ን/ህ/ቁ 80 እና 517 (መ) እና (ሰ) መሰረት ካፒታላቸውን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ስለ ካፒታል መጥፋት ስናስብ መሰረታችን የሚሆነው የአክስዬን ዋጋ በሙሉ ስለተከፈለበት አክስዬን ማህበር ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ካፒታል እንጂ ቀደም ሲል ስለገለፅናቸው የማህበሩ ካፒታል ሁለት ሶስተኛ መጥፋት አለመሆኑን ከን/ህ/ቁ 495(1) (ሽ) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ በአንድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሶስት አራተኛው ካፒታል መጥፋትን መሰረት በማድረግ ሊፈርስ የሚችለው በን/ህ/ቁ 543(1) መሰረት በማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማህበሩ እንዲፈርስ ሃሳብ ሲቀርብ መሆኑና የዚህ ዓይነት መፍረስ ሊከሰት የሚችለው የማህበሩ ሶስት አራተኛ ካፒታል በመጥፋቱ ምክንያት አንድ አክስዬን ማህበር እንዲፈርስ የሚደረገው በን/ህ/ቁ 495(2) የአባላቱ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ (Extraordinary meeting) በመጥራት መሆኑና ይህም የሚደረግበት ምክንያት አባላቱ የማህበሩን ካፒታል

ከፍ እንዲል በማድረግ ሊታደጉት ይችሉ እንደሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ን/ህ/ቁ 495(3) እንደሚደነግገው በአንድ ጥቅም አለኝ የሚል ወገን ጠያቂነት ማህበሩ በፍ/ቤት እንዲፈርስ ይደርጋል፡፡

### 1.3 ኩባንያው በመክሰሩ ምክንያት ክስ ሲቀርብበት የሚኖር መፍረስ (bankruptcy proceeding)

አክስዮን ማህበርና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሁሌ ነጋዴ ናቸው ተብለው ሲለሚታሰቡ ለመክሰር ህግ በእጅጉ የቀረቡ የንግድ ማህበራት ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ን/ህ/ቁ 968 (1) በን/ህ/ቁ 5 መሰረት ነጋዴ በሆኑና በን/ህ/ቁ 10(1) ከአሽሙር ማህበር በስተቀር የመክሰር ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ሲል የሚደነግገው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ማስተዋልን የሚጠይቅ ነገር ን/ህ/ቁ 969 "ማንኛውንም ከንግድ የተያያዘውን ዕዳውን መክፈል ያቋረጠና መክሰሩ በፍርድ ቤት የተወሰነ ነጋዴ ሁሉ ሆኖ የሚቆጠር ነው" በማለት ስለሚደነግግ የመክሰር ህግ የሚመለከተው በን/ህ/ቁ 5 ነጋዴ ለሚባሉ ብቻ ነው የሚል ትርጓሜ በመስጠት ሌሎች የንግድ ማህበራትን አይመለከትም ብሎ መወሰድ የለሌበት መሆኑ ነው፡፡ ለምን ቢባል ን/ህ/ቁ 5 ከ10 ጋር አጣምረን ካየነው ከአሽሙር ማህበር በስተቀር ሁሉም የንግድ ማህበራት ነጋዴ ናቸው ተብለው ስለሚታሰቡ አክስዮንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርም የመክሰር ህግ በነሱም ላይ ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ አንድ አክስዮን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዕዳውን መክፈል ካልቻለ በ15 ቀን ውስጥ ስልጣን ወዳለው ሬጂስትራር ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡ (ን/ህ/ቁ 974) የዚህ ማህበራት በመክሰር ምክንያት በፍ/ቤት ውሳኔ መስጠቱን እንደምክንያት በመውሰድ በህግ እንደፈረሱ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ን/ህ/ቁ 495(1) ይዘት በመመልከት ልንገነዘብ የምንችል ሲሆን ይህ የሚደረግበት ምክንያትም አንድ ከሰሯል የተባለ የንግድ ማህበር በአባላቱ ውሳኔ ይቀጥል የሚባል ከሆነ የማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች ዋስትና እንዲያጡ የሚያደርግ በመሆኑ መክሰር እንደ አንድ የንግድ ማህበር በህግ የሚፈርስበት ምክንያት በመውሰድ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስትና መስጠት ተገቢ በመሆኑ ነው፡፡

በንግድ ህጉ አንድ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመክሰር ምክንያት ሊፈርስ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለየና ግልፅ በሆነ መንገድ የሚለው ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን ን/ህ/ቁ 542 ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሌሎች የንግድ ማህበራት በሚፈርሱባቸው ምክንያቶች ሊፈርስ እንደሚችል የሚደነግግ በሆኑና ሌሎች የንገድ ማህበራት በመክሰር ምክንያት ሊፈርሱ እንደሚችሉ ደግሞ ን/ህ/ቁ 968(1) ስለሚደነገግ የዚህ ዓይነት ማህበርም በመክሰር ምክንያት ሊፈርስ እንደሚችል ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ የንግድ ማህበር ይፈርስልኝ ጥያቄ የሚቀርበውም በን/ህ/ቁ 975 መሰረት፡-

- ነጋዴው መክሰሩን ለማሳወቅ ማመልከቻ ሲያቀርብ

- አንድ ወይም ከዚያ በላይ ገንዘብ ጠያቂዎች ሲያመለክቱ
- ህግ አስከባሪው ሲጠይቅ
- ፍ/ቤት ራሱ ሲፈቅድ ናቸው፡፡

ስለዚህ የአንድ የንግድ ማህበር መፍረስ ከህግ ሊመነጭ የሚችለው የተቋቋመበት ዓላማ ማሳካት ሲሳነው፣ ዓላማውን ያሳካ ቢሆንም የተቋቋመው ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑና ጊዜው ሲደርስ አባላቱ የመመስረቻ ፅሁፋቸውን በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ በማግኘት እንዲታደስ ለማድረግ የሚያስችል ውሳኔ መስጠት ሳይችሉ የቀሩ እንደሆነ ወይም በመክስር(bankruptcy) ምክንያት ወይም ን/ህ/ቁ 495(1) የተዘረዘሩ ሌሎቸ ምክንያቶች ነው፡፡

## 2. በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስ (Dissolution by the court)

አንድ አክስዮን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአባላቱ ወይም አንድ አባል በቀረበ የይፍረስልን ጥያቄ ሊፈርስ ይችላል፡፡ (ን/ህ/ቁ 218(1)) አባል የሚባለውም በን/ህ/ቁ 331 ወይም 521 መሰረት መዋጮ ያደረገ ሰው ነው፡፡ ማህበሩ እንዲፈርስ የሚደረገው ግን እንዲሁ የማህበሩ አባል ስላመለከተ ብቻ ሳይሆን በን/ህ/ቁ 218 መሰረት ትክክልኛ ምክንያት (good cause) መኖርንም ጭምር የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ እንደመከራከርያ ሊነሱ የሚችሉት ሃሳቦች ን/ህ/ቁ 218(2) በሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደነገገ በመሆኑ በአክስዮንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርም ተፈፃሚ መሆን አለበት፡፡ በፍርድ ቤት ውሳኔ የመፍረስ ጉዳይ ለሽርካ ማህበር ብቻ የተሰጠ የማፍረሻ መንገድ አይደለም፡፡ በሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚነት ማግኘት ያለበት ነው የሚሉ መከራከሪያዎችን በማንሳት ን/ህ/ቁ 495(1) እና 542(1) ጠቅሶ መከራከር ይቻላል፡፡ ሌላው መከራከርያ ሊሆን የሚችለውም ን/ህ/ቁ 218(2) ያለቀለት ዝርዝር (exhaustive list) አይደለም በማለት የሚቀርብ መከራከርያ ነው፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ የፍርድ ቤት አቋም ምን ይመስላል ብሎ ለማየት ዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያ ከብሄራዊ ባንክ ጋር የተከራከሩበትን ፍ/መ/ቁ 812/88 ወስደን ስናይ መሰራቾች ነን የሚሉት ከብሄራዊ ባንክ ጋር የተፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት ምክንያት በማድረግ ማህበሩ እንዲፈርስ አቤቲታቸውን ወደ ፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያና ብሄራዊ ባንክ መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት መፈጠሩን ሳያጣራ በሌሎች ፍሬ-ነገሮች እንደ ጠቅላላ ጉባኤ አለማካሄድ፣ ኦዲተሮች ያለመሾም፣ ከአባላቱ በመዋጮ የተሰበሰበ የማህበሩ ገንዘብ ዕዳው ለመሸፈን የማይችል መሆኑን እንደ ትክክልኛ ምክንያት (good cause) በመውሰድ ዩኒቨርሳል ኢንሹራንስ ኩባንያ እንዲፈርስ ወስኗል፡፡ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ መረዳት የሚቻለው በን/ህ/ቁ 218(2) የተዘረዘሩት ትክክልኛ ምክንያቶች አንድ የንገድ ማህበር በፍ/ቤት ውሳኔ ለማፍረስ ብቸኛ ምክንያቶች አለመሆነቸውን ነው፡፡

ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን በፍ/ቤት በማፍረስ ዙርያ ያሉትን የፍ/ቤቶች አካሄድ ስንመለከት እንደዚሁ የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት አቶ ጣሂር ሃጀና አቶ አብዱል

መሊክ የመሰረቱት "Engineering and mechanical work shop Garage private limited company" በመካከላችን አለመግባባት ስለተፈጠረ ማህበሩ ይፍረስልን በማለት ባስከፊቱት ፍ/መ/ቁ 2869/87 ላይ ማህበሩ እንዲፈርስ የወሰነ ሲሆን የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በአባላቱና አልፋ የጉዞ ወኪል መካከል የነበረውን የማህበሩ ይፍረስልን ክርክር በፍ/መ/ቁ 97/90 ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ለመስጠት ምክንያት አድርጎ የወሰደው በመካከላቸው ጠንካራ ጠብ የመፈጠሩ ምክንያት ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ን/ህ/ቁ 218(2) ጠቅላላ ድንጋጌ እንደመሆኑ መጠን ለሁሉም የንግድ ማህበራት ተፈፃሚ መሆን አለበት የሚል አረዳድ በፍ/ቤቶች አካባቢ መኖሩን ነው፡፡

3. **የአባላት ቁጥር ባለመሟላት ምክንያት የማህበር መፍረስ** (Reduction of the number of members below the legal requirement)

ኩባንያውን ለመመስረት በህግ የታወቀው ቁጥር ባለመሟላቱ ምክንያት አንድ ኩባንያ ሊፈርስ ይችላል፡፡ ለዚህም ን/ህ/ቁ 311 የአባላቱ ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ ማህበሩ እንደሚፈርስ ይደነግጋል፡፡ ስለ አክስዬን ማህበር መፍረስ የሚደነግገው ን/ህ/ቁ 495(1) የሚመለሰውም ወደ ን/ህ/ቁ 311 ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ኩባንያ በን/ህ/ቁ 525 እና 532 (1) ማማላት የሚገባውን አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ የሃላፊነቱ የተወሰነ ግል ማህበር አባላት ቁጥርን ለመወሰን የተደነገገው ን/ህ/ቁ 511 የአባላቱ ቁጥር ከሁለት በታች ከሆነ ማህበሩ እንደሚፈርስ ይደነግጋል፡፡ ሌላው አንድ እንደዚህ ያለ የንግድ ማህበር እንዲፈርስ ምክንያት የሚሆነው የዕጣዎቹ በአንድ ሰው ባለቤትነት ስር መካማቸት ሲኖር በን/ህ/ቁ 278(ሰ) መሰረት የሚደረግ መፍረስ ነው፡፡ ለዚህም የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በኢትዮጵያ መድን ድርጅትና ረዲ አለም አቀፍና አባላቱ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መካከል የነበረውን ክርክር በፍ/መ/ቁ 70/89 የአባላቱ ቁጥር ህግ ከሚጠይቀው መስፈርት በታች በመሆኑ ምክንያት ማህበሩ እንዲፈርስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የአባላት ቁጥር ለንግድ ማህበሩ ህልውና የቱን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ነው፤፤

4. **በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መፍረስ** (Voluntary dissolution of share and private limited company)

በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የንግድ ማህበር መፍረስ የሚከሰተው ን/ህ/ቁ 217(ለ) በሚደነገገው መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን ነው፡፡ ይህ ህግ ጠቅለላ ድንጋጌ በሚል ስር የሚገኝ በመሆኑ ለአክስዬንና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ለዚህም ነው ን/ህ/ቁጥር 495(1) (ሀ) "በድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲቀጥል ካልተወሰነ በቀር..." የሚለውን አባባል የሚጠቀመው፡፡ በአክስዬን ማህበር ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚጠራው የአባላቱን የአክስዬን ብዛት ከግምት ሳያስገባ ነው፡፡ (ን/ህ/ቁ 424) እንደዚህም ምልአተ ጉባኤውን በተመለከተ ን/ህ/ቁ 425(3) የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለማሳለፍ በመጀመርያው ጥሪ ከባለአክስዬኖች ግማሽ፣ በሁለተኛው ጥሪ አንድ ሶስተኛ፣ በሶስተኛው ጥሪ

እጅግ ቢያንስ አንድ አስረኛው ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ ስብሰባው ይቀጥላል ሲል የሚደነግገው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ አንድ አክስዮን ማህበር ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ በአባላቱ ፈቃድ እንደሚፈርስ ግን በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያትም በህግ ሁኔታዎች በማስቀመጥ የማህበሩ አባላት ፍላጎትን ከመገደብ ይልቅ በራሳቸው ነፃ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ የማህበር መፍረስን እንድ አካሄድ የመረጠ ይመስላል፡፡ በሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዙርያ ያለውን በፈቃድ ላይ የተመሰረተ መፍረስን ስናይ ን/ህ/ቁ 217 (ለ) ማንኛውም የንግድ ማህበር በአባላቱ ፈቃድ ሊፈርስ እንደሚችል ቢደነግግም የዚህ ዓይነት ማህበርን የማፍረስ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የሚደነግገው የህጉ ማእቀፍ ሃላፊነቱ የግል ማህበር በምን መንገድ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ መፍረስን ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚችል የሚለው ነገር የለም፡፡ ን/ህ/ቁ 532(1) እና 535 ቢሆንም ለዚህ መልስ የሚሰጡ አይደሉም፡፡

### 3.4.5 የሂሳብ ማጣራት (liquidation)

የአክስዮን ወይም ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እስካሁን እያየናቸው በመጠን ምክንያቶች ሊፈርሱ ይችላሉ፡፡ የፈረሰ ማህበር ሂሳብ መጣራት ደግሞ ከፍተኛ የህግ እውቅና የተሰጠው ነው፡፡ በአገራችን ከን/ህ/ቁ 497-509 ባሉ ድንጋጌዎች የአክስዮን ማህበር ንብረት ማጣራትን በሚመለከት የሚደነግግ ሲሆን ስለ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማጣራት ከመፍረስ ቀጥሎ የሚመጣ አማራጭ የሌለው መንገድ (indispensable element) ሆኖ ሳለ ስለመፍረስ ብቻ ደንግጎ ስለ ማጣራት በዝምታ ማለፉ ምክንያታዊ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሽርካና አክስዬን ማህበር ቅይጥ እንደመሆኑ መጠንና በሽርካና አክስዬን ማህበር የማጣራት ሂደት ተመሳሳይነት ያለው ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የአንዳቸውን የማጣራት ሂደት ህግ ተከትለን እንዳናጣራ የሚከለክል ህግ ባለመኖሩ በዚህ መንገድ ሂሰሳቡን ማጣራት ይቻላል ፡፡ ስለ ማጣራት ስናነሳ የአጣሪዎችን ጉዳይ ማንሳታችን የግድ ሰለሆነ አጣሪዎችን በተመለከተ በሚቀጥለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

#### 1. የአጣሪዎች ህጋዊነት (Legal status of liquidators)

አጣሪ ሁለት (dual) ማንነት ያለው ነው፤፤ አንደኛው ኩባንያውን በመወከል የሚይዘው አቋም (position) ሲሆን ሌለኛው ደግሞ አበዳሪዎችን በመወከል የሚኖረው አቋም (position) ነው፡፡ የኩባንያው ወኪል በመሆን በን/ህ/ቁ 500(1) መሰረት ንብረት መሸጥ የሚችል ሲሆን ስራውን የሚያከናውነውም ልክ እንደ ኩባንያው አስተዳዳሪ በመሆን እንደሆነና የሚኖረው ግዴታም ሆነ ሃላፊነት የሚገዛው በን/ህ/ቁ 499(1) መሰረት ነው፡፡

#### 2. የአጣሪዎች ሹመት(Appointment of Liquidators)

አጣሪ የሚሸምበት ዋናው ምክንያት ፍትሃዊ የንብረት አስተዳደርና ክፍፍል በአባዳሪዎች (Creditors) እና በን/ህ/ቁ 496 መሰረት የሚሾመው በመመስረቻ ፅሁፍ ወይም ኩባንያው

www.abyssinialaw.com

ለማፍረስ በተካሄደው ጠቅላላ ድንገተኛ ጉባኤ ነው፡፡ ከሁለቱ ባንዱ መንገድ ካልተሾመ በፍርድ ቤት ሊሾም ይችላል፡፡ ን/ህ/ቁ 496(1) ኣጣሪ ስለሚሾምባቸው መንገዶች ቢደነግግም የመመስረቻ ፅሁፍን በማስመልከት የተደነገጉት ን/ህ/ቁ 313 እና 516 በመመስረቻ ፅሁፍ ኣጣሪ ስለሚሾምበት የሚሉት ነገር የላቸውም፡፡ ይህም ብቻ ኣይደለም ኣጣሪ የሚሆን እንዴት ያለ ሰው እንደሆነና የተፈጥሮ ሰው ኣጣሪ ስለሚሆንበት ሁኔታም ሆነ እንዳይሆን የሚከለከልበት ግልፅ የሆነ ድንጋጌ የለም፡፡ በነዚህ ሓሳቦች ዙርያ አንድ Lawrence church የተባለ ፀሃፊ፣ በዚህ ፀሓፊ ኣባባል ኣጣሪ መሆን ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው ለምን ቢባል ን/ህ/ቁ 347(4) የዳሬክተሮች ቦርድ ሊቀመንበር የተፈጥሮ ሰው መሆን ኣለበት በማለት ስለሚደነግግ የተፈጥሮ ሰው በመሆኑ በህግ የወጣን ነገር በመጣስ በህግ ሰውነት የተሰጠውን ተቋም አጣሪ (liquidator) አድርጎ መሾም ኣይቻልም የሚል ነው፡፡ የኣጣሪ መሾም ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? ያልን እንደሆነ ን/ህ/ቁ 499(2) ዳሬክተሮቹ በስራ ላይ እንደሚቆዩ የሚደነግግ በመሆኑ ኣጣሪዎች ስራቸውን በኣግባቡ እንዳያከናውኑ ሊገቷቸው የሚችሉ መሆናቸውና ን/ህ/ቁ 498(2) ዳሬክተሩ ማህበሩን ሊወክል ስለሚችልበት ሁኔታ ስለሚደነግግና ን/ህ/ቁ 497(2) ዳሬክተሮቹ በማጣራቱ ወቅት አንዳንድ ስራዎች እየሰሩ በማህበሩ ስለመቆዩበት ሁኔታ የሚጠቁመው ነገር በመኖሩ ኣጣሪዎች በተገቢው መንገድ ስልጣናቸውን መሰረት በማድረግ እንዳይሰሩ ሊገድባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ የሚያሳይ ነው፡፡ ሆኖመ ግን አጣሪዎቹ ይህን ተቋቁመው ንብረቱን የማጣራትና ለጉዳዩ እልባት የመሰጠት ሃላፊነትና የንግድ ህጉ በሚሰጣቸው መብት ተጠቃሚ የመሆን መብትን የሚያሰገኝላቸው ነው፡፡

## 3. የኣጣሪዎች ክፍያ (Remuneration of liquidators)

የሂሳብ ኣጣሪ የኩባንያውን አባላትን ሆነ ገንዘብ ጠያቂዎች (creditors) ለመርዳት ሲል ወደ ስራው የሚገባ ሰው ኣይደለም፡፡ የንግድ ህጉ ስለ ሂሳብ ኣጣሪ ክፍያ የሚለው ነገር ባይኖርም ይህን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ኣስተያየቶችን መስጠት ይቻላል፡፡ ኣንደኛው ህግ ኣውጪው የሂሳብ ኣጣሪውን ክፍያ የመወሰን ጉዳይ ለሿሚዎች ስለተወው እነርሱ መወሰን ይችላሉ የሚል ሲሆን ሌላው የዳሬክተሮችና ስራ ኣስኪያጆች ክፍያ በኣባላቱ የሚወሰን እስከሆነና የሂሳብ ኣጣሪው ሃላፊነት በን/ህ/ቁ 499 መሰረት የዳሬክተሮችና ስራ ኣስኪያጆች ካላቸው ሃላፊነት ጋር እኩል እስከሆነ ድረስ ክፍያውም መወሰን ያለበት በማህበሩ ኣባላት ነው ብሎ በህጉ የሚታየውን ክፍተት መሙላት ይቻላል የሚል ነው፡፡

4. **የሂሳብ አጣሪውን ስለመሻር** (removal of a liquidator)

የሂሳብ አጣሪን መሻር በማስመልከት ን/ህ/ቁ 496(3) "ሂሳብ አጣሪዎችን የማህበሩ መፍረስ የመወሰነው ጉባኤ ሊሽራቸው ይችላል፡፡ ሂሳብ አጣሪዎቹን በቂ በሆኑ ምክንያቶች ማህበርተኞች ወይም ተቆጣጣሪዎች በሚያቀርቡት ጥያቄ በ/ን/ህ/ቁ 493(2) መሰረት ፍርድ ቤት ሊሽራቸው ይችላል፡፡" በማለት ስለሚደነግግ የሂሳብ አጣሪዎች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤና በፍርድ ቤት ውሳኔ ከስልጣናቸው ሊነሱ ይችላሉ፡፡

5. **የሂሳብ አጣሪዎች አጠቃላይ ስልጣን**

የሂሳብ አጣሪዎች የኩባንያው ወኪሎች እንደመሆናቸው መጠን የሚኖራቸው ስልጣንም መታየት ያለበት አንድ ወኪል ከሚኖረው ስልጣን አንፃር ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጣሪዎች ፍ/ብ/ህ/ቁ 2189 እንደሚደነግገው ወካዩ በሰጠው ስልጣን መሰረትና ለወካዩ ጥቅም መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ይሁንና ሂሳብ አጣሪ የኩባንያው ወኪል በመሆኑ ስለሚኖረው ስልጣን ለማየት ከፍ ብሎ የተገለፀውን አነሳን እንጂ ን/ህ/ቁ 500(1) የሂሳብ አጣሪ ስልጣን በማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ሊገደብ እንደሚችል ስለሚደነግግ የሂሳብ አጣሪ ስልጣን እንዲሁ ያለገደብ (un limitedly) የተተወ አይደለም፡፡ አንድ ሂሳብ አጣሪ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ እንደ አንድ የመልካም ቤተሰብ አባት (*bonus pater familias*) በከፍተኛ ቅን ልቦና (utmost good faith) መስራት ይጠበቅበታል፡፡ አጣሪዎች የኩባንያውን ንብረትና የሂሳብ ደብተር የመያዝና የገንዘብ ጠያቂዎችን የመጥራትና ዕዳውን የማጣራት ማስረጃ የመመርመር፣ ዕዳውን የመክፈልና የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት የማስጠበቅ፣ ከዕዳ መክፈያ የቀረውን ትርፍ ሃብት በአባላቱ መካከል እንዲከፈል የማድረግ፣ በን/ህ/ቁ 226 መሰረት ማህበሩ ከንግድ መዝገብ እንዲሰረዝ የማድረግ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ለዚህም ን/ህ/ቁ 499(2)፣ 500፣ 504(1)፣ 502(3)፣ 1110፣ 1056፣ 1066፣ 1068፣ 508(2)፣ 505፣ 495፣ 542፣ 217፣ 218 መሰረት በማድረግ ያሉትን የስራ ድርሻዎች፣ ሃላፊነቶችና ስልጣን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ የንግድ ማህበራት መሰረታቸው ውል ቢሆንም የራሳቸው የተለየ ባህሪ ያላቸውና በንግድ ህጉ ድንጋጌዎች የሚገዙ ናቸው፡፡ እንደሁሉም ውሎች ተመስርተው ለረዥም ጊዜም ሆነ ላጭር ጊዜ በሂወት ከቆዩ በኃላ ቀሪ የሚሆኑና ለዚህም የራሳቸው ስርዓት ያላቸው መሆናቸውን ልንገነዘብ ይገባል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ካልተመዘገበ፣ የማስታወቅ ስራ ካልሰራና ፈቃድ ከሌለው የንግድ ማህበር ጋር የተደረገ ውል ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው?
2. አበበች ጎበና ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ከAction Aid Ethiopia ጋር በመተባበር ገቢው ለጎዳና ተዳዳሪዎች ማሳደጊያ የሚውል "ወገን ለወገን" ማተሚያ ቤት ቢከፍት በን/ህ/ቁ 210 ትርጉም የንግድ ማህበር ሊባል ይችላልን?

3. የእጅ ኢደጥበበኛ ማን ነው? አንድን ሰው እደ ጥበበኛ ብሎ ለመፈረጅ ያሉት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
4. በሽርካና የጋራ ባለሃብትነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
5. አክስዬን (ዕጣ) መብት በኣላባ ወይም በዋስትና ለሌላ ሰው ሊሰጥ የሚችል መብት ነውን?
6. የኣክስዬን ዓይነቶችና ባህርያት ምንድን ናቸው?
7. በኣክስዬንና የግዴታ ወረቀቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
8. ገንዘብ ጠያቂዎች በኣክስዬን ማህበር ዳሬክተሮች ስራ ኣስኪያጆች የግል ንብረት ላይ እጃቸውን ሊዘረጉ የሚችሉት መቼና እንዴት ነው?
9. በንግድ ማህበር መፍረስና ሂሳብ መጣራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
10. በመለወጥ (Conversion) ላይ ባለ ኩባንያ የገንዘብ ጠያቂዎች መብት ምንድን ነው?

# 4. የኢንሹራንስ ውል ሕግ

## 4.1. ስለኢንሹራንስ ውል በጠቅላላ (Insurance in General)

ኢንሹራንስ እንደ ግንኙነት በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል በሚደረስ ስምምነት ላይ የሚመሰረት ሆኖ ትርጉሙንና ባህሪውን በምንመለከትበት ጊዜም የኢትዮጵያ ንግድ ህግ በቁጥር 654(1) ላይ የኢንሹራንስን ምንነት በሚከተለው መንገድ፡-

“A contract where by a person called the insurer undertake against payment of one or more premiums to pay a person called the beneficiary a sum of money where a specified risk materializes” በማለት ፍቺ ሲሰጥ የዘርፉ ተመራማሪ የሆኑ E.R.Hardy Ivamy የተባሉ እንግሊዛዊ የዘርፉ ተመራማሪ ደግሞ፡-

> *Insurance or as it is sometimes called assurance, In the widest sense of the term may be defined, as a contract where by a person called the insurer undertakes in return for the agreed consideration called the premiums to pay to the another person called the assured on the happening of the specified event.*

በማለት የኢንሹራንስን ምንነት ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህ ሁለት ትርጓሜች መገንዘብ የሚቻለው ልዩነት ን/ህ/ቁ 654(1) የኢንሹራንስ ካሳ አከፋፈል (mode of indemnification) የኢንሹራንስ ሽፋን የተገባለት አደጋ ሲደርስ የኢንሹራንስ ውል ሰጪው (insurer) ኢንሹራንስ ውል ተቀባዩ (insured) በጥሬ ገንዘብ ካሳ እንደሚከፈል ሲደነግግ በእውቁ ተመራማሪ professor Ivamy በሰጡት ፍች ላይ ግን” A sum of money or its equivalent” በማለት አማራጭ የካሳ አከፋፈልን የሚፈቅድ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ በኢንሹራንስ ትርጉም ዙርያ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ አንድ የኢንሹራንስ ውል ተቀባይ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ካሳ እንዲከፈለው በሚጠይቅበት ግዜ የን/ህ/ቁ 654(1) የካሳ ኣከፋፈሉ ስርዓት በጥሬ ገንዘብ

ስለሚል በሌላ መንገድ ካሳውን አልቀበልም ብሎ በመከራከርያ ሊያነሳው ይችላልን? የሚል ሲሆን እንደ አዘጋጁ አስተያየት ከሆነ ካሳ ተከፋዩ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ አልቀበልም ብሎ መከራከር አይችልም የሚል ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው ን/ህ/ቁ 654(1) ካሳ በጥሬ ገንዘብ እንደሚከፈል ቢደነግግም

1. የኢንሹራንስ ውል ዓላማ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት አደጋ የደረሰበት መሆኑ ሲረጋገጥ ባለንብረቱን ወይም ህጋዊ ወራሾቹን አደጋው ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መመለስ እስከሆነ ድረስ ይህ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ በሌላ መንገድ መፈፀም አይቻልም ብሎ መደምደም የማይቻል በመሆኑ የዚህ ዓይነት መከራከርያ ተቀባይነት ማግኘት የለበትም የሚልና፡-
2. በአገራችን ያለውን አሰራር በምንመለከትበት ግዜ ለምሳሌ በናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) ለንግድ ተሽከርካሪ እንዲያገለግል የተዘጋጀው የኢንሹራንስ ፖሊሲ ክፍል 1 አንቀፅ 2 ላይ፡-

“The company may at its option pay **in cash** the amount of loss or damage or may **repair**, **reinstate** or **replace** the motor vehicle or any part there of ……” በማለት የውል ቃሉን አሰፍሮ የምናገኘውና እስካሁን ባሉ የመንግስትም ሆነ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እየተከተሉት ያለ አሰራር ይሄው በመሆኑና የባለንብረቱን ጥቅም እንዲቀር የሚያደርግ ባለመሆኑ መብቱ ተጣሰ ብሎ ለመክሰስ የሚያስችል ምክንያት የሌለው በመሆኑ መከራከርያው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚል ነው፡፡የኢንሹራንስን ባህሪ በምንመለከትበት ግዜ የኢንሹራንስ ፖሊሲ አስቀድሞ በኩባንያዎች ተዘጋጅቶ የሚቆይና የኢንሹራንስ ሽፋን የሚጠይቀው ግለሰብ ወይም ድርጅት የማመልከቻ ፎርሙን ሞልቶ ካቀረበ በኃላ በኢንሹራንስ ኩባንያው የስምምነት ቃሉ ተሞልቶ ከቀረበ በኃላ ካስፈለገህ ተቀብለው ካልፈለግክ ደግሞ ተወው (take it or leave it) ፖሊሲን የሚከተል የውል ዓይነት በመሆኑ የኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው የመደራደር መብት ዝቅተኛ የሆነበት ልዩ የውል ዓይነት ነው፡፡

## 4.2. የኢንሹራንስ ውል አመሰራረት (Formation)

አንድ የኢንሹራንስ ውል ሕግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ የማስገደድ ሃይል እንዲኖረው ከተፈለገ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1678 ያሉትን መመዘኛዎች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም ማለት በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ላይ መመስረት ይኖርበታል በመሆኑም የኢንሹራንስ የነፃ ፈቃድ መርህን *(consensus ad idem)* የሚከተል ነው፡፡ በነፃ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ስምምነት አለ ብሎ ለማለት በጥያቄ አቅራቢው (offeror) የቀረበውን የውል ቃል ውሉን ተቀብየዋለሁ የሚለው ወገን (acceptor) የቀረበለትን የውል ቃል ያለምንም ሁኔታ (unconditionally) እንዳለ መቀበል ይጠበቅበታል፡፡ ሌላ ቃል በመጨመር መልስ ከሰጠ ግን መቀበል ወይም መስማማት መሆኑ ይቀርና አፀፋዊ መጠይቅ (counter offer) ስለሚሆን በነዚህ ወገኖች መካከል የኢንሹራንስ ውል አለ ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡ በመጠየቅና መቀበል ሂደት አንደኛው

ወገን የቀረበለትን ጥያቄ መሰረት ያደረገ መልስ በወቅቱ ሳይሰጥ ቢቀር የሚኖረው ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው? የሚለውን መሰረት አድርገን በምናይበት ግዜ በአሜሪካን አገር አብዛኛዎቹ ፍ/ቤቶች የተከሰተው መዘግየት አሳማኝ ምክንያት የሌላው መዘግየት (Unreasonable delay) ነው ብለው ባመኑበት ግዜ በኩባንያው ላይ የሚከተሉትን የሃላፊነት መርሆች መሰረት በማድረግ ተጠያቂ የሚያደርጉበት አሰራርን ይከተላሉ፡፡ መርሆቹም

1. የማመልከቻ ፍርም ከሰጠውና ሞልቶ ከመለሰለት በኃላ በተገቢው ግዜ መቀበሉን ካላስታወቀው ፎርሙን በመስጠቱ ብቻ በውስጠ ታዋቂነት የውሉን ቃል እንደተቀበለ ተቆጥሮ ይህን በመጣሱ (breach of implied agreement) መሰረት በማድረግ ተጠያቂ የሚሆንበት መርህን ተከትለው የሚወሱኑበት አካሄድ፣
2. ማመልከቻ ተሞልቶ በሚቀርብበት ግዜ ለማስተማመኛ ተብሎ የተያዘ ገንዘብ (retention payment) ከነበርና ኩባንያው በወቅቱ መቀበሉን ሳይገልፅ የዘገየ እንደሆነ ኩባንያው ስምምነቱን እንደሰጠ ተቆጥሮ ተጠያቂ (liable) የሚሆንበት የአወሳሰን መርህን ፣
3. የማመልከቻ ፎርም ተሞልቶ የቀረበለት የኢንሹራንስ ኩባንያ ሳይዘገይ መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህን ግዴታውን በአግባቡ ካልተወጣ ከውል ውጭ (tort) ሃላፊነት አለበት የሚል መርህን ተከትለው ተጠያቂ የሚያደርጉበት አካሄድን ይከተላሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የአገራችን ንግድ ህግ በዚህ ጭብጥ ዙርያ ያለው አቋም ምንድን ነው? ብለን ስንመለከት አንድ የማመልከቻ ፎርም ተሞልቶ የቀረበለት የኢንሹራንስ ኩባንያ መቀበሉን ሆነ ያለመቀበሉን በመግለፅ ሂደት ላይ በመዘግየቱ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ለደረሰው ጉዳት ሃላፊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚደነግግ አይደለም ይህም ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ህግ "ዝም ማለት መቀበል ማለት አይደለም" *(non-consent it quit tacit)* የሚለውን መርህ (maxim) የሚከተል ነው፡፡ በመሆኑም ነው የኛ አገር ህግ ኢንሹራንሰ ገቢውን በማሃል ሊከሰት ከሚችለው የኢንሹራንስ ሽፋን ያለማግኘት ለመከላከል *(cover note or provisional guarantee)* አሰራርን በን/ህ/ቁ 657 (1) ላይ ደንግጎ የምናገኘው፡፡

የኢንሹራንስ ውል ልዩ ውል ቢሆንም እንደሌሎቹ ውሎች የመጠየቅና መመለስ (offer and acceptance) ችሎታ ያላቸው መሆን (competent parties) የውሉ መሰረት የሆነ ንብረት ወይ ሂወት (subject matter of insurance) የውል ፎርም እና የሚታወቅ አደጋ (certain peril) መግለፅን የሚጠይቅ የውል ዓይነት ነው፡፡ የኢንሹራንስ ውል ለመግባት ሁለት ሰነዶችን መጠቀም ይጠይቃል እነህም በኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው (offeror) የሚሞላ ቅፅ (Proposal form) እና የመድን ሽፋን ሰጪ (acceptor company) የውሉን ቃል በማተት የኢንሹራንስ ኩባንያ ስራ አስኪያጅ የሚፈርምበትና የኩባንያው ማህተም የሚያርፍበት ፖሊሲ ናቸው፡፡ የነዚህ ሰነዶች ይዘት አጠር ባለመልኩ የተመለከትን እንደሆነ በማመልከቻ ፎርሙ (insurance

proposal) ላይ እንደ የሚጠየቀው ኢንሹራንስ ሽፋን የተለያየ ቢሆኑም ሀሉም ዓይነቶች በይዘትነት አካተውት የምናገኘው ይዘት ደግሞ ኣላቸው፡፡

1. የኢንሹራንስ ሽፋን ተቀባዩ ማንነት የሚገልፅ (description of the proposed assured)
2. የአደጋው መግለጫ (description of the risk)
3. የኢንሹራንስ ሽፋን የተጠየቀበት አደጋ እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች (description of circumstances affecting the risk)
4. የኢንሹራንስ ሽፋን የተጠየቀበት አደጋ እውን ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች (Previous history of the offeror) ዋናው ይዘቱ ሆኖ ግን ደግሞ በኢንሹራንስ ሽፋን በተጠየቀበት ንብረት ወይም ሂወት ሁኔታ ላይ እንዲያተኩር ተደርጐ የተዘጋ ጁ ናቸው፡፡

## 4.2.1 የኢንሹራንስ ፖሊሲ ይዘት (contents of the policy)

የኢንሹራንስ ፖሊሲ በኩባንያዎች የሚዘጋጅ የውል ሰነድ ነው፡፡ የዚህ ሰነድ ይዘትም ከዚህ በታች በተገለፀው መልኩ ተዘጋጅቶ የሚቆይ ሰነድ ሆኖ ይዘቱም፡-

1. የኢንሹራንስ ዓይነትና ባህርያት የሚገልፅ መግብያ (preamble clause)
2. የኢንሹራንስ ሽፋን ከመቼ እስከ መቼ እንደሚቆይና የኢንሹራንስ ሽፋን ሰጪው ካሳ የሚከፍልባቸው ሁኔታዎች (operative clause)
3. የኢንሹራንስ ኩባንያው ስራስኪያጅ የሚፈርምበትና የኩባንያው ማህተም የሚያርፍበት (signature clause) የያዘ ሲሆን ፖሊሲው በዋናነት የውሉን ሁኔታዎች (conditions) የያዘው የፖሊሲው operative clause ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት የምናገኘው ክፍል የያዘ ነው፡፡

ከኢንሹራንስ አመሰራረት ጋር ተያይዞ በህግና በተግባር መካከል ያለው ሁኔታ መሰረት በማድረግ በአገራችን ያለው የፎርም ሁኔታ ምን ይመስላል? ብለን ስንመለከት ለአንድ ህግ ፊት ዋጋ ያለው የኢንሹራንስ ውል (valid contract of insurance) ፈቃድ፣ ችሎታ ያላቸው መሆንና ህጋዊ መሆን አስፈላጊ የመሆኑን ያክል የኢንሹራንስ ውል ፎርም ህግ በሚያዘው መሰረት መፈፀሙ ለውሉ ዋጋ ያለው መሆን (validity) ወሳኝ ነው፡፡ በኣገራችን የኢንሹራንስ ፎርም ምን መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1725(1) በግልፅ በፅሑፍ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ሲደነግግ በንግድ ህጉ እምብዛም ግልፅ ባልሆነ መንገድ (not vividly) በን/ህ/ቁ 657(1) የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ ፖሊሲ መደገፍ እንዳለበት በን/ህ/ቁ 667(3) የኢንሹራንስ ውል በኢንሹራንስ ፖሊሲ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑና ፖሊሲው የውሉን ዝርዝር ይዘት መያዝ ያለበት ስለመሆኑና በን/ህ/ቁ 659(1) በበኩሉ ውሉ መፈረም ያለበት ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ የኢንሹራንስ ውልን ፎርም በማስመልከት የሚደነግጉ ህጎች መገንዘብ

የሚቻለው የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በአገራችን ፍ/ብ/ህ/ቁ 1727(1) መሰረት ውሉ በተዋዋይ ወገኖች መፈረም ያለበት ስለመሆኑና ፍ/ብ/ህ/ቁ 1728(1) ውሉ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ እንዳለበት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የኢንሹራንስ ውልን አመሰራረት በተመለከተ በአገራችን ያለው አካሄድ ግን በእጅጉ ከህጉ ያፈነገጠ ነው የሚመስለው፡፡ በተግባር እየተሰራበት ያለው አካሄድ የኢንሹራንስ ሽፋን ጠያቂው ማመልከቻውን (Proposal) ሞልቶ ያቀርብና ከኩባንያው ጋር ከተነጋገሩ በኃላ ስምምነት ላይ ከደረሱ ኩባንያው የኢንሹራንስ ፖሊሲውን በሞምላት የስራ አስክያጁን ፊርማና የኩባንያው ማህተም አርፎበት ውል ነው ተብሎ ለአመልካቹ ተሰጥቶት ውል እንደተመሰረተ የሚወሰድበትን አካሄድ የሚከተል ነው፡፡ ይህም ማለት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1727(1)፣ 1728(1) መሰረት የኢንሹራንስ ውሉ፡-

- ➢ በፅሁፍ መሆን እንዳለበት
- ➢ የተዋዋይ ወገኖች ፊርማ በአንድ ሰነድ መኖር
- ➢ በምስክሮች መረጋገጥ የሚጠይቅ ሲሆን

በን/ህ/ቁ 657፣ 658፣ 659 መሰረት ደግሞ

- ማመልከቻውን የመሙላት
- ውሉን ፖሊሲ በሚባል ሰነድ ማዘጋጀት
- የፖሊሲው መፈረም የሚጠይቅ ፎርማሊቲ ያለው ነው፡፡

የፍታብሄር ህጉንና የኢንሹራንስ ህጎችን ፎርምን በማስመልከት ያላቸውን ይዘት ስንመለከት የተወሰነ ልዩነት እንዳላቸው ማስተዋል የሚቻል ቢሆንም የንግድ ህጉ የፍታብሄር ህጉ አጋዥ መሆን peter win ship በፃፉት መፅሃፍ ላይ የሰፈረውን፣

> *"…..a recent theory which is still wide spread maintains that the commercial law is autonomous. I thought it preferable, however, and more in conformity with the permanent place of civil law in the future law of Ethiopia, in the theory of obligation, and in regulation of contracts, to maintain the classic principle of the priority of civil law. Commercial law is thus a law supplementing their civil code. This principle I have incorporated in article 1 of the commercial code…*

በማለት የወሰድን እንደሆነ የኢንሹራንስ ፎርምን በማስመልከት በፍታብሄር ህጉና ንግድ ህጉ የተወሰነ ልዩነት (apparent contradiction) ያለ ቢሆንም ልዩነቱ መፈታት ያለበት የገለፁትን ገገሮው የፍታብሄር ህጎቹ ናቸው በሚል የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ ተዘጋጅቶ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ፈርመውበት በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ አለበት የሚለውን በስራ ላይ እንዲውል በማድረግ እንደሆነ የህጉ አርቃቂ ሃሳብ ቢሆንም በተግባር ከፎርም ጋር በተያያዘ ሁኔታ በፍ/ቤቶች የተለያየ አቋም ሲያዝበት የቆየው የኢንሹራንስ ፎርም ተሟልቷል አልተሟላም ክረክር የፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት በርካታ ጉዳዮችን ፍ/ብ/ህ/ቁ 1725(ለ)፣ 1727(1)

www.abyssinialaw.com

እና 1728(1) በሚያዘው መሰረት የተገባ ውል ባለመሆኑ በኩባንያውና በኢንሹራንስ ውልን ተቀባይ መካከል ውል የለም በማለት ሲወሰን እንደቆየ በፌደራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት

1. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. መልከ ኣክስዬን ማህበር - መ/ቁ 49788
2. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. ኦሮሚያ የውሃ፣ መአድንና ኢነርጂ ቢሮ - መ/ቁ 24051
3. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት V. ሳትኮን ሃ.የተ.የግ.ማህበር - መ/ቁ 30269
4. " " " V. ጥሩወርቅ መኮንን - መ/ቁ 04649
5. " " " V. ፊጣን የኮንስትራክሽ ድርጅት - መ/ቁ 39988
6. ብሄራዊ የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ኩባንያ ሀ. አለማዬህ - መ/ቁ 45444

ከሰጣቸው ውሳኔዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከዚህ በተለየ መንገድ የኢንሹራንስ ውል ፎርም መታየት ያለበት ከንግድ ህጉ አንፃር ነው በመሆኑም የንግድ ህጉ የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ የሚደረግ ስለመሆኑ በግልፅ የሚለው ነገር እስከሌለ ድረስ ወደ ፍ/ብሄር ህጉ መሄድ ሳያስፈልግ " *The special derogates over the general* " የሚለውን መርህ ተከትለን መሄድ አለብን በሚል ምክንያትና የንግድ ህጉ ለኢንሹራንስ ጉዳይ ልዩ በመሆኑ ውል አለ ተብሎ ነው መወሰድ ያለበት በማለት በስር ፍ/ቤት የተሰጡትን ውሳኔዎች ሲሽር ይታያል፤፤ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ ሳሊኒሌክስ አሽሙር ማህበር ከአዋሽ ኢንሹራንስ ጋር በሚከራከርበት ሰ.መ.ቁ . 23703 ፍ/ብሄር ህጉ በ1725 ላይ የሚደነግገው ለብዙ ዘመን የሚቆዩ ውሎች ስለሆነና የኢንሹራንስ ውል ግን ለአንድ ዓመት ብቻ የሚደረግ ውል በመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ሽሮታል፤፤ የሰበር ችሎት ውሳኔ አዋጅ ቁጥር 454/2005 በሚያዘው መሰረት ታትሞ ያልወጣ በመሆኑ አስገዳጅነት አለው ባይባልም እንደሌሎቹ ውሳኔዎች ለትችት ግን የተጋለጠ ነው፤፤ ለምን ቢባል እንደ አዘጋጁ ግንዛቤ ከሆነ " ለብዙ ዘመን የሚቆዩ ውሎች" የሚለውን የድንጋጌውን ርእስ ብቻ ወስዶ የኢንሹራንስ ውል ለአንድ አመት ብቻ የሚደረግ ውል ነው ብሎ ማሰብ በራሱ የሂወት ኢንሹራንስን ከህጉ ሽፋን የሚያገል ነው፤፤ በሌላ በኩልም ፍ/ብ/ህ/ቁ 1725 ብዙ ዘመን የሚል ቃል በርእስነት መጠቀሙ በ1725(ለ) የተደነገገውን የኢንሹራንስ ውል በፅሁፍ መሆን አለበት የሚለውን የህጉን ሃይለ ቃል መሻር አልነበረበትም፤፤ በመሆኑም የሰበር ውሳኔም ቢሆን በስር ፍ/ቤቶች ከሚታየው የአተረጓጎም ችግር እምብዛም ችግሩን በሚፈታ መንገድ የተሰጠ ውሳኔ ነው የሚሰኝ እይደለም፤፤ ስለዚህ የኢንሹራንስ ፎርምን በማስመልከት በፍ/ብሔር ህጉና የንግድ ህጉ ያሉት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በኣዋጅ ቁጥር 454/2005 የተሰጠውን ስልጣን መሰረት በማድረግ ለኣመታት የቆየውን ኣወዛጋቢ ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ያደረገ ነው በሎ ለማለት የሚሰደፍር አይደለም፡፡

## የኢንሹራንስ መሰረታዊ መርሆች (Basic Principles of Insurance)

### የጉዳት ካሳ ፅንሰ ሓሳብ (The concept of Indemnity)

የኢንሹራንስ ውል ዋስትና የተሰጣቸው አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ሃላፊነት የሚወስድበት ውል አይደለም፡፡ የኢንሹራንስ ዋስትና በተሰጣቸው አደጋዎች ምክንያት የሚደርሰን የገንዘብ ጉዳትና ለመተካት የሚዳረግ ውል ነው፡፡ በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት በሞተር ኢንሹራንስ ፖሊሲ ዋስትና ስለተሰጠው መኪና የኢንሹራንስ ስፋን የሚደረግለት መኪናው አደጋ እንዳይደርስበት መከላከል ሳይሆን በአደጋ ምክንያት የሚደርስ የገንዘብ ጉዳትን ለመካስ ነው፡፡ በመሆኑም በሞተር ፖሊሲው ዋስትና የተሰጠው ነገር መኪናው ሳይሆን የኢንሹራንስ ገቢው የገንዘብ ጥቅም ነው፡፡ የኢንሹራንስ ዋስትና የተሰጠው ነገር ምናልባትም ንብረት ሆኖ የራስና ከእቃው ተለይቶ የማይታይ ዋጋ ቢኖረውም በኢንሹራንስ ውል የውል ጉዳይ (subject matter of Insurance contract) የሚሆነው ማለትም የተዋዋዮች ግዴታ የሚመሰረትበት ነገር ኢንሹራንስ ገቢው በንብረቱ ላይ ያለው የገንዘብ ጥቅም ኢንሹራንስ ገቢው ኢንሹራን ለመግባት የሚያስችል ሕጋዊ መብት ይሰጠዋል፡፡ የኢንሹራንስ ውል በሕግ ድጋፍ እንዲያገኝ ለማድረግ ውሉ ኢንሹራንስ ለመግባት በሚያስችል ጥቅም መደገፍ አለበት፡፡ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ከሌለ የኢንሹራንስ ውል ሊኖር አይችልም በሌላ አነጋገር ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አለመኖር ውሉን ከመሰረቱ ያፈርሰዋል፡፡

የካሳ መርህ የሚመነጨው የኢንሹራንስ ውሎች የካሳ ውሎች ብቻ ናቸው ከሚለው ህግ ነው፡፡ ይህን ማለት ጉዳቱ መካስ ያበለት ኢንሹራንስ ገቢው በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ከነበረበት የገንዘብ አቋም በማያሳንስ ወይም በማያስበልጥ መንገድ ነው፡፡ የመርሁ ግብ ኢንሹራንስ ገቢው ጉዳት ከደረሰበት በኋላ በተቻለ መጠን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደነበረበት የገንዘብ አቋም መመለስ ነው፡፡ የዚህ መርህ ውጤትም ኢንሹራንስ ገቢው ከጉዳቱ ትርፍ እንዳያገኝ ወይም ማናቸውንም ጥቅም እንዳያገኝ መከልከል ነው፡፡ የመርሁ ዋነኛ ሓሳብም ካሳ ከጉዳቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ነው፡፡ ማነስም መብዛትም የለበትም፡፡ ካሳው ከጉዳቱ የሚበልጥ ከሆነ ኢንሹራንስ ገቢው ትርፍ ማግኘቱ ሲሆን ይህ ደግሞ ስለ ኢንሹራንስ የመግባት ጥቅም በሚገልፀው ክፍል ውስጥ ከተጠቀሰው ኢንሹራንስ ዓላማ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በሌላ በኩል ካሳው ያነሰ ከሆነ ኢንሹራንስ ገቢው አልተካሰም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የካሳ መርሆዎች ሚዛኑ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይሞክራል፡፡ ከደረሰው ጉዳት ትርፍ ማግኘት የሚቻል ቢሆን ኢንሹራንስ ገቢው ሆነ ብሎ ጉዳቱን እንዲያመጣ ይገፋፋል፡፡ እንዲሁም ኢንሹራንስ ገቢው ንብረቱን ለመጠበቅና አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል ግዴለሽ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡ በመሆኑም የዚህ መርህ አስፈላጊነት ከሕዝብ ጥቅም ይመነጫል፡፡ ሆነ ተብለው የሚመጡ ጉዳቶች የአገር ሃብት ያባክናሉ በመሆኑም የህዝብ ጥቅምና የህዝብ ፖሊሲ የኢንሹራንስ ውሎች ካሳ እና ካሳ ብቻ የሚሰጠው እንዲሆኑ ያስገድዳሉ፡፡

ኢንሹራንስ ከጋራ ገንዘብ ጉዳቶችን መካፈል በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጋራ ገንዘቡ ማለትም የአረቦን መዋጮ የሚወስነው ቀደም ብለው በደረሱ ጉዳቶች ላይ በመመስረት እንደመሆኑ ከጋራ ገንዘቡ የሚከፈለው ክፍያ ኢንሹራንስ ገቢው ትርፍ ወይም ጥቅም ሳያገኝ በደረሰበት ጉዳት ልክ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የካሳ መርህ ተግባራዊ የማይሆን ከሆነ የኢንሹራንስ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥርና ለሃብት ብክነት የሚዳርግ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ የኢንሹራንስ ውል መሰረቱ ካሳ መክፈል በሚሆንበት ግዜ የሚከተለው ዓላማ አደጋ ያገጠመውን ባለንብረት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት የኢኮኖሚ ሁኔታ መመለስ ሲሆን የካሳው መጠንም ከደረሰበት ጉዳት መብለጥ የሌለበት መሆኑን ን/ህ/ቁ 678 መሰረት በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሌ የጉዳት ካሳው መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል መሆን አለበት ማለት አይደለም ምክንያቱም ኢንሹራንስ ሽፋን በከፊል በመግዛት ባለንብረቱ ቀሪውን ራሱ በንብረቱ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደነበረበት የመመለስ አሰራር (self insuring) በጉዳት ካሳ መርህ የሚከለከል ባለመሆኑ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሚኖረው የካሳ አከፋፈል መሰረት ተደርጎ የሚወስደው የጉዳቱ መጠን ሳይሆን የኢንሹራንስ ሽፋኑ መጠን ነው፡፡

### 4.3.2. ኢንሹራንስ ሊገባባት የሚችል ጥቅም (Insurable interest)

የኢንሹራንስ ውል ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም መኖርን እንደ አንድ ህጋዊ መስፈርት የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህም ነው አንድ Patterson የተባሉ የዘርፉ ተመራማሪ "An insurable interest in its broadest sense is a relation between the insured and the event will cause substantial loss or injury of the some kind to the insured." በማለት የሚገልፁት፡፡ ይህን ዘርዘር ባለ መልኩ ስናይ አንድ ሰው ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም አለው የሚባለው መቼ ነው? የመለውን ያነሳን እንደሆነ Professor Vance በፃፉት መፅሃፍ ላይ በሚመለከተው መልኩ አንድ ሰው ኢንሹራንስ ሊገባበት የሚችል ጥቅም አለው የሚባለው፡-

- *When the insured possesses a legal title to the property insured, whether vested or contingent, defensible or indefensible.*
- *When he has an equitable title, of whatever character and in whatever manner acquired.*
- *When he possesses a qualified property or possessor right in the subject of the insurance, such as that of bailee.*
- *When he has mere possession or right of possession.*
- *When he has neither possession of the property, nor any other legal interest in it, but stands in such elation with respect to it that he may suffer, from its*

*destruction, loss of legal right dependent up on its continued existence.* ሲኖር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህ የኢንሹራንስ መርህ በአገራችን ን/ህ/ቁ 675 እና 693 ተደንግጎ የምናገኘው ሲሆን መርሁ ህዝባዊ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ የዜጎች ጥቅምን የማስጠበቅ ዓላማ ያለው ነው፡፡ አንድ ሰው የኢንሹራንስ ሽፋን ሊሰጠው የሚያስችል ጥቅም አላው ብሎ ለማለት ከሂወት ኢንሹራንስ ውጭ ባሉ ሌሎች የኢንሹራንስ ዓይነቶች የኢንሹራንስ ሽፋን የሚሰጠው ነገር በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ የካሳ መሰረተ ሃሳብ ውጤት ከሆኑ ነገሮች አንዱ ኢንሹራንስ ገቢው የሚጠይቀው ካሳ የደረሰበትን ኪሳራ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ኪሳራ እንዲደርሰበት ከተስፈለገ በወደመው ወይም በተጎዳው ንብረት ላይ ጥቅም ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ ኢንሹንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅምን የሚደግፉ ዋና ዋና ሁኔታዎች የሚከተሉ ናቸው፡፡

ሀ. ዋስትና ሊሰጠው የሚቻል ንብረት፣ መብት፣ ጥቅም ፣ ሕይወት፣ ሃላፊነት መኖር

ለ. ይህ ንብረት መብት ሕይወት ወዘተረፈ የኢንሹራንስ ዋስትና የሚሰጠው ነገር (subject mater of Insurance) መሆን አለበት፣

ሐ. ኢንሹራንስ ገቢው የኢንሹራንስ ዋስትና ከሚሰጠው ነገር ጋር ሕጋዊ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማሳየት ማለትም ንብረቱ መብቱ ጥቅሙ ሕይወቱ ሲጠበቅ ተጠቃሚ መሆን ከነዚህ ነገሮች መጉዳት እና ከሃላፊነቱ መፈጠር ደግሞ የሚጎዳ መሆኑን ማሳየት

መ. የኢንሹራንስ ዋስትና በተሰጠው ነገር እና በኢንሹራንስ ገቢው መካከል በሕግ ተቀባይነት ያለው ግንኙነት መኖር ኣለበት

### 4.3.2.1ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም አፈጣጠር ወይም አነሳስ

❖ **ከባለቤትነት የሚነሳ ጥቅም**

የንብረት ባለቤትነት ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም መኖሩን ለማረጋገጥ የተለመደውና ግልፅ የሆነው ምሳሌ ነው፡፡ ለምሳሌ የአንድ ህንፃ ባለቤት ህንፃው በእሳት ቢጋይ ወይም በሌላ አደጋ ቢጎዳ የገንዘብ ኪሣራ ይደርስበታል፡፡ በመሆኑም ሕጉ ለባንብረቱ ኢንሹራንስ የመግባት እና ኪሳውን የማግኘት መብት ይሰጠዋል፡፡ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችል ጥቅም ከጋራ ባለቤትነትም ይገኛል፡፡

❖ **ፍፁም ከሆነ ባለቤትነትም ባሻገር ከፊል ባለቤትነት**

ከፊል ባለቤትነት ባለበት ጊዜ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችለው ጥቅም ይኖራል፡፡ በርካታ ኢንሹራንስ ለመግባት የሚያስችሉ ጥቅሞች በአንድ ንብረት ላይ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ባለቤትና መያዣ ያዥ በአንድ ንብረት ላይ ጥቅም ይኖራቸዋል፡፡ መያዣ ያገዙ ማለትም ገንዘቡን ያበደረው ሰው መያዣ የተያዘው ንብረት እንዲጠበቅ ስለሚፈልግ በዚህ ንብረት ላይ

www.abyssinialaw.com

ERROR: syntaxerror
OFFENDING COMMAND: --nostringval--

STACK: